# ሉቃስ የጻፈው

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል

### መግቢያ

የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስን የሚያቀርበው አስቀድሞ ይመጣል የተባለው የእስራኤል አዳኝ ፥ እንዲሁም የሰው ልጆች ሁሉ አዳኝ እንደሆነ አድርጎ ነው ፤ ሉቃስ ፥ ኢየሱስን የእግዚአብሔር መንፈስ የጠራው "ለድኾች ወንጌልን እንዲሰብክ" መሆኑንና ይህም ወንጌል ሰዎች ላለባቸው ልዩ ልዩ ችግር መፍትሔ የያዘ መሆኑን ይተርካል ፤ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ በተለይም ስለ ኢየሱስ መምጣት በሚያበሥሩት በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎችና እንደገናም ስለ ኢየሱስ ወደ ሰማይ መውጣት በሚናገሩት የመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ጐልቶ የተነገረው ስለ ደስታ ነው ፤ ከኢየሱስ ወደ ሰማይ መውጣት በኋላ የክርስትና እምነት እንዴት እንዳደገና እንደተስፋፋ የሚያስረዳው ታሪክ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በዚሁ ጸሐፊ ተነግሮአል ።

ስለ መላእክት ዝማሬ ፥ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ እረኞች እንደጐበኙት የሚናገረው ታሪክ ፥ ኢየሱስ በልጅነቱ ወደ ቤተ መቅደስ ስለመሄዱ ፥ የርኅሩኅ ሳምራዊና ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ብቻ የሚገኙ ናቸው ፤ በወንጌሉ ውስጥ ዳር እስከ ዳር ታላቅ አትኩረት የተደረገው ስለ ጸሎት ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፥ ሴቶች በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ስላላቸው ስፍራና እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ስለማለቱ ነው ።

---

## ምዕራፍ 1

1 ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ!
በእኛ መካከል የተፈጸሙትን ነገሮች የሚገ
ልጥ ታሪክ ከዚህ ቀደም ብዙዎች ጽፈዋል ።
2 ይህን መልእክት ለእኛ ያስተላለፉልን ከመጀ
መሪያው አንሥቶ የዐይን ምስክሮችና የምሥ
ራቹ ቃል አገልጋዮች የነበሩት ናቸው ። 3 እንዲ
ሁም እኔ ከመጀመሪያው አንሥቼ ሁሉን ነገር
በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኋላ ታሪኩን በቅደም
ተከተል እጽፍልህ ዘንድ መልካም ሆኖ ታየኝ ።
4 ይህንንም ማድረጌ የተማርከውን ትምህርት
እውነተኛነት በደምብ እንድትረዳ ብዬ ነው ።

### የአጥማቂው ዮሐንስን መወለድ መልአኩ ገብርኤል አስቀድሞ ተናገረ

5 ሄሮድስ በይሁዳ አገር ንጉሥ በሆነበት ዘመን
ከአብያ የክህነት ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል
ካህን ነበር ። እርሱ ከአሮን ዘር የምትወለድ ኤልሳ
ቤጥ የምትባል ሚስት ነበረችው ። 6 ሁለቱም በእ
ግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ ፤ የጌታንም ትእዛ
ዝና ሕግ ያለ ነቀፋ ይጠብቁ ነበር ። 7 ኤልሳቤጥ
መኻን ስለሆነች ልጅ አልነበራቸውም ፤ ደግሞ
ሁለቱም በጣም አርጅተው ነበር ።
8 በዚያን ጊዜ የዘካርያስ የክህነት ሥራ
ቡድን ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ተረኛ
ነበር ፤ ስለዚህ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት የክህ
ነቱን አገልግሎት በመፈጸም ላይ ነበር ። 9 እንደ
ካህናት አሠራር ደንብ ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ገብቶ ዕጣን ለማጠን ዕጣ ደረሰው ።
10 በቤተ መቅደሱም ውስጥ ዕጣን በሚታጠን
በት ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጪ ቆመው ይጸልዩ
ነበር ። 11 የእግዚአብሔር መልአክ ዕጣን በሚ
ጤስበት መሠዊያ በስተቀኝ በኩል ቆሞ ለዘካር
ያስ ታየው ። 12 ዘካርያስ መልአኩን ባየው ጊዜ
ደንግጦ በፍርሃት ተዋጠ ። 13 መልአኩ ግን እን
ዲህ አለው ፥ "ዘካርያስ ሆይ! አትፍራ ፤ ጸሎ
ትህ ተሰምቶልሃል ፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ
ልጅ ትወልድልሃለች ፤ ስሙንም ዮሐንስ ብለህ
ትጠራዋለህ ። 14 የእርሱ መወለድ ለአንተ ተድ
ላና ደስታ ይሆንልሃል ፤ ብዙዎችም በመወለዱ
እንዲሁ ደስ ይላቸዋል ። 15 ምክንያቱም እርሱ
በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል ፤ የወይን
ጠጅና ሌላም የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ፤
ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተ
ሞላ ይሆናል ። 16 እርሱ ከእስራኤል ሕዝብ
ብዙዎቹን ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላካቸው
ይመልሳቸዋል ፤ 17 በመንፈስና በኀይል እንደ
ነቢዩ ኤልያስ ሆኖ ሕዝቡን ለጌታ ያዘጋጃል ፤
እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው ፥ የማይ
ታዘዙትንም ሰዎች ልብ ወደ ጻድቃን ጥበብ
ይመልሳል ።"

---

1፥5 ፦ 1ዜ.መ. 24፥10 ። 1፥15 ፦ ዘኍ. 6፥3 ። 1፥17 ፦ ሚል. 4፥5-6 ።

[18]ዘካርያስ ግን መልአኩን “ይህ ነገር እር
ግጥ መሆኑን በምን ዐውቃለሁ? እኔ አርጅቻ
ለሁ ፤ ሚስቴም በዕድሜዋ ገፍታለች” አለው ።
[19]መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰለት ፦
“እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብር
ኤል ነኝ ፤ ይህን የምሥራች እንድነግርህ ከእግ
ዚአብሔር ዘንድ ተልኬ መጥቻለሁ ። [20]አንተ
ግን ጊዜው ሲደርስ የሚፈጸመውን ቃሌን አላ
መንህም ፤ ስለዚህ ይህ የነገርሁህ ሁሉ በጊዜው
እስኪፈጸም ድረስ ድዳ ትሆናለህ ፤ መናገርም
አትችልም ።”
[21]በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ዘካርያስን ይጠባበቁ
ነበር ፤ በቤተ መቅደስ ውስጥ ስለዘገየባቸውም
ተገረሙ ። [22]ዘካርያስ ከቤተ መቅደስ በወጣ
ጊዜ ከሰዎቹ ጋር መነጋገር አልቻለም ፤ ስለዚህ
እነርሱ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አንድ ነገር የታ
የው መሆኑን ዐወቁ ፤ እርሱ በእጁ እየጠቀሰ ያስ
ረዳቸው ነበር ። በዚህም ሁኔታ ድዳ ሆኖ ቆየ ።
[23]የአገልግሎቱም ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ ዘካ
ርያስ ወደ ቤቱ ሄደ ። [24]ከጥቂት ጊዜም በኋላ
ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች ፤ አምስት ወር በቤ
ትዋ ውስጥ ተሸሽጋ ቆየች ። [25]እርስዋ “እግዚ
አብሔር በምሕረቱ ጐብኝቶ ይህን መልካም
ነገር አደረገልኝ ፤ በሰዎች መካከል የነበረብኝን
ነቀፌታ አስወገደልኝ” አለች ።

### የኢየሱስን መወለድ መልአኩ ገብርኤል አስቀድሞ አበሠረ

[26]ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር
መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ
ናዝሬት ተላከ ። ናዝሬት በገሊላ ክፍል ሀገር
የምትገኝ ከተማ ናት ። [27]መልአኩ የተላከው
ማርያም ወደምትባል ወደ አንዲት ድንግል
ነው ። እርስዋ ከዳዊት ዘር ለሆነው ዮሴፍ ለሚ
ባል ሰው የታጨች ነበረች ። [28]መልአኩም ወደ
እርስዋ መጥቶ “አንቺ ጸጋን የተሞላሽ ፤ ሰላም
ለአንቺ ይሁን ፤ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር
ነው ፤ [አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ”
አላት ።]
[29]እርስዋም በመልአኩ አነጋገር በጣም ደን
ግጣ “ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ ይሆን?” ብላ
አሰበች ። [30]መልአኩም እንዲህ አላት ፦ “ማር
ያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝተ
ሻልና አትፍሪ ፤ [31]እነሆ ትፀንሻለሽ ፤ ወንድ
ልጅም ትወልጃለሽ ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋ
ለሽ ። [32]እርሱ ታላቅ ይሆናል ፤ የልዑል እግዚ
አብሔር ልጅም ይባላል ፤ ጌታ አምላክ የአባ
ቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ። [33]በእስራኤ
ልም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፤ መንግሥቱም
መጨረሻ የለውም ።”
[34]ማርያም መልአኩን “እኔ ድንግል ነኝ ፤
ታዲያ ይህ ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል?” አለ
ችው ።
[35]መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ ፦ “መን
ፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፤ የልዑል እግ
ዚአብሔርም ኀይል በአንቺ ላይ ይሆናል ፤ ስለ
ዚህ ከአንቺ የሚወለደው ሕፃን ቅዱስ ነው ፤
የእግዚአብሔርም ልጅ ይባላል ። [36]ዘመድሽ
ኤልሳቤጥ እንኳ መኻን ስትባል ኖራ አሁን በስ
ተእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች ፤ ከፀነሰችም
እነሆ ስድስተኛ ወርዋ ነው ። [37]ለእግዚአብሔር
እኮ የሚሳነው ነገር የለም ።”
[38]ከዚያም በኋላ ማርያም “እነሆ እኔ የእግ
ዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ፤ አንተ እንዳልህ ይሁ
ንልኝ” አለችው ። በዚህ ጊዜ መልአኩ ተለይቶ
አት ሄደ ።

### ማርያም ኤልሳቤጥን ጐበኘች

[39]በዚያን ጊዜ ማርያም ኤልሳቤጥን ለመጐ
ብኘት በተራራማው በይሁዳ አገር ወዳለችው
ከተማ በፍጥነት ተነሥታ ሄደች ። [40]ወደ ዘካር
ያስ ቤትም ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ ሰጠ
ቻት ። [41]ኤልሳቤጥ የማርያምን የሰላምታ ቃል
በሰማች ጊዜ በማሕፀንዋ የነበረው ሕፃን ዘለለ ።
ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች ።
[42]ድምፅዋንም ከፍ አድርጋ እንዲህ አለች ፦
“አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ ፤ ከአንቺ
የሚወለደውም ልጅ የተባረከ ነው ፤ [43]የጌታዬ
እናት ልትጐበኘኝ መምጣትዋ ለእኔ እንዴት
ያለ ታላቅ ክብር ነው! [44]የሰላምታሽን ድምፅ
ገና ከመስማቴ በማሕፀኔ ያለው ሕፃን በደስታ
ዘለለ ። [45]አንቺ እግዚአብሔር የተናገረውን
ሁሉ የሚፈጽም መሆኑን በማመንሽ ምንኛ የታ
ደልሽ ነሽ ።”

### የማርያም የምስጋና ጸሎት

[46]ማርያም እንዲህ አለች ፦
“ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብራለች ፤
[47]መንፈሴ በአምላኬ በመድኃኒቴ
ትደሰታለች ፤
[48]እግዚአብሔር እኔን ዝቅተኛ አገልጋይቱን
ተመልክቶአልና ፦
ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ
የተመሰገንሽ ነሽ ይለኛል ፤
[49]ምክንያቱም ኀያሉ እግዚአብሔር ትልቅ
ነገር ስላደረገልኝ ነው ፤
ስሙም ቅዱስ ነው ።
[50]እግዚአብሔር ለሚፈሩት ሰዎች ሁሉ
ከትውልድ እስከ ትውልድ ምሕረቱን
ያደርጋል ።

1፥19 ፡- ዳን. 8፥16 ፤ 9፥21 ። 1፥27 ፡- ማቴ. 1፥18 ። 1፥31 ፡- ማቴ. 1፥21 ። 1፥32-33 ፡- 2ሳሙ. 7፥12-13 ፣16 ፤
ኢሳ. 9፥7 ። 1፥37 ፡- ዘፍ. 18፥14 ። 1፥46-55 ፡- 1ሳሙ. 2፥1-10 ። 1፥48 ፡- 1ሳሙ. 1፥11 ።



[51]በብርቱ ክንዱ ኀይሉን አሳይቶአል ፤
ትዕቢተኞችንም ከነአሳባቸው
በትኖአቸዋል ።
[52]ታላላቅ ገዦዎችን ከዙፋናቸው
አውርዶአቸዋል ፤
ዝቅተኞችን ግን በክብር ከፍ
አድርጎአቸዋል ።
[53]የተራቡትን በመልካም ነገር
አጥግቦአቸዋል ፤
ሀብታሞችን ግን ባዶ እጃቸውን
ሰዶአቸዋል ፤
[54-55]ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ያሳየውን
ምሕረት በማስታወስ ፦
አገልጋዩን እስራኤልን ረድቶታል ።
ይህንንም ያደረገው ለቀድሞ አባቶቻችን
የሰጠውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም
ነው ።”
[56]ማርያም ከኤልሳቤጥ ጋር ሦስት ወር
ያህል ከቆየች በኋላ ወደ ቤትዋ ተመልሳ
ሄደች ።

### የአጥማቂው ዮሐንስ መወለድ

[57]ኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰና ወንድ
ልጅ ወለደች ። [58]ጐረቤቶችዋና ዘመዶችዋ
ሁሉ እግዚአብሔር ምሕረቱን እንዳደረገላት
ሰምተው ከእርስዋ ጋር ተደሰቱ ።
[59]ሕፃኑ በተወለደ በስምንተኛው ቀን በግዝ
ረቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት ጐረቤቶችዋና
ዘመዶችዋ ተሰብስበው መጡ ፤ ባባቱ ስም ዘካር
ያስ ብለው ሊጠሩት ፈልገው ነበር ፤ [60]እናቱ ግን
“እንዲህ አይሆንም ፤ ስሙ ዮሐንስ ነው” አለች ።
[61]እነርሱም “ከዘመዶችሽ በዚህ ስም የተ
ጠራ ማንም የለም እኮ?” አሉአት ። [62]ከዚህም
በኋላ አባቱን “ልጅህ ማን ተብሎ እንዲጠራ
ትፈልጋለህ?” ብለው በምልክት ጠየቁት ።
[63]ዘካርያስም መጻፊያ እንዲሰጡት ጠይቆ
“ስሙ ዮሐንስ ነው” ብሎ ጻፈ ፤ ሁሉም በዚህ
ነገር ተደነቁ ። [64]በዚያን ጊዜ ዘካርያስ ምላሱ
ተፈትቶለት መናገር ቻለ ፤ እግዚአብሔርንም
ማመስገን ጀመረ ። [65]ከዚህም የተነሣ በጐረቤቶ
ቻቸው ሁሉ ፍርሃት አደረባቸው ፤ ዜናውም
በተራራማው በይሁዳ አገር ሁሉ ተሰማ ።
[66]ይህን ነገር የሰሙ ሁሉ “ይህ ሕፃን ምን
ሊሆን ይሆን?” እያሉ ይጠያየቁ ነበር ። ምክን
ያቱም የእግዚአብሔር ረድኤት በእርግጥ ከእ
ርሱ ጋር ስለነበር ነው ።

### ዘካርያስ የተናገረው ትንቢት

[67]የሕፃኑ አባት ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ ፦
[68]“ሕዝቡን በምሕረት ስለጐበኘና ስላዳነ
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ይመስገን ፤
[69]ከአገልጋዩ ከዳዊት ዘር ታላቅ አዳኝ
አስነሥቶልናል ፤
[70]አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ
እንደተናገረ ፤
[71]ከጠላቶቻችንና ከባላጋራዎቻችን እጅ
አድኖናል ፤
[72]ይህንንም ማድረጉ ለአባቶቻችን
ምሕረትን እንደሚያደርግና
የተናገረውንም ቅዱስ ቃል ኪዳኑን
እንደሚፈጽም በማሰብ ነው ።
[73]ይህንንም ቃል ኪዳን በመሐላ የሰጠው
ለአባታችን ለአብርሃም ነበር ፤
[74]የተስፋውም ቃል ከጠላቶቻችን እጅ ነፃ
ወጥተን
ያለፍርሃት እንድናገለግለው ነው ፤
[75]እንዲሁም በሕይወታችን ዘመን ሁሉ
በእግዚአብሔር ፊት በቅድስናና
በጽድቅ መኖር እንድንችል ነው ።
[76]ደግሞም አንተ ሕፃን ፦ የልዑል
እግዚአብሔር ነቢይ ትባላለህ ።
መንገዱን ለማዘጋጀት ቀድመህ በጌታ
ፊት ትሄዳለህ ።
[77]የኃጢአታቸውን ይቅርታ የሚያገኙበትን
የደኅንነት ዕውቀት
ለሕዝቡ ትሰጣለህ ።
[78]ይህም ሊሆን የቻለው በአምላካችን
ምሕረትና ርኅራኄ ነው ፤
ስለዚህ የደኅንነት ፀሐይ ከሰማይ
ሊወጣልን ነው ።
[79]እርሱ በጨለማና በሞት ጥላ ሥር ላሉት
ሁሉ ያበራል ፤
እርምጃችንንም ወደ ሰላም መንገድ
ይመራል ።”
[80]ሕፃኑም አደገ ፤ በመንፈስም ጠነከረ ፤ ለእ
ስራኤል ሕዝብ እስኪታየበት ጊዜ ድረስ በበረሓ
ኖረ ።

## ምዕራፍ 2

### የኢየሱስ መወለድ
(ማቴ. 1፥18-25)

[1]በዚያን ጊዜ በሮማውያን ግዛት ያሉ ሰዎች
ሁሉ ለሕዝብ ቈጠራ እንዲመዘገቡ የሮም ቄሳር
አውግስጦስ አዘዘ ። [2]ይህም የመጀመሪያው የሕ
ዝብ ቈጠራ በተደረገ ጊዜ ቄሬኔዎስ የሶርያ
አገረ ገዥ ነበር ። [3]ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው
ስሙን ለማስመዝገብ ወደ ትውልድ አገሩ
ይሄድ ነበር ።

1፥52 ፡- ኢዮብ 5፥11 ፤ 12፥19 ። 1፥55 ፡- ዘፍ. 17፥7 ። 1፥59 ፡- ዘሌ. 12፥3 ። 1፥76 ፡- ሚል. 3፥1 ።
1፥79 ፡- ኢሳ. 9፥2 ።

⁴ዮሴፍም በገሊላ አውራጃ ከምትገኘው ከና
ዝሬት ከተማ ተነሥቶ በይሁዳ አገር ወደምትገ
ኘው ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ሄደ ፤
ምክንያቱም እርሱ በትውልዱ የዳዊት ዘር ስለነ
በረ ነው ። 5 ሊጻፍ የሄደውም ፀንሳ ከነበረችው
ከእጮኛው ከማርያም ጋር ነው ። 6 ሁለቱም
በቤተልሔም ከተማ ሳሉ ማርያም የመውለጃዋ
ጊዜ ደረሰ ። 7 በዚያም የበኲር ልጅዋን ወለ
ደች ፤ በመታቀፊያ ጨርቅ ጠቀለለችው ፤ በእን
ግዶች ማደርያ ስፍራ ስላላገኙ በበረት በከብ
ቶች መመገቢያ ግርግም ውስጥ አስተኛችው ።

## እረኞችና መላእክት

8 በዚያም አገር ከከተማው ውጪ በሜዳ ላይ
ሌሊት መንጋቸውን እየጠበቁ የሚያድሩ እረ
ኞች ነበሩ ። 9 እነሆ ለእነርሱ የእግዚአብሔር
መልአክ ታያቸው ፤ የእግዚአብሔርም የክብር
ብርሃን በላያቸው አበራ ፤ ስለዚህም በጣም
ፈሩ ፤ 10 መልአኩ ግን እንዲህ አላቸው ፦ “አይ
ዞአችሁ ፥ አትፍሩ ፤ ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ደስታ
የሚሆን መልካም ዜና ይዤላችሁ መጥቻለሁ ፤
11 እነሆ ዛሬ በዳዊት ከተማ አዳኝ ተወልዶ
ላችኋል ፤ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው ። 12 ምል
ክቱም ይህ ነው ፤ በመታቀፊያ ጨርቅ የተጠቀ
ለለ ሕፃን በበረት ፥ በከብቶች መመገቢያ ግር
ግም ውስጥ ተኝቶ ታገኛላችሁ ።”

13 በድንገት ብዙ የሰማይ መላእክት ከመል
አኩ ጋር አብረው ታዩ ፤ እግዚአብሔርንም በማ
መስገን ፦

14 “በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን ፤
በምድርም እግዚአብሔር ለሚወዳቸው
ሰዎች ሁሉ ሰላም ይሁን” ይሉ
ነበር ።

15 መላእክቱ ተለይተዋቸው ወደ ሰማይ
በወጡ ጊዜ እረኞቹ እርስ በርሳቸው “እንግዲህ
ወደ ቤተልሔም እንሂድ ፤ አሁን የተፈጸመው
ንና እግዚአብሔር የገለጠልንን ነገር እንይ”
ተባባሉ ።

16 በፍጥነት ሄደው ማርያምንና ዮሴፍን
አገኙ ፤ ሕፃኑንም በበረት ፥ በከብቶች መመገ
ቢያ ግርግም ውስጥ ተኝቶ አዩት ። 17 ሕፃኑንም
ካዩ በኋላ መልአኩ ስለ እርሱ የነገራቸውን
አወሩ ። 18 ይህንንም የሰሙ ሁሉ እረኞቹ ባወሩ
ላቸው ነገር ተደነቁ ። 19 ማርያም ግን ይህን
ሁሉ ነገር በልብዋ ይዛ ታሰላስለው ነበር ።
20 እረኞቹ ፥ ሁሉ ነገር መልአኩ እንዳላቸው
ሆኖ በማየታቸውና በመስማታቸው እግዚአብሔ
ርን እያከበሩና እያመሰገኑ ወደ ስፍራቸው
ተመለሱ ።

## ሕፃኑን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት

21 ከስምንት ቀን በኋላ ሕፃኑ በሚገረዝበት
ሥነ ሥርዓት ላይ ፥ ስሙ “ኢየሱስ” ተብሎ
ተጠራ ። ይህም ገና ከመፀነሱ በፊት መልአኩ
ያወጣለት ስም ነው ።

## ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደ

22 በሙሴ ሕግ መሠረት የመንጻት ሥርዓት
የሚፈጸምበት ጊዜ ደረሰ ፤ ስለዚህ ሕፃኑን ለእግ
ዚአብሔር ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም ይዘውት
ሄዱ ። 23 ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት በእግ
ዚአብሔር ሕግ “ወንድ የሆነ በኲር ልጅ ሁሉ
ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ የተቀደሰ ይሆናል”
የሚል ትእዛዝ ተጽፎ ስለነበር ነው ። 24 እንዲ
ሁም በእግዚአብሔር ሕግ “ሁለት ዋኖሶች
ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች ለመሥዋዕት
ማቅረብ አለበት” የሚል ትእዛዝ ነበረ ።

25 በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚ
ባል አንድ ሰው ነበር ፤ እርሱም ሕይወቱን ለእ
ግዚአብሔር የሰጠ ጻድቅ ሰው ነበር ፤ የእስራኤ
ልን የመዳን ተስፋ ይጠባበቅ ነበር ፤ መንፈስ
ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበር ። 26 እርሱ የእግዚአ
ብሔርን መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ
ቅዱስ ገልጦለት ነበር ። 27 በዚያን ቀን መንፈስ
ቅዱስ አነሣሥቶት ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ ፤
ዮሴፍና ማርያምም የሕጉን ሥነ ሥርዓት ለመ
ፈጸም ሕፃኑን ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ ።
28 በዚያን ጊዜ ስምዖን ሕፃኑን አቅፎ እግዚአብ
ሔርን በማመስገን እንዲህ አለ ፤

29 “ጌታ ሆይ ! እነሆ የሰጠኸኝ የተስፋ ቃል
ተፈጸመ ፤
እንግዲህ አሁን እኔን አገልጋይህን
በሰላም አሰናብተኝ ፤
30 ምክንያቱም ማዳንህን በዐይኔ አይቻለሁ ፤
31 እርሱም በሕዝቦች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸው
ነው ፤
32 እርሱ ለአሕዛብ እውነትን የሚገልጥ
ብርሃን ይሆናል ፤
ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው ።”

33 ዮሴፍና ማርያም ስለ ሕፃኑ በተባለው
ነገር ሁሉ ይደነቁ ነበር ። 34 ስምዖን ከባረካ
ቸው በኋላ ፥ በተለይ የሕፃኑን እናት ማርያምን
እንዲህ አላት ፥ “እነሆ ይህ ሕፃን በእስራኤል
ውስጥ ለብዙዎቹ የመጥፋት ፥ ለብዙዎቹ ግን
የመዳን ምክንያት ይሆናል ፤ እርሱም ብዙዎች
የማይቀበሉት ምልክት ይሆናል ። 35 በዚህም
በብዙዎች ልብ ያለው ስውር አሳብ ይገለጣል ፤
የአንቺንም ልብ የሐዘን ሰይፍ ሰንጥቆት ያል
ፋል ።”

2፥21 ፦ ዘሌ. 12፥3 ፤ ሉቃ. 1፥31 ። 2፥22-24 ፦ ዘሌ. 12፥6-8 ። 2፥23 ፦ ዘጸ. 13፥2 ፡12 ።
2፥32 ፦ ኢሳ. 42፥6 ፤ 49፥6 ፤ 52፥10 ።



36 እንዲሁም በዚያን ጊዜ ከአሴር ነገድ የሆ
ነች የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢ
ይት ነበረች ። በዕድሜዋም በጣም የገፋች ሴት
ነበረች ፤ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ከተቀመጠች
በኋላ ባልዋ ሞተባት ፤ 37 ከዚህም በኋላ ዕድ
ሜዋ ሰማኒያ አራት ዓመት እስኪሆን ድረስ
ከቤተ መቅደስ ሳትለይ በጾምና በጸሎት ቀንና
ሌሊት እግዚአብሔርን ታገለግል ነበር ። 38 በዚ
ያኑ ጊዜ እርስዋም መጥታ እግዚአብሔርን
ታመሰግን ጀመር ፤ ስለ ሕፃኑም የኢየሩሳሌምን
መዳን በተስፋ ለሚጠባበቁ ሁሉ ትናገር ነበር ።

## ወደ ናዝሬት መመለስ

39 በእግዚአብሔር ሕግ የታዘዘውን ሥርዓት
ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ በገሊላ ወደምትገኘው ወደ
መኖሪያ ከተማቸው ወደ ናዝሬት ተመለሱ ።
40 ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ ሄደ ፤ በጥበብም
የተሞላ ሆነ ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ ከእርሱ
ጋር ነበረ ።

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ

41 ዮሴፍና ማርያም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል
ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር ። 42 ኢየሱስ
ዐሥራ ሁለት ዓመት በሆነውም ጊዜ እንደተለ
መደው በዓሉን ለማክበር ሄዱ ። 43 በዓሉ ከተፈ
ጸመ በኋላ እነርሱ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ኢየ
ሱስ በኢየሩሳሌም ቀረ ፤ ዮሴፍና ማርያም ግን
እዚያ መቅረቱን አላወቁም ነበር ። 44 ከመንገደ
ኞች ጋር አብሮ የሚሄድ መስሎአቸው የአንድ
ቀን መንገድ ሲጓዙ ዋሉ ፤ ከዚያም በኋላ ከዘመ
ዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ዘንድ ይፈልጉት
ጀመር ። 45 ነገር ግን ሊያገኙት ስላልቻሉ እየፈ
ለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። 46 ከሦስት
ቀንም በኋላ በቤተ መቅደስ አገኙት ፤ በዚያም
በሊቃውንት መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸ
ውና ጥያቄም ሲያቀርብላቸው ነበር ። 47 የሰሙ
ትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ይገረሙ
ነበር ። 48 ዮሴፍና ማርያም በቤተ መቅደስ
ባዩት ጊዜ ተደነቁ ፤ በዚያን ጊዜ እናቱ “ልጄ
ምነው እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨ
ንቀን ስንፈልግህ ነበር እኮ!” አለችው ።

49 ኢየሱስም “ስለምን ፈለጋችሁኝ? እኔ በአ
ባቴ ቤት መሆን እንደሚገባኝ አታውቁም ኖሮ
አልን?” አላቸው ። 50 እነርሱ ግን እርሱ የተና
ገረውን አላስተዋሉም ።

51 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ወደ
ናዝሬት ሄደ ፤ ይታዘዛቸውም ነበር ፤ እናቱም
ይህን ሁሉ ነገር በልብዋ ትይዘው ነበር ።

52 ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወ
ደደ ሆኖ በጥበብና በቁመት እያደገ ይሄድ
ነበር ።

# ምዕራፍ 3

## የአጥማቂው ዮሐንስ ትምህርት

(ማቴ. 3፥1-12፤ ማር. 1፥1-8፤ ዮሐ. 1፥19-28)

1 የሮም ቄሳር ጢባርዮስ በነገሠ በዐሥራ
አምስተኛው ዓመት ፥ ጳንጤናዊው ጲላጦስ የይ
ሁዳ አገር አስተዳዳሪ ነበር ፤ ሄሮድስ የገሊላ
አገረ ገዥ ነበር ፤ እንዲሁም ወንድሙ ፊልጶስ
የኢጡርያስና የጥራኮኒዶስ ገዥ ፥ ሊሳኒዮስም
የአቢላኒስ ገዥ ነበሩ ፤ 2 ሐናና ቀያፋም የካህ
ናት አለቆች ነበሩ ፤ በዚህ ጊዜ የዘካርያስ ልጅ
ዮሐንስ በበረሓ ሳለ የእግዚአብሔር ቃል ወደ
እርሱ መጣ ። 3 ስለዚህ ዮሐንስ በዮርዳኖስ
ወንዝ ዙሪያ ባሉት አገሮች ሁሉ እየተዘዋወረ
“የኃጢአታችሁን ይቅርታ እንድታገኙ ንስሓ
ግቡታችሁ ተጠመቁ” እያለ ያስተምር ነበር ።
4 ይህም የሆነው ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ዮሐንስ
አስቀድሞ እንዲህ ሲል በጻፈው መሠረት ነው ፤

“እነሆ ይህ በበረሓ እንዲህ እያለ
የሚጮኽ ሰው ድምፅ ነው ፦
‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ ፤
ጥርጊያውንም አቅኑ ።
5 ጐድጓዳው ቦታ ሁሉ ይደልደል ፤
ተራራና ኰረብታውም ሁሉ ዝቅ
ይበል ፤
ጠማማው መንገድ ይቅና ፤
ሻካራውም መንገድ ይስተካከል ፤
6 ሰውም ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን
ይይ!’ ”

7 ሊጠመቁ ወደ እርሱ የመጡትን ሰዎች
ዮሐንስ እንዲህ ይላቸው ነበር ፥ “እናንተ የእፉ
ኝት ልጆች! ከሚመጣው ከእግዚአብሔር ቊጣ
ማምለጥ እንደምትችሉ ማን ነገራችሁ? 8 ይልቁ
ንስ ንስሓ መግባታችሁን የሚያመለክት ሥራ
ሥሩ እንጂ እኛ የአብርሃም ልጆች ነን እያላ
ችሁ በልባችሁ አትመኩ ። እግዚአብሔር ከእነ
ዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት
እንደሚችል እነግራችኋለሁ ። 9 አሁንስ ዛፎችን
ከሥራቸው ቈርጦ ለመጣል መጥረቢያ ተዘጋጅ
ቶአል ፤ ስለዚህ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ
ሁሉ ተቈርጦ ወደ እሳት ይጣላል ።”

10 ሕዝቡም “ታዲያ ምን እናድርግ?” ሲሉ
ዮሐንስን ጠየቁት ።

11 እርሱም “ሁለት ልብስ ያለው አንዱን
ለሌለው ይስጥ ፤ ምግብ ያለውም ለሌለው ያካ
ፍል” አላቸው ።

2፥39 ፦ ማቴ. 2፥23 ። 2፥41 ፦ ዘጸ. 12፥1-27 ፤ ዘዳ. 16፥1-8 ። 2፥52 ፦ 1ሳሙ. 2፥26 ፤ ምሳ. 3፥4 ።
3፥4-6 ፦ ኢሳ. 40፥3-5 ። 3፥7 ፦ ማቴ. 12፥34 ፤ 23፥33 ። 3፥8 ፦ ዮሐ. 8፥33 ። 3፥9 ፦ ማቴ. 7፥19 ።

12 ቀራጮችም ሊጠመቁ ወደ እርሱ መጥ
ተው "መምህር ሆይ! እኛስ ምን እናድርግ?"
ብለው ጠየቁት ።
13 እርሱም "በሕግ ከታዘዘው አብልጣችሁ
አትጠይቁ" አላቸው ።
14 ወታደሮችም መጥተው "እኛስ ምን እና
ድርግ" አሉት፤
እርሱም "የሰው ገንዘብ በግፍ ነጥቃችሁ
አትውሰዱ፤ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፤ የራሳ
ችሁ ደመወዝ ይብቃችሁ" አላቸው ።
15 በዚያን ዘመን ሕዝቡ ሁሉ የመሲሕን
መምጣት በተስፋ ይጠባበቅ ነበር፤ ስለዚህ ዮሐ
ንስን "ይህ ሰው ምናልባት መሲሕ ይሆንን?"
እያሉ በልባቸው አሰቡ ። 16 ዮሐንስ ግን እንዲህ
አላቸው፦ "እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር
ግን ሌላ ከእኔ የሚበልጥ ይመጣል፤ እኔ የእር
ሱን ጫማ ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የበቃሁ
አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት
ያጠምቃችኋል ። 17 እርሱ በእውድማ ላይ እህ
ሉን ከገለባ ለመለየት መንሹን በእጁ ይዞአል፤
ካጣራውም በኋላ ጥሩውን እህል በጐተራ ይከ
ታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለ
ዋል ።" 18 እንዲሁም ዮሐንስ በልዩ ልዩ መን
ገድ ሕዝቡን እየመከረ መልካሙን ዜና ያበሥር
ነበር ። 19 የገሊላውን ገዥ ሄሮድስን ግን የወን
ድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮዲያዳን በማግባ
ቱና ሌላም ብዙ ክፉ ነገር በማድረጉ ገሥጸው ።
20 ሄሮድስ ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎት በክፋት
ላይ ክፋት በመጨመር ዮሐንስን ወደ ወህኒ
ቤት አስገባው ።

### የኢየሱስ መጠመቅ
(ማቴ. 3፥13-17፤ ማር. 1፥9-11)

21 ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስም
ተጠመቀ፤ ሲጸልይ ሳለ ሰማይ ተከፈተ፤
22 መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ሆኖ በእ
ርሱ ላይ ወረደ፤ በዚያን ጊዜ "አንተ የተወደ
ድህ ልጄ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል" የሚል
ድምፅ ከሰማይ መጣ ።

### የኢየሱስ ትውልድ ሐረግ
(ማቴ. 1፥1-17)

23 ኢየሱስ የማስተማር ሥራውን ሲጀምር
ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር፤ ለሕ
ዝቡ ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው ነበር፤
ይኸውም ዮሴፍ የዔሊ ልጅ፥ 24 ዔሊ የማቲ
ልጅ፥ ማቲ የሌዊ ልጅ፥ ሌዊ የሚልኪ ልጅ፥
ሚልኪ የዮና ልጅ፥ ዮና የዮሴፍ ልጅ፥
25 ዮሴፍ የማታትዩ ልጅ፥ ማታትዩ የአሞጽ
ልጅ፥ አሞጽ የናሆም ልጅ፥ ናሆም የኤስሊም
ልጅ፥ ኤስሊም የናጌ ልጅ፥ 26 ናጌ የማአት
ልጅ፥ ማአት የማታትዩ ልጅ፥ ማታትዩ የሴ
ሜይ ልጅ፥ ሴሜይ የዮሴፍ ልጅ፥ ዮሴፍ የዮዳ
ልጅ፥ 27 ዮዳ፥ የዮናን ልጅ፥ ዮናን የሬስ
ልጅ፥ ሬስ የዘሩባቤል ልጅ፥ ዘሩባቤል የሰላት
ያል ልጅ፤ ሰላትያል የኔሪ ልጅ፤ 28 ኔሪ የሚ
ልኪ ልጅ፥ ሚልኪ የሐዲ ልጅ፥ ሐዲ የቆሳም
ልጅ፥ ቆሳም የኤልሞዳም ልጅ፥ ኤልሞዳም
የዔር ልጅ፥ 29 ዔር የዮሴዕ ልጅ፥ ዮሴዕ የኤሊ
ዔዘር ልጅ፥ ኤሊዔዘር የዮራም ልጅ፥ ዮራም
የማጣት ልጅ፥ ማጣት የሌዊ ልጅ፥ 30 ሌዊ
የስምዖን ልጅ፥ ስምዖን የይሁዳ ልጅ፥ ይሁዳ
የዮሴፍ ልጅ፥ ዮሴፍ የዮናን ልጅ፥ ዮናን የኤ
ልያቄም ልጅ፥ 31 ኤልያቄም የሜልያ ልጅ፥
ሜልያ የማይናን ልጅ፥ ማይናን የማጣት
ልጅ፥ ማጣት የናታን ልጅ፥ ናታን የዳዊት
ልጅ፥ 32 ዳዊት የእሴይ ልጅ፥ እሴይ የኢዮ
ቤድ ልጅ፥ ኢዮቤድ የቦዔዝ ልጅ፥ ቦዔዝ የሳ
ልሞን ልጅ፥ ሳልሞን የነአሶን ልጅ፥ 33 ነአሶን
የዓሚናዳብ ልጅ፥ ዓሚናዳብ የራም ልጅ፥
ራም የአርኒ ልጅ፥ አርኒ የሔጽሮን ልጅ፥
ሔጽሮን የፋሬስ ልጅ፥ ፋሬስ የይሁዳ ልጅ፥
ይሁዳ የያዕቆብ ልጅ፥ 34 ያዕቆብ የይስሐቅ
ልጅ፥ ይስሐቅ የአብርሃም ልጅ፥ አብርሃም
የታራ ልጅ፥ ታራ የናኮር ልጅ፥ 35 ናኮር የሰ
ሩግ ልጅ፥ ሰሩግ የረው ልጅ፥ ረው የፋሌግ
ልጅ፥ ፋሌግ የዔቤር ልጅ፥ ዔቤር የሼላሕ
ልጅ፥ 36 ሼላሕ የቃይንም ልጅ፥ ቃይንም የአ
ርፋክሳድ ልጅ፥ አርፋክሳድ የሴም ልጅ፥ ሴም
የኖኅ ልጅ፥ ኖኅ የላሜሕ ልጅ፥ 37 ላሜሕ የማ
ቱሳላ ልጅ፥ ማቱሳላ የሔኖክ ልጅ፥ ሔኖክ
የያሬድ ልጅ ያሬድ የመላልኤል ልጅ፥ መላል
ኤል የቃይናን ልጅ፥ 38 ቃይናን የሄኖስ ልጅ፥
ሄኖስ የሤት ልጅ፥ ሤት የአዳም ልጅ፥ አዳም
የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይሉ ነበር ።

## ምዕራፍ 4

### የኢየሱስ መፈተን
(ማቴ. 4፥1-11፤ ማር. 1፥12-13)

1 ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳ
ኖስ ወንዝ ተመለሰ፤ ከዚያም ወደ በረሓ እንዲ
ሄድ መንፈስ ቅዱስ አንሣሣው ። 2 እዚያም በበ
ረሓ አርባ ቀን በዲያብሎስ ተፈተነ፤ በእነዚ
ያም ቀኖች ምንም ስላልበላ በመጨረሻ
ራበው ።
3 ዲያብሎስም ኢየሱስን "የእግዚአብሔር
ልጅ ከሆንህ እስቲ ይህ ድንጋይ እንጀራ እንዲ
ሆን እዘዝ" አለው ።
4 ኢየሱስም "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም
ተብሎ ተጽፎአል" ሲል መለሰለት ።

3፥12 ፦ ሉቃ. 7፥29 ። 3፥19-20 ፦ ማቴ. 14፥3-4፤ ማር. 6፥17-18 ። 3፥22 ፦ ዘፍ. 22፥2፤ መዝ. 2፥7፤ ኢሳ. 42፥1፤
ማቴ. 3፥17፤ ማር. 1፥11፤ ሉቃ. 9፥35 ። 4፥4 ፦ ዘዳ. 8፥3 ።



5 ከዚህም በኋላ ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ
አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ አውጥቶ የዓለምን መን
ግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየውና እንዲህ
አለው፦ 6 "ይህን ሁሉ ሥልጣንና ክብር ለአ
ንተ እሰጥሃለሁ፤ ይህ ሁሉ ለእኔ የተሰጠኝ ስለ
ሆነ ለፈለግሁት መስጠት እችላለሁ፤ 7 ስለዚህ
አንተ ለእኔ ብትሰግድልኝ ይህ ሁሉ የአንተ
ይሆናል ።"
8 ኢየሱስም "'ለእግዚአብሔር ለአምላክህ
ብቻ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አገልግል ተብሎ
ተጽፎአል" ሲል መለሰለት ።
9 ከዚያም በኋላ ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ
ኢየሩሳሌም ወሰደው፤ በቤተ መቅደሱም ጣራ
ጫፍ ላይ እንዲቆም አድርጎ እንዲህ አለው፦
"አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ
ከዚህ ወደታች ዘልለህ ውረድ፤ 10 ምክንያቱም
'አንተን እንዲጠብቁህ እግዚአብሔር መላእክ
ቱን ያዝዛል፤ 11 እግርህም በድንጋይ እንዳይሰና
ከል በእጃቸው ደግፈው ይይዙሃል' ተብሎ ተጽ
ፎአልና" አለው ።
12 ኢየሱስም "'እግዚአብሔር አምላክህን
አትፈታተነው' ተብሎ ተጽፎአል" ሲል መለሰ
ለት ።
13 ዲያብሎስ ኢየሱስን በብዙ መንገድ ከፈተ
ነው በኋላ ለጊዜው ትቶት ሄደ ።

### ኢየሱስ የማስተማር ሥራውን በገሊላ ጀመረ
(ማቴ. 4፥12-17፤ ማር. 1፥14-15)

14 ኢየሱስም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተሞ
ልቶ ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ዝናውም በአገሩ
ሁሉ ተሰማ ። 15 በምኲራቦቻቸውም ያስተምር
ነበር፤ ሁሉም በትምህርቱ አመሰገኑት ።

### ኢየሱስ በናዝሬት ተቃውሞ ደረሰበት
(ማቴ. 13፥53-58፤ ማር. 6፥1-6)

16 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ወደ አደገበት
አገር ወደ ናዝሬት ሄደ፤ እንደ ልማዱም በሰን
በት ቀን ወደ ምኲራብ ገባ፤ ሊያነብም ተነሣ፤
17 የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ተሰጠው፤ መጽ
ሐፉንም በገለጠ ጊዜ እንዲህ ተብሎ የተጻፈበ
ትን ቦታ አገኘ፦
18 "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ
ነው፤
መልካም ዜናን ለድኾች እንዳበሥር
ሾሞኛል፤
ለታሠሩት መፈታትን፥
ለታወሩት ማየትን እንዳውጅና
የተጨቈኑትንም ነፃ እንዳወጣ
ልኮኛል፤
19 እንዲሁም እግዚአብሔር ሕዝቡን
የሚያድንበትን
የጸጋ ዓመት እንዳስታውቅ ልኮኛል ።"
20 ኢየሱስ መጽሐፉን አጥፎ ለአስተናባሪው
ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኲራቡ የነበሩትም ሁሉ
ትኲር ብለው ወደ እርሱ ይመለከቱ ጀመር፤
21 እርሱም "እነሆ ይህ አሁን ሲነበብ የሰማች
ሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ" አላቸው ።
22 ስለ እርሱ ሁሉም መልካም ይናገሩ
ነበር፤ በሚናገረውም ውብ ቃል ተደንቀው
"ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን?" አሉ ።
23 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ "'አንተ
ሐኪም፥ እስቲ ራስህን አድን' የሚለውን
ምሳሌ እንደምትጠቅሱብኝ እርግጠኛ ነኝ፤ እን
ዲሁም 'በቅፍርናሆም አድርገሃል ሲሉ የሰማነ
ውን ሁሉ እዚህም በገዛ አገርህ አድርግ' ትሉኛ
ላችሁ ። 24 በእውነት እላችኋለሁ፥ ነቢይ በገዛ
አገሩ ሰዎች ዘንድ አይከበርም ።
25 "ስሙኝ እውነቱን ልንገራችሁ፤ በነቢዩ
በኤልያስ ዘመን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር
ዝናም ባለመዝነሙ በአገሩ ሁሉ ብርቱ ረሀብ
ሆኖ ነበር፤ በዚያን ጊዜ በእስራኤል አገር ብዙ
መበለቶች ነበሩ ። 26 ነገር ግን ኤልያስ በሲዶና
አገር ሰራጵታ በምትባል መንደር ወደምትገ
ኘው ወደ አንዲት መበለት ብቻ ተላከ እንጂ
ወደ ሌላ ወደ ማንም አልተላከም ። 27 እንዲ
ሁም በነቢዩ በኤልሳዕ ጊዜ ብዙ ለምጻሞች በእ
ስራኤል አገር ነበሩ፤ ነገር ግን ከሶርያዊው ከን
ዕማን በቀር ከእነርሱ አንድ እንኳ አልዳነም ።"
28 በምኲራብ የነበሩትም ሁሉ ይህን በሰሙ
ጊዜ እጅግ ተቈጡ ። 29 ተነሥተውም ኢየሱስን
ጐትተው ከከተማ ውጭ አወጡት፤ ወደ ገደ
ልም ገፍትረው ሊጥሉት ፈልገው ከተማቸው
ወደ ተሠራችበት ኰረብታ አፋፍ ላይ ወሰ
ዱት ። 30 እርሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ ።

### ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው
(ማር. 1፥21-28)

31 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በገሊላ ክፍለ ሀገር
ወደምትገኘው ከተማ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ፤
በዚያም ሕዝቡን በሰንበት ቀን ያስተምር
ነበር ። 32 በሥልጣን ቃል ይናገር ስለነበር
ሁሉም በትምህርቱ ይደነቁ ነበር ። 33 እዚያም
በምኲራብ ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበር፤
እርሱ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ ጮኸ፦
34 "የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! እኛ ከአንተ ጋር
ምን ግንኙነት አለን? ልታጠፋን መጣህን?
አንተ ማን እንደሆንህ እኔ ዐውቃለሁ፤ አንተ
እኮ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!"

4፥8 ፦ ዘዳ. 6፥13 ። 4፥10 ፦ መዝ. 91፥11 ። 4፥11 ፦ መዝ. 91፥12 ። 4፥12 ፦ ዘዳ. 6፥16 ።
4፥18-19 ፦ ኢሳ. 61፥1-2 ። 4፥24 ፦ ዮሐ. 4፥44 ። 4፥25 ፦ 1ነገ. 17፥1 ። 4፥26 ፦ 1ነገ. 17፥8-16 ።
4፥27 ፦ 2ነገ. 5፥1-14 ። 4፥32 ፦ ማቴ. 7፥28-29 ።

35 ኢየሱስም ርኵሱን መንፈስ "ዝም ብለህ
ከእርሱ ውጣ!" ሲል ገሠጸው ፤ ርኵሱ መንፈስ
ሰውየውን በሕዝቡ ፊት ጣለውና ምንም ሳይጐ
ዳው ወጣ ።
36 ሁሉም በመደነቅ እርስ በርሳቸው "ይህ
ምን ዐይነት ነገር ነው? በሥልጣንና በኀይል
ርኵሳን መናፍስትን ያዝዛል ፤ እነርሱም ታዝ
ዘው ይወጣሉ" ተባባሉ ። 37 የኢየሱስም ዝና
በዚያ አገር ዙሪያ ሁሉ ተሰማ ።

ኢየሱስ ብዙ ሕመምተኞችን ፈወሰ
(ማቴ. 8፥14-17፤ ማር. 1፥29-34)

38 ኢየሱስ ከምኵራብ ተነሥቶ ወደ ስምዖን
ቤት ሄደ ፤ እዚያም የስምዖን ዐማት በጣም አተ
ኩሶአት ታማ ተኝታ ነበር ፤ ስለዚህ እንዲያድ
ናት ኢየሱስን ለመኑት ። 39 ኢየሱስም ወደ እር
ስዋ ቀርቦ አጠገብዋ ቆመና ትኩሳቱ እንዲለቅ
ቃት አዘዘ ፤ ትኩሳቱም ለቀቃት ፤ ወዲያውኑም
ተነሥታ ታስተናግዳቸው ጀመር ።
40 ፀሐይ ስትጠልቅ ሰዎች በልዩ ልዩ ደዌ
የተያዙባቸውን ሕመምተኞች ሁሉ ወደ ኢየ
ሱስ አመጡ ፤ እርሱም በእያንዳንዳቸው ላይ
እጁን በመጫን ፈወሳቸው ። 41 አጋንንትም
"አንተ እኮ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!" እያሉ
በመጮኸ ብዙ ሰዎችን እየለቀቁ ይወጡ ነበር ፤
እርሱ መሲሕ መሆኑንም ዐውቀው ነበር ፤
ኢየሱስ ግን ስለ እርሱ ምንም እንዳይናገሩ
በመገሠጽ ይከለክላቸው ነበር ።

ኢየሱስ በገሊላ ማስተማሩን ቀጠለ
(ማቴ. 4፥23-25፤ ማር. 1፥35-39)

42 በነጋም ጊዜ ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ሰው
ወደሌለበት ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ ሄደ ፤
ሰዎቹም ይፈልጉት ነበር ፤ ባገኙትም ጊዜ
"ተለይተኸን አትሂድብን" ብለው ለመኑት ።
43 እርሱ ግን "እኔ የተላክሁት ለዚህ ስለሆነ
ወደ ሌሎችም ከተሞች ሄጄ የእግዚአብሔርን
መንግሥት የምሥራች ቃል ማብሠር ይገባ
ኛል" አላቸው ።
44 ስለዚህ በይሁዳም በምኵራቦች ሁሉ እየ
ተዘዋወረ ያስተምር ነበር ።

## ምዕራፍ 5

### ኢየሱስ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት ጠራ
(ማቴ. 4፥18-22፤ ማር. 1፥16-20)

1 አንድ ቀን ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ባሕር ዳር
ቆሞ ሳለ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ቀርበው የእግ
ዚአብሔርን ቃል ለመስማት ይጋፉ ነበር ።
2 እርሱ በባሕሩ ዳር ተጠግተው የቆሙትን
ሁለት ጀልባዎች አየ ፤ ዓሣ አጥማጆቹ ግን ከጀ
ልባዎቹ ወርደው መረቦቻቸውን ያጥቡ ነበር ።
3 ኢየሱስ ከጀልባዎቹ ወደ አንዲቱ ፥ የስምዖን
ወደሆነችው ገባ ። ስምዖንንም "ይህችን ጀልባ
ከምድር ወደ ባሕሩ እስቲ ጥቂት ፈቀቅ አድር
ግልኝ" አለው ። ከዚህም በኋላ በጀልባዋ ላይ
ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ጀመር ።
4 ንግግሩንም ከጨረሰ በኋላ ስምዖንን "ጀል
ባዋን ወደ ጥልቁ ባሕር ራቅ አድርገህ አንተና
ጓደኞችህ ዓሣ ለማጥመድ መረባችሁን ጣሉ"
አለው ።
5 ስምዖንም "መምህር ሆይ! ሌሊቱን ሙሉ
ስንደክም አድረን ምንም አልያዝንም ፤ አንተ
ካልህ ግን እነሆ መረቡን እንጥላለን" አለው ።
6 መረቡን በጣሉ ጊዜ መረቡ እስኪቀደድ ድረስ
እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ ። 7 ስለዚህ በሌላይቱ
ጀልባ ላይ የነበሩት ጓደኞቻቸው መጥተው እን
ዲያግዙዋቸው በጥቅሻ ጠሩዋቸው ፤ እነርሱም
መጥተው ሁለቱ ጀልባዎች ሊሰምጡ ጥቂት
እስኪቀራቸው ድረስ በዓሣ ሞሉአቸው ። 8 ስም
ዖን ጴጥሮስ ይህንን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ፊት ተን
በርክኮ "ጌታ ሆይ! እኔ ኃጢአተኛ ስለሆንሁ
ወደ እኔ አትቅረብ" አለው ።
9 ይህንንም ያለበት ምክንያት እርሱና አብረ
ውት የነበሩት ጓደኞቹ ሁሉ ከያዙት ዓሣ
ብዛት የተነሣ እጅግ ተገርመው ስለነበር ነው ።
10 እንዲሁም የስምዖን ጓደኞች የሆኑት የዘብዴ
ዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተገርመው
ነበር ። ኢየሱስ ስምዖንን "አይዞህ አትፍራ ፤
ከእንግዲህ ወዲህ ሰዎችን የምታጠምድ ትሆና
ለህ" አለው ።
11 እነርሱም ጀልባዎቹን ወደ ምድር ካስ
ጠጉ በኋላ ሁሉን ነገር ትተው የኢየሱስ ተከታ
ዮች ሆኑ ።

### ኢየሱስ ለምጻሙን[1*] ሰው አነጻ
(ማቴ. 8፥1-4፤ ማር. 1፥40-45)

12 አንድ ቀን ኢየሱስ በአንዲት ከተማ
ውስጥ ሳለ ገላውን ለምጽ የወረሰው አንድ ሰው
ወደ እርሱ መጣ ፤ ኢየሱስን ባየው ጊዜ በግን
ባሩ ተደፍቶ "ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላ
ለህ" ሲል ለመነው ።
13 ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና "ፈቅ
ጃለሁ ንጻ" አለው ። ወዲያውኑ ከለምጹ ነጻ ።
14 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ ሲል አዘዘው ፥
"ይህን ነገር ለማንም አትናገር ፤ ነገር ግን በቀ
ጥታ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ፤ ለሕዝብ

[1*] 5፥12 ለምጽ ፡- እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ ቃሉ በሰውነት ላይ የሚታዩን ልዩ ልዩ ዐይነት ተላላፊ የቆዳ በሽታ ሁሉ ያመለክታል
(ዘሌ. 13 ተመልከት) ።
5፥1 3 ፡- ማቴ. 13፥1-2፤ ማር. 3፥9-10፤ 4፥1 ። 5፥5 ፡- ዮሐ. 21፥3 ። 5፥6 ፡- ዮሐ. 21፥6 ። 5፥14 ፡- ዘሌ. 14፥1-32 ።



ምስክር እንዲሆን ስለ መንጻትህ ሙሴ ያዘዘ
ውን መሥዋዕት አቅርብ ።"
15 የኢየሱስ ዝና ግን ከምንጊዜውም ይበልጥ
ተሰማ ፤ ብዙ ሰዎችም እርሱን ለመስማትና ከበ
ሽታቸውም ለመዳን ፈልገው ይሰበሰቡ ነበር ።
16 እርሱ ግን በየጊዜው ብቻውን ወደ በረሓ እየ
ሄደ ይጸልይ ነበር ።

### ኢየሱስ ሽባውን ሰው ፈወሰ
(ማቴ. 9፥1-8፤ ማር. 2፥1-12)

17 አንድ ቀን ኢየሱስ ሲያስተምር ሳለ ፈሪሳ
ውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን በአጠገቡ ተቀ
ምጠው ነበር ፤ እነርሱ ከገሊላና ከይሁዳ መንደ
ሮች ሁሉ እንዲሁም ከኢየሩሳሌም ከተማ
የመጡ ነበሩ ። ኢየሱስ በሽተኞችን የሚፈውስ
በት የእግዚአብሔር ኀይል ነበረው ። 18 እነሆ
አንድ ሽባ ሰው በአልጋ የተሸከሙ ሰዎች ወደ
ኢየሱስ መጡ ፤ ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቤት አግ
ብተው በፊቱ ሊያኖሩት ፈልገው ነበር ፤
19 ነገር ግን ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሽባውን
ወደ ቤት ማግባት አቃታቸው ፤ ስለዚህ ወደ
ጣራ ላይ ይዘውት ወጡ ፤ ጣራውንም ሸንቁረው
ሽባውን ከነአልጋው በኢየሱስ ፊት አወረዱት ።
20 ኢየሱስ እምነታቸውን ባየ ጊዜ ሽባውን
"አንተ ሰው! ኃጢአትህ ተደምስሶልሃል"
አለው ።
21 የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን
"በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል የሚናገር
ይህ ማንነው? ኃጢአትን የሚደመስስ እግዚአብ
ሔር ብቻ ነው እንጂ ሌላ ማነው?" እያሉ
ያስቡ ነበር ።
22 ኢየሱስም አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው ፥ "በልባችሁ ስለምን ይህን ታስባላችሁ?
23 ለመሆኑ 'ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል' ከማ
ለትና 'ተነሥተህ ሂድ' ከማለት የትኛው ይቀል
ላል? 24 ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ
ኃጢአትን ለመደምሰስ ሥልጣን እንዳለው
ማወቅ አለባችሁ" ብሎ ሽባውን ሰው "አንተ
ሰው ተነሥ ፤ አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ
ሂድ" አለው ።
25 ሽባውም በሰዎቹ ፊት ተነሣና አልጋውን
ተሸክሞ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ
ሄደ ። 26 በዚያም የነበሩ ሰዎች ሁሉ እጅግ ተገ
ርመው በመፍራት "ዛሬ ድንቅ ነገር አየን"
እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ ።

### ኢየሱስ ማቴዎስ የተባለውን ሌዊን ጠራ
(ማቴ. 9፥9-13፤ ማር. 2፥13-17)

27 ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ሲሄድ ሌዊ የተባለ
ውን ቀራጭ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ
አየውና "ተከተለኝ" አለው ። 28 ሌዊም ብድግ
አለና ሁሉን ነገር ትቶ ተከተለው ።
29 ከዚህም በኋላ ሌዊ በቤቱ ለኢየሱስ ክብር
ትልቅ ግብዣ አደረገ ፤ በግብዣውም ላይ ብዙ
ቀራጮችና ሌሎችም ብዙ ሰዎች ተገኝተው
ነበር ። 30 ፈሪሳውያንና ወገኖቻቸው የሆኑ
የሙሴ ሕግ መምህራን "ከቀራጮችና ከኃጢአ
ተኞች ጋር የምትበሉትና የምትጠጡት ስለምን
ድን ነው?" ብለው በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት
ላይ አጕረመረሙ ።
31 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋ
ቸውም ፤ 32 እኔ የመጣሁት ኃጢአተኞችን ወደ
ንስሓ ለመጥራት ነው እንጂ ጻድቃንን ወደ
ንስሓ ለመጥራት አይደለም ።"

### ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 9፥14-17፤ ማር. 2፥18-22)

33 ከዚህም በኋላ ኢየሱስን "የዮሐንስና የፈሪ
ሳውያን ደቀ መዛሙርት ጾምና ጸሎት ያዘወት
ራሉ ፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ሁል ጊዜ
የሚበሉትና የሚጠጡት ለምንድን ነው?" በማ
ለት ጠየቁት ።
34 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች
መጾም ይገባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁን?
35 ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይበት
ጊዜ ይመጣል ፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ ።"
36 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ ሲል አንድ
ምሳሌ ነገራቸው ፥ "ከአዲስ ልብስ ላይ ዕራፊ
ቀድዶ በአሮጌ ልብስ ላይ የሚጥፍ ማንም
የለም ፤ ይህን የሚያደርግ ቢኖር ግን አዲሱን
ልብስ በከንቱ ይቀድደዋል ፤ አዲሱም ዕራፊ ለአ
ሮጌው ልብስ አይስማማም ፤ 37 እንዲሁም በአ
ረጀ የወይን ጠጅ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ
የሚያኖር ማንም የለም ፤ ይህን የሚያደርግ
ቢኖር ግን አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈ
ነዳዋል ፤ የወይን ጠጁም ይፈስሳል ፤ አቁማዳ
ውም ከጥቅም ውጪ ይሆናል ። 38 ስለዚህ አዲ
ሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገ
ባል ፤ 39 ብዙ ጊዜ የቆየ ደረቅ የወይን ጠጅ
የጠጣ አዲሱን በተሐ የወይን ጠጅ መጠጣት
አይፈልግም ፤ ምክንያቱም 'የቆየው ደረቅ የወ
ይን ጠጅ የተሻለ ነው' ይላል ።"

## ምዕራፍ 6

### ስለሰንበት የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 12፥1-8፤ ማር. 2፥23-28)

1 በሰንበት ቀን ኢየሱስ በእርሻ መካከል ሲያ
ልፍ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ የስንዴ እሸት እየቀ
ጠፉ በእጃቸው ማሸትና መብላት ጀመሩ ፤

5፥30 ፡- ሉቃ. 15፥1-2 ። 6፥1 ፡- ዘዳ. 23፥25 ።

2 ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርቱን
“በሰንበት ቀን ሊደረግ የማይገባውን ነገር ስለ
ምን ታደርጋላችሁ?” አሉአቸው ።
3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እርሱና አብረውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ
ጊዜ ዳዊት ያደረገውን አላነበባችሁምን?
4 እርሱ ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ ከካህናት
በቀር ለሌሎች መብላት ያልተፈቀደውን የተቀ
ደሰ የመባ ኅብስት አንሥቶ በላ ፤ ከእርሱ ጋር
ለነበሩትም ሰዎች ሰጣቸው ።”
5 ቀጥሎም ኢየሱስ “የሰው ልጅ ለሰንበትም
ጌታዋ ነው” አላቸው ።

## ኢየሱስ እጀ ሽባውን አዳነ
(ማቴ. 12፥9-14፤ ማር. 3፥1-6)

6 በሌላም ሰንበት ቀን ኢየሱስ ወደ ምኩራብ
ገብቶ ያስተምር ነበር ፤ እዚያም ቀኝ እጁ ሽባ
የሆነ አንድ ሰው ነበር ። 7 የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያንም ኢየሱስን የሚከሱበት ወን
ጀል ለማግኘት ፈልገው “እስቲ በሰንበት ቀን
ይፈውሰው እንደሆነ እንይ” ብለው ይጠባበቁት
ነበር ። 8 ኢየሱስ ግን አሳባቸውን ዐውቆ እጀ
ሽባውን “ተነሥና በመካከል ቁም!” አለው ፤
ሽባውም ተነሣና በመካከል ቆመ ። 9 በዚህ ጊዜ
ኢየሱስ “እስቲ ልጠይቃችሁ ፥ ለመሆኑ በሰን
በት ቀን የተፈቀደው መልካም ማድረግ ነውን?
ወይስ ክፉ ፥ ነፍስን ማዳን ነውን ወይስ ማጥ
ፋት?” አላቸው ። 10 ኢየሱስ በዙሪያው ወዳ
ሉት ሰዎች ሁሉ ከተመለከተ በኋላ እጀ ሽባ
ውን “እጅህን ዘርጋ” አለው ። እርሱም እጁን
በዘረጋው ጊዜ ዳነለትና እንደ ሌላው እጅ ደህና
ሆነ ።
11 የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ግን
በጣም ተቈጥተው “እንግዲህ ኢየሱስን ምን
ማድረግ ይቻለናል?” በማለት እርስ በርሳቸው
ተነጋገሩ ።

## ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ
(ማቴ. 10፥1-4፤ ማር. 3፥13-19)

12 ከዚህ በኋላ አንድ ቀን ኢየሱስ ለመጸለይ
ወደ ተራራ ወጣ ፤ እዚያ ሌሊቱን ሙሉ ወደ
እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ ። 13 በነጋም ጊዜ
ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠራ ፤ ከእነርሱም
መካከል ዐሥራ ሁለቱን መርጦ “ሐዋርያት”
ብሎ ሰየማቸው ፤ 14 እነርሱም ቀጥለው የሚገ
ኙት ናቸው ፦ ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው ስምዖ
ንና ወንድሙ እንድርያስ ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ፥
ፊልጶስና በርተሎሜዎስ ፥ 15 ማቴዎስና ቶማስ ፥
የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና “ተቀናቃኝ” ተብሎ
የሚጠራው ስምዖን ፥ 16 የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ፥
ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው አስቆሮታዊው
ይሁዳ ።

## ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን አስተማረ ፥ ፈወሰም
(ማቴ. 4፥23-25)

17 ኢየሱስ ከሐዋርያቱ ጋር ከተራራው
ወርዶ በሜዳ ላይ ቆመ ፤ ከደቀ መዛሙርቱም
ብዙዎቹ በዚያ ነበሩ ፤ እንዲሁም ሊሰሙትና
ከበሽታቸው ሊፈወሱ ፈልገው የመጡ እጅግ
ብዙ ሰዎች ነበሩ ። እነርሱም የመጡት ከይሁዳ
ክፍለ ሀገር ፥ ከኢየሩሳሌም ከተማ ፥ በባሕር
አጠገብ ከሚገኙት ከጢሮስና ከሲዶና ከተማ
ዎች ነበር ። 18 በርኩሳን መናፍስት የተያዙ
ሰዎችም መጥተው ይፈወሱ ነበር ። 19 የማዳን
ኀይል ከእርሱ እየወጣ ሁሉንም ይፈውስ ስለ ነ
በር ፥ ሰዎቹ ሁሉ ኢየሱስን ለመንካት ይፈልጉ
ነበር ።

## የደስታና የሐዘን ምክንያቶች
(ማቴ. 5፥1-12)

20 ኢየሱስ መለስ ብሎ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
እየተመለከተ እንዲህ አላቸው ፥
“የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ
ናትና
እናንተ ድኾች ደስ ይበላችሁ!
21 እናንተ አሁን የምትራቡ
በኋላ ትጠግባላችሁና ደስ ይበላችሁ!
እናንተ አሁን የምታለቅሱ
በኋላ ትስቃላችሁና ደስ ይበላችሁ!
22 “የእኔ ተከታዮች በመሆናችሁ ምክንያት
ሰዎች ሲጠሉዋችሁና አንቀበላችሁም ብለው
ሲለዩአችሁ ፥ ሲደበድቡዋችሁና ስማችሁን ሲያ
ጠፉ ደስ ይበላችሁ! 23 በመንግሥተ ሰማይ ዋጋ
ችሁ ትልቅ ነውና ይህ ሁሉ ሲደርስባችሁ ደስ
ይበላችሁ ፤ በደስታም ፈንድቁ ፤ አባቶቻቸውም
በነቢያት ላይ እንዲህ ያለውን ክፉት አድርገው
ባቸው ነበር ።
24 “እናንተ ሀብታሞች ግን የፈለጋችሁትን
ሁሉ አሁን አግኝታችኋልና
ወዮላችሁ!
25 “እናንተ አሁን የጠገባችሁ
ኋላ ትራባላችሁና ወዮላችሁ!
እናንተ አሁን የምትስቁ
ኋላ ስለምታዝኑና ስለምታለቅሱ
ወዮላችሁ!
26 “ሰዎች ሁሉ ሲያመሰግኑአችሁና ስለ እና
ንተ መልካም ሲናገሩ ወዮላችሁ! አባቶቻቸ
ውም ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ አድርገው
ነበር ።

6፥3-4 ፦ 1ሳሙ. 21፥1-6 ። 6፥4 ፦ ዘሌ. 24፥9 ። 6፥22 ፦ 1ጴጥ. 4፥14 ። 6፥23 ፦ 2ዜ.መ. 36፥16 ፤ ሐ.ሥ. 7፥52 ።



## ጠላትን መውደድ
(ማቴ. 5፥38-48፤ ማቴ. 7፥12)

27 “ለእናንተ ለምትሰሙኝ ግን እንዲህ
እላችኋለሁ ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ ለሚጠሉ
አችሁም መልካም ነገር አድርጉ ፤ 28 የሚረግ
ሙአችሁን መርቁ ፤ ለሚበድሉአችሁም ጸልዩላ
ቸው ፤ 29 አንዱን ጕንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ፥
ሌላውንም ጕንጭህን እንዲመታ አዙርለት ፤
ነጠላህን ለሚወስድብህ እጀ ጠባብህንም ጨም
ረህ ስጠው ፤ 30 ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ ፤ ገንዘብ
ህን የሚወስድብህን ሰው ፥ እንዲመልስ አትጠይ
ቀው ። 31 ሰዎች ለእናንተ ሊያደርጉላችሁ የም
ትፈልጉትን እናንተም እንዲሁ ለእነርሱ አድር
ጉላቸው ።
32 “የሚወድዱአችሁን ብትወድዱ ምን
ብልጫ ታገኛላችሁ ፤ ኀጢአተኞችም እኮ የሚ
ወድዱአቸውን ይወድዳሉ! 33 መልካም ነገር
ለሚያደርጉላችሁ እናንተም መልካም ነገር
ብታደርጉላቸው ምን ብልጫ ታገኛላችሁ?
ኀጢአተኞችም እኮ እንዲሁ ያደርጋሉ!
34 ‘ይመልሱልናል’ ብላችሁ ለምታበድሩአቸው
ሰዎች ብታበድሩ ምን ብልጫ ታገኛላችሁ?
ያንኑ ያበደሩትን መልሰው ለመቀበልማ ኀጢአ
ተኞችም ለኀጢአተኞች ያበድራሉ ። 35 እናንተ
ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ መልካም ነገርም
አድርጉላቸው ፤ ‘ብድራችን ይመልሱልናል’ ብላ
ችሁ ተስፋ ሳታደርጉ አበድሩ ፤ ይህን ብታደ
ርጉ ዋጋችሁ ትልቅ ይሆናል ፤ የልዑል እግዚአ
ብሔር ልጆችም ትሆናላችሁ ፤ እርሱ ለውለታ
ቢሶችና ለክፉዎች እንኳ ሳይቀር ቸር ነው ።
36 የሰማይ አባታችሁ መሐሪ እንደሆነ እናንተም
እንዲሁ መሐሪዎች ሁኑ ።

## በሌሎች ላይ መፍረድ አይገባም
(ማቴ. 7፥1-5)

37 “በማንም ላይ አትፍረዱ ፤ በእናንተም
ላይ አይፈረድባችሁም ፤ ሌሎችን አትንቀፉ ፤
እናንተም አትነቀፉም ፤ ይቅር በሉ ፤ እናንተም
ይቅርታ ታገኛላችሁ ፤ 38 ስጡ ፤ ለእናንተም
ይሰጣችኋል ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ እን
ዲሁ ይሰፈርላችኋል ፤ እንዲያውም በጥሩ መስ
ፈሪያ ታምቆና ተጠቅጥቆ እስኪትረፈረፍ ድረስ
ተሰፍሮ ይሰጣችኋል ።”
39 ቀጥሎም ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ነገራ
ቸው ፥ “ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን? እን
ዲህማ ቢያደርግ ሁለቱም ተያይዘው በጕድጓድ
ውስጥ ይወድቃሉ ። 40 ተማሪ ከአስተማሪው
አይበልጥም ፤ ይሁን እንጂ ተማሪ ትምህርቱን
በደንብ ከተማረ እንደ አስተማሪው ይሆናል ።
41 “በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ ሳታይ ፥
ስለምን በሰው ዐይን ያለውን ጉድፍ ትመለከታ
ለህ? 42 ደግሞስ በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ
ሳታይ ሌላውን ሰው ‘ወንድሜ ሆይ! እስቲ በዐ
ይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ’ ማለት እን
ዴት ትችላለህ? አንተ ግብዝ አስቀድመህ በአ
ንተ ዐይን ያለውን ግንድ አውጣ ፤ ከዚህ በኋላ
በሌላው ሰው ዐይን ያለውን ጉድፍ ለማውጣት
አጥርተህ ማየት ትችላለህ ።

## ዛፍ በፍሬው ይታወቃል
(ማቴ. 7፥16-20፤ 12፥33-35)

43 “ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ አያፈራም ፤ እንዲ
ሁም መጥፎ ዛፍ ጥሩ ፍሬ አያፈራም ። 44 ዛፍ
ሁሉ በፍሬው ይታወቃል ፤ ከእሾኽ ቍጥቋጦ
የበለስ ፍሬ አይለቀምም ፤ እንዲሁም ከቀጋ የወ
ይን ፍሬ አይለቀምም ። 45 ስለዚህ ደግ ሰው
ከመልካም ልቡ መልካምን ነገር ያወጣል ፤
ክፉ ሰውም ከመጥፎ ልቡ ክፉውን ነገር ያወ
ጣል ። ሰው በአፉ የሚናገረው ከልቡ ሞልቶ
የተረፈውን ነው ።

## ሁለት ዐይነት ቤት ሠሪዎች
(ማቴ. 7፥24-27)

46 “እኔ የምነግራችሁን አትፈጽሙም ፤
ታዲያ ስለምን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! እያላችሁ
ትጠሩኛላችሁ? 47 ወደ እኔ የሚመጣና ቃሌ
ንም ሰምቶ የሚፈጽም ማንን እንደሚመስል
ልንገራችሁ ፤ 48 እርሱ በጥልቅ ቈፍሮ ቤቱን
በጽኑ አለት ላይ የመሠረተውን ሰው ይመስ
ላል ፤ ጐርፍ መጥቶ ያንን ቤት ገፋው ፤ ነገር
ግን በጽኑ መሠረት ላይ ስለ ተሠራ ሊያነቃን
ቀው አልቻለም ። 49 ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም
ግን ያለ መሠረት በአሸዋማ መሬት ላይ ቤቱን
የሠራ ሰውን ይመስላል ፤ ጐርፍ መጥቶ ያንን
ቤት በገፋው ጊዜ ወዲያውኑ ወደቀ ፤ አወዳደ
ቁም እጅግ ታላቅ ሆነ ።”

# ምዕራፍ 7

## ኢየሱስ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ፈወሰ
(ማቴ. 8፥5-13)

1 ኢየሱስ ይህን ሁሉ ለሕዝቡ ተናግሮ ከጨ
ረሰ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ ። 2 በዚያም
አንድ ሮማዊ የመቶ አለቃ ነበረ ። እርሱም የሚ
ወድደው አገልጋይ በጠና ታምሞ ለሞት ተቃ
ርቦ ነበር ። 3 የመቶ አለቃው ስለ ኢየሱስ በሰማ
ጊዜ የአይሁድ ሽማግሌዎችን “እባካችሁ ኢየ
ሱስ መጥቶ አገልጋዬን እንዲፈውስልኝ ሄዳችሁ

6፥31 ፦ ማቴ. 7፥12 ። 6፥39 ፦ ማቴ. 15፥14 ። 6፥40 ፦ ማቴ. 10፥24-25 ፤ ዮሐ. 13፥16 ፤ 15፥20 ።
6፥44 ፦ ማቴ. 12፥33 ። 6፥45 ፦ ማቴ. 12፥34 ።

ለምኑልኝ” ሲል ላካቸው ። 4 እነርሱም ወደ
ኢየሱስ ሄደው “ይህን እንድታደርግለት የሚገ
ባው ሰው ነው ፤ 5 እርሱ ሕዝባችንን ይወድ
ዳል ፤ ምኩራብም ሠርቶልናል” ሲሉ አጥብ
ቀው ለመኑት ።
6 ስለዚህ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር አብሮ ሄደ ፤
ወደ ቤቱም በቀረበ ጊዜ የመቶ አለቃው ወዳጆ
ቹን እንዲህ ሲል ወደ ኢየሱስ ላከ ፡ “ጌታ ሆይ
አንተ ወደ ቤቴ ትገባ ዘንድ ያልተገባሁ ነኝና
ወደ እኔ ለመምጣት አትድከም ። 7 እኔም ራሴ
ወደ አንተ ለመምጣት የበቃሁ ሰው አይደለ
ሁም ። ስለዚህ አንተ እዚያው ሆነህ በቃልህ
ብታዝዝ አገልጋዬ ይድናል ። 8 እኔ ራሴ ለባለ
ሥልጣኖች ታዛዥ ስሆን ከእኔ በታች የማዝዛ
ቸው ወታደሮች አሉኝ ። ስለዚህ አንዱን ‘ሂድ’
ስለው ይሄዳል ፤ ሌላውን ‘ና’ ስለው ይመጣል ፤
አገልጋዬንም ፤ ‘ይህን አድርግ’ ስለው ያደር
ጋል ።”
9 ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ ተደነቀ ፤ ወደሚ
ከተሉትም ሰዎች መለስ ብሎ “በእስራኤል
እንኳ እንዲህ ያለ እምነት ከቶ አላገኘሁም
እላችኋለሁ” አላቸው ።
10 የተላኩትም ሰዎች ወደ መቶ አለቃው
ቤት ተመልሰው በመጡ ጊዜ አገልጋዩ ድኖ
አገኙት ።

### ኢየሱስ የአንዲት መበለት ልጅ ከሞት አስነሣ

11 በማግሥቱ ኢየሱስ ናይን ወደምትባል
ወደ አንዲት ከተማ ሄደ ፤ ደቀ መዛሙርቱና
ብዙ ሕዝብ ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ ፤ 12 ኢየ
ሱስ ወደ ከተማይቱ በር አጠገብ ሲደርስ እነሆ
ሰዎች ሬሳ ተሸክመው ከከተማይቱ ይወጡ
ነበር ። የሞተው ሰው ለእናቱ አንድ ነበር ። እና
ቱም ባልዋ የሞተባት መበለት ነበረች ፤ ከከተማ
ይቱም ብዙ ሰዎች ተከትለዋት ነበር ።
13 ጌታም ባያት ጊዜ ራራላትና “አይዞሽ ፡ አታ
ልቅሺ” አላት ። 14 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደፊት
ራመድ ብሎ ቃሬዛውን ነካ ፤ ቃሬዛውንም የተ
ሸከሙት ሰዎች ቆሙ ፤ ኢየሱስም “አንተ
ወጣት ተነሥ እልሃለሁ!” አለ ። 15 የሞተው
ቀና ብሎ ተቀመጠና መነጋገር ጀመረ ፤ ከዚ
ህም በኋላ ኢየሱስ ለእናትዮዋ “እነሆ ልጅሽ”
ብሎ ሰጣት ፤
16 ሁሉንም ፍርሃት ይዞአቸው “ታላቅ
ነቢይ ከመካከላችን ተነሥቶአል ፤ እግዚአብሔር
ሕዝቡን ሊያድን መጥቶአል” እያሉ እግዚአብ
ሔርን አመሰገኑ ።
17 የኢየሱስ ዝና በይሁዳ ክፍለ ሀገር ሁሉና
በዙሪያውም ባለው አገር ሁሉ ተሰማ ።

### ከአጥማቂው ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ የተላኩ መልእክተኞች
(ማቴ. 11፥2-19)

18 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ይህን ሁሉ ለዮ
ሐንስ አወሩለት ፤ እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ
ሁለቱን ጠርቶ ፡ 19 “ ‘ይመጣል የተባለው
መሲሕ አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ብላ
ችሁ ጠይቁት” ሲል ወደ ጌታ ኢየሱስ ላካ
ቸው ።
20 እነርሱም ወደ ኢየሱስ ሄደው “ ‘ይመ
ጣል የተባለው መሲሕ አንተ ነህን? ወይስ ሌላ
እንጠብቅ?’ ብላችሁ ጠይቁት ሲል አጥማቂው
ዮሐንስ ወደ አንተ ልኮናል” አሉት ።
21 ኢየሱስ በዚያኑ ሰዓት ሰዎችን ከልዩ ልዩ
በሽታና ደዌ ፈወሰ ፤ ርኩሳን መናፍስትንም አስ
ወጣ ፤ የብዙ ዕውሮችንም ዐይን አበራ ። 22 ኢየ
ሱስ መልእክተኞቹን እንዲህ አላቸው ፡ “ተመ
ልሳችሁ ሂዱና ለዮሐንስ ያያችሁትንና የሰማች
ሁትን ንገሩት ፤ እነሆ ዕውሮች ያያሉ ፤ አንካ
ሶች ቀጥ ብለው ይሄዳሉ ፤ ለምጻሞች ይድናሉ ፤
ደንቆሮዎች ይሰማሉ ፤ ሙታን ይነሣሉ ፤ ለድሆ
ችም የምሥራች ይነገራል ። 23 በእኔ የማይጠራ
ጠርና የማይሰናከል የተመሰገነ ነው ።”
24 የዮሐንስ መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ ኢየ
ሱስ ስለ ዮሐንስ ለሕዝቡ እንዲህ እያለ ይናገር
ጀመር ፡ “ምን ልታዩ ወደ በረሓ ወጣችሁ? በነ
ፋስ የሚወዛወዘውን ሸንበቆ ለማየት ነውን?
25 ደግሞስ ምን ለማየት ወጣችሁ? ቀጭን የሐር
ልብስ የለበሰውን ሰው ለማየት ነውን? ቀጭን
የሐር ልብስ የሚለብሱና በቅምጥልነት የሚኖ
ሩማ በነገሥታት ቤት ይገኛሉ! 26 ታዲያስ ምን
ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይ ለማየት ነውን? አዎ
እላችኋለሁ ፡ እንዲያውም ከነቢይ የሚበልጠ
ውን ለማየት ነው ። 27 እርሱ ‘እነሆ እፊት እፊት
እየሄደ መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን
እልካለሁ’ ተብሎ የተጻፈለት ነው ። 28 በምድር
ላይ ከተወለዱት ሰዎች ሁሉ ከዮሐንስ የሚበልጥ
ከቶ ማንም የለም ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት
ግን ከሁሉ ያነሰ ይበልጠዋል ።”
29 ይህን በሰሙ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቀራጮ
ችም እንኳ ሳይቀሩ በዮሐንስ እጅ ተጠምቀው
ስለነበር የእግዚአብሔር ሥራ ትክክል መሆኑን
ተገነዘቡ ። 30 ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህ
ራን ግን በዮሐንስ እጅ አንጠመቅም በማለት
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተቃውመው ነበር ።
31 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “እንግ
ዲህ የዚህን ዘመን ሰዎች በምን እመስላቸዋ
ለሁ? ምንስ ይመስላሉ? 32 በአደባባይ ተቀም
ጠው የሚጫወቱ ልጆችን ይመስላሉ ፤ እነር
ሱም እርስ በእርሳቸው እየተጠራሩ ‘የደስታ



ሙዚቃ አሰማናችሁ ፤ እናንተ ግን አልጨፈራች
ሁም ፤ የሐዘን እንጉርጉሮ አሰማናችሁ እናንተ
ግን አላለቀሳችሁም’ የሚሉ ናቸው ። 33 እንዲ
ሁም አጥማቂው ዮሐንስ እህል ሳይበላና የወይን
ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ ‘ጋኔን አለበት’ አላች
ሁት ። 34 የሰው ልጅ ደግሞ እየበላና እየጠጣ
ቢመጣ ‘እነሆ ይህ መብልና መጠጥ የሚወድ
ነው ፤ የቀራጮችና የኃጢአተኞችም ወዳጅ
ነው’ አላችሁት ። 35 ነገር ግን የእግዚአብሔር
ጥበብ ትክክለኛነት የሚታወቀው በጥበበኞች
ዘንድ ብቻ ነው ።”

### አንዲት ሴት የኢየሱስን እግር ሽቶ ቀባች

36 አንድ ፈሪሳዊ ኢየሱስን ምሳ ጋበዘው ፤
ኢየሱስም ወደ ፈሪሳዊው ቤት ገብቶ ምሳ ለመ
ብላት በማእድ ተቀመጠ ። 37 በዚያች ከተማ
አንዲት ኃጢአተኛ ሴት ነበረች ፤ እርስዋም
ኢየሱስ በፈሪሳዊው ስምዖን ቤት ምሳ መጋበ
ዙን በሰማች ጊዜ ሽቶ የሞላበት የአልባስጥሮስ
ብልቃጥ ይዛ መጣች ። 38 ከኢየሱስ በስተኋላ
በእግሮቹ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች እግሮቹን
በእንባዋ ታርስና በጠጉርዋ ታብስ ነበር ፤ እግሮ
ቹን እየሳመች ሽቶ ትቀባቸው ነበር ። 39 ምሳ
የጋበዘው ፈሪሳዊ ይህን ባየ ጊዜ “ይህ ሰው
ነቢይ ቢሆን ኖሮ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን
እንደሆነችና ምን ዐይነት ኃጢአተኛ እንደሆ
ነች ባወቀ ነበር” ሲል በልቡ አሰበ ።
40 ኢየሱስም “ስምዖን ሆይ! አንድ የምነግ
ርህ ነገር አለኝ” አለው ።
እርሱም “መምህር ሆይ! እሺ ንገረኝ”
አለው ።
41 ኢየሱስም እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ ፡
“ከአንድ አበዳሪ ገንዘብ የተበደሩ ሁለት ሰዎች
ነበሩ ፤ አንዱ አምስት መቶ ብር ሌላው ደግሞ
ኀምሳ ብር ተበደሩ ፤ 42 ሁለቱም የተበደሩትን
መክፈል ቢያቅታቸው አበዳሪው ዕዳቸውን ተወላ
ቸው ፤ ታዲያ ከሁለቱ ባለዕዳዎች አበዳሪውን አብ
ልጦ የሚወድ የትኛው ይመስልሃል?” አለው ።
43 ስምዖንም “ብዙ ዕዳ የቀረለት ሰው አብ
ልጦ የሚወድደው ይመስለኛል” ሲል መለሰ ።
ኢየሱስም “መልስህ ልክ ነው” አለው ።
44 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ሴትዮዋ መለስ
ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው ፡ “ይህችን ሴት
ታያለህን? እኔ ወደ ቤትህ ስገባ አንተ ውሃ
እንኳ ለእግሬ አላቀረብህልኝም ፤ እርስዋ ግን
እግሬን በእንባዋ አጥባ በጠጉርዋ አበሰችው ።
45 አንተ ስትቀበለኝ አልሳምኸኝም ፤ እርስዋ
ግን እኔ ወደ ቤትህ ከገባሁ ጀምሮ እግሬን ከመ
ሳም አላቋረጠችም ፤ 46 አንተ ራሴን ዘይት
እንኳ አልቀባኸኝም ፤ እርስዋ ግን እግሮቼን
ሽቶ ቀባች ፤ 47 ስለዚህ ብዙ ስለወደደች ፡ ብዙ
ኃጢአትዋ ይቅር ተብሎላታል እልሃለሁ ። ኃጢ
አቱ በጥቂት ይቅር የሚባልለት ግን የሚወድደ
ውም በጥቂቱ ነው ።”
48 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሴትዮዋን “ኃጢአ
ትሽ ይቅር ተብሎልሻል” አላት ።
49 ከእርሱ ጋር በማእድ ይበሉ የነበሩትም
“ኃጢአትን እንኳ ይቅር የሚል ይህ ማን
ነው?” እያሉ በልባቸው ያስቡ ጀመር ።
50 ኢየሱስ ግን ሴትዮዋን “እምነትሽ አድኖ
ሻል ፤ በሰላም ሂጂ” አላት ።

## ምዕራፍ 8

### ኢየሱስን የተከተሉና ያገለገሉ ሴቶች

1 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በየከተማውና በየመ
ንደሩ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች
እያወጀ ያልፍ ነበር ፤ ዐሥራ ሁለቱም አብረ
ውት ነበሩ ። 2 እንዲሁም ከርኩሳን መናፍስት
የተላቀቁና ከበሽታ የተፈወሱ ሴቶች ኢየሱስን
ይከተሉት ነበር ፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወ
ጡላት መግደላዊት የተባለችው ማርያም ፡ 3 የሄ
ሮድስ ቤት አዛዥ የነበረው የኩዛ ሚስት
ዮሐና ፡ ሶስናና ሌሎችም ብዙዎች ነበሩ ፤ እነ
ዚህ ሴቶች ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን በገንዘ
ባቸው ያገለግሉ ነበር ።

### የዘሪው ምሳሌ
(ማቴ. 13፥1-9፤ ማር. 4፥1-9)

4 ብዙ ሕዝብ ከየከተማው ወደ እርሱ መጥ
ተው በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ ኢየሱስ ይህን
ምሳሌ ነገራቸው ፡
5 “አንድ ገበሬ ዘሩን ሊዘራ ወጣ ፤ ሲዘራም
አንዳንዱ ዘር በመንገድ ዳር ወደቀና ተረገጠ ፤
ወፎችም በሉት ። 6 ሌላውም ዘር በጭንጫማ
መሬት ላይ ወደቀ ፤ በበቀለም ጊዜ መሬቱ እር
ጥበት ስላልነበረው ቡቃያው ደረቀ ። 7 ሌላውም
ዘር በእሾኽ መካከል ወደቀ ፤ እሾኹ አብሮ አደ
ገና አንቆ አስቀረው ። 8 ሌላው ዘር ግን በመል
ካም መሬት ላይ ወድቆ በቀለ ፤ ቡቃያውም
አድጎ እያንዳንዱ መቶ እጥፍ አፈራ ።”
ቀጥሎም ኢየሱስ “ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ”
አለ ።

### ኢየሱስ በምሳሌዎች የተናገረበት ምክንያት
(ማቴ. 13፥10-17፤ ማር. 4፥10-12)

9 ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን “የዚህ ምሳሌ
ትርጒም ምንድን ነው?” ብለው ጠየቁት ።
10 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፡ “ለእና
ንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር

7፥22 ፦ ኢሳ. 35፥5-6 ፤ 61፥1 ። 7፥27 ፦ ሚል. 3፥1 ። 7፥29-30 ፦ ማቴ. 21፥32 ፤ ሉቃ. 3፥12 ።

7፥37-38 ፦ ማቴ. 26፥7 ፤ ማር. 14፥3 ፤ ዮሐ. 12፥3 ። 8፥2-3 ፦ ማቴ. 27፥55-56 ፤ ማር. 15፥40-41 ፤ ሉቃ. 23፥49 ።
8፥10 ፦ ኢሳ. 6፥9-10 ።

ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ፤ ሌሎች ግን ሁሉ ነገር
በምሳሌ ይነገራቸዋል ፤ ምክንያቱም እነርሱ
እያዩ ልብ እንዳያደርጉ ፥ እየሰሙም እንዳያስተ
ውሉ ነው ።”

### ኢየሱስ የዘሪውን ምሳሌ አስረዳ
(ማቴ. 13፥18-23፤ ማር. 4፥13-20)

11 የምሳሌው ትርጒም ይህ ነው ፥ “ዘሩ የእ
ግዚአብሔር ቃል ነው ፤ 12 በመንገድ ዳር የወደ
ቀው ዘር የሚያመለክተው ቃሉን ለጊዜው የሚ
ሰሙትን ሰዎች ነው ፤ ነገር ግን እነርሱ አም
ነው እንዳይድኑ ዲያብሎስ መጥቶ ቃሉን ከልባ
ቸው ይወስዳል ። 13 በጭንጫማ መሬት ላይ
የወደቀውም ዘር የሚያመለክተው ቃሉን ሰም
ተው በደስታ የሚቀበሉትን ሰዎች ነው ፤ ነገር
ግን እነርሱ የሚያምኑት ለጊዜው ነው ፤ ሥር
ስለሌላቸውም በፈተና ጊዜ ወዲያውኑ ይክ
ዳሉ ። 14 በእሾኽም ቊጥቋጦ መካከል የወደ
ቀው ዘር የሚያመለክተው ፥ ቃሉን ለጊዜው
የሚሰሙትን ሰዎች ነው ፤ ነገር ግን የዚህ
ዓለም አሳብና ሀብት ፥ የምድራዊ ኑሮ ምቾትም
አንቆ ያለፍሬ ያስቀራቸዋል ። 15 በመልካም
መሬት ላይ የወደቀው ዘር የሚያመለክተው ግን
በመልካምና በቅን ልብ ቃሉን ሰምተው የሚጠ
ብቁትን ነው ፤ እነርሱ በቃሉ ጸንተው ፍሬ
የሚያፈሩ ናቸው ።”

### ስውር መብራት
(ማር. 4፥21-25)

16 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “መብ
ራት አብርቶ እንቅብ የሚደፋበት ወይም በአ
ልጋ ሥር የሚያኖረው ማንም የለም ። ይልቅስ
ወደ ቤት የሚገቡ ሁሉ ብርሃኑን እንዲያዩ በመ
ቅረዝ ላይ ያኖረዋል ።
17 “እንዲሁም በይፋ ሳይገለጥ ተሰውሮና
ተሸሽጎ የሚቀር ምንም ነገር የለም ።
18 “ስለዚህ ቃሉን እንዴት እንደምትሰሙ
ተጠንቀቁ ፤ ምክንያቱም ላለው ሰው ተጨምሮ
ይሰጠዋል ፤ የሌለው ግን አለኝ ብሎ የሚያስ
በው ጥቂቱም እንኳ ሳይቀር ይወሰድበታል ።”

### የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ
(ማቴ. 12፥46-50፤ ማር. 3፥31-35)

19 የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ ወደ እርሱ
መጡ ፤ ነገር ግን ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያገ
ኙት አልቻሉም ። 20 ስለዚህ “እነሆ እናትህና
ወንድሞችህ በውጪ ቆመው ሊያዩህ ይፈል
ጋሉ” ብለው ሰዎች ነገሩት ።
21 ኢየሱስም “የእግዚአብሔርን ቃል ሰም
ተው የሚፈጽሙት ሁሉ እነርሱ እናቴና ወንድ
ሞቼ ናቸው” አለ ።

### ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ
(ማቴ. 8፥23-27፤ ማር. 4፥35-41)

22 አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
በጀልባ ተሳፈረና “ወደ ባሕሩ ማዶ እንሻገር”
አላቸው ። እነርሱም ለመሄድ ተነሡ ። 23 በባ
ሕሩ ላይ እየቀዘፉ ሲሄዱ ሳሉ ኢየሱስ አንቀ
ላፋ ፤ በዚያን ጊዜ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ በባሕሩ
ላይ ተነሣ ። ውሃውም በጀልባው ውስጥ መሙ
ላት ስለጀመረ ሁሉም ተጨነቁ ። 24 ስለዚህ
ደቀ መዛሙርቱ “መምህር ሆይ! መምህር
ሆይ! እረ ልናልቅ ነው!” ሲሉ ኢየሱስን ቀሰ
ቀሱት ።
እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና ማዕበሉን ገሠጻ
ቸው ፤ ነፋሱና ማዕበሉ ወዲያውኑ ቀጥ አሉ ፤
ታላቅ ጸጥታም ሆነ ። 25 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ
ደቀ መዛሙርቱን “እምነታችሁ የት አለ?”
አላቸው ።
እነርሱ ግን እጅግ ተደንቀውና ፈርተው
እርስ በርሳቸው “ነፋስንና ማዕበልን ያዝዛል ፤
እነርሱም ይታዘዙለታል ፤ እረ ለመሆኑ ይህ
ማን ነው?” ተባባሉ ።

### ኢየሱስ አጋንንት ያደሩበትን ሰው አዳነ
(ማቴ. 8፥28-34፤ ማር. 5፥1-20)

26 ባሕሩንም ተሻግረው በገሊላ ማዶ ወደም
ትገኘው ወደ ጌራሴኖን አገር ደረሱ ፤ 27 ኢየ
ሱስ ከጀልባ ወደ ምድር በወረደ ጊዜ አጋንንት
ያደሩበት አንድ ሰው ከከተማ ወጥቶ ተገና
ኘው ፤ ይህ ሰው ልብሱን ከጣለ ብዙ ጊዜው
ነበር ፤ የሚኖረውም ፥ በመቃብር ቦታ እንጂ
በቤት ውስጥ አልነበረም ። 28 ኢየሱስን ባየ ጊዜ
ጮኸ ፤ በኢየሱስ ፊትም ወደቀና ድምፁን ከፍ
አድርጎ “አንተ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ
ኢየሱስ ሆይ! ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለህ?
እባክህ አታሠቃየኝ!” አለው ። 29 ይህንንም ያለ
በት ምክንያት ኢየሱስ ርኩሱን መንፈስ ከሰው
የው እንዲወጣ አዝዞት ስለነበር ነው ። ከዚህ
በፊት ርኩሱ መንፈስ በሰውየው ላይ ብዙ ጊዜ
ይነሣበት ነበር ፤ በሰንሰለትና በእግር ብረት እየ
ታሰረ ይጠበቅ ነበር ፤ ይሁን እንጂ ሰንሰለቱን
ይበጥስ ፥ እግር ብረቱንም ይሰብር ነበር ። ጋኔ
ኑም እየነዳ ወደ በረሓ ይወስደው ነበር ።
30 ኢየሱስም “ስምህ ማን ነው?” ብሎ ጠየ
ቀው ፤
እርሱም ብዙ አጋንንት ሰፍረውበት ስለነበር
“ስሜ ሠራዊት ነው” ሲል መለሰለት ። 31 አጋን
ንቱም “እባክህ ወደ ጥልቁ ገደል አትስደደን”
ሲሉ ለመኑት ።
32 በዚያም ስፍራ በኮረብታ ጥግ የብዙ ዐሳ
ማዎች መንጋ ተሰማርቶ ነበር ፤ አጋንንቱ

8፥16 ፦ ማቴ. 5፥15 ፤ ሉቃ. 11፥33 ። 8፥17 ፦ ማቴ. 10፥26 ፤ ሉቃ. 12፥2 ። 8፥18 ፦ ማቴ. 25፥29 ፤ ሉቃ. 19፥26 ።



“ወደ ዐሳማዎቹ እንድንገባ ፍቀድልን” ሲሉ
ኢየሱስን ለመኑት ፤ እርሱም ፈቀደላቸው ።
33 ስለዚህ አጋንንቱ ከሰውየው ወጥተው በዐሳማ
ዎቹ ውስጥ ገቡ ፤ ዐሳማዎቹ ከገደሉ ላይ እየተ
ንደረደሩ ወረዱ ፤ ወደ ባሕር ገብተውም
ሰጠሙ ።
34 የዐሳማዎቹም እረኞች የሆነውን ነገር ባዩ
ጊዜ ሸሽተው ሄዱ ፤ በየከተማውና በየገጠሩም
ወሬውን ነዙት ። 35 ሰዎቹም የሆነውን ነገር ለማ
የት ከየቤታቸው ወጥተው ወደ ኢየሱስ መጡ ፤
አጋንንት የወጡለትንም ሰው ልቡናው ተመልሶለ
ትና ልብሱንም ለብሶ ፥ በኢየሱስ እግር ሥር ተቀ
ምጦ ባዩት ጊዜ ፈሩ ፤ 36 የዐይን ምስክር የነበሩ
ሰዎችም አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው እን
ዴት እንደ ዳነ አወሩላቸው ። 37 ከዚህ በኋላ የገራ
ሴኖን ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ከአገራቸው ወዲያ እን
ዲሄድላቸው ለመኑት ። ይህንንም ያሉበት ምክን
ያት በጣም ፈርተው ስለነበረ ነው ። ስለዚህ ኢየ
ሱስ በጀልባ ተሳፈረና ወደ መጣበት ስፍራ ተመ
ልሶ ሄደ ። 38 አጋንንት የወጡለትም ሰው ኢየሱ
ስን “እባክህ ልከተልህ” ብሎ ለመነው ።
39 ኢየሱስ ግን “ወደ ቤትህ ሂድና እግዚአብ
ሔር ያደረገውን ሁሉ ተናገር” ብሎ አሰናበ
ተው ።
ሰውየውም ኢየሱስ ያደረገለትን ትልቅ ነገር
በከተማው ሁሉ እየተናገረ ሄደ ።

### የኢያኢሮስ ልጅና የኢየሱስን ልብስ የነካች ሴት
(ማቴ. 9፥18-26፤ ማር. 5፥21-43)

40 ሕዝቡ ይጠባበቀው ስለነበር ፥ ኢየሱስ
ተመልሶ በመጣ ጊዜ ሁሉም በደስታ ተቀበ
ሉት ። 41 በዚያን ጊዜ አንድ የምኵራብ አለቃ
የሆነ ኢያኢሮስ የተባለ ሰው መጣ ፤ በኢየሱስ
እግር ሥር ወድቆ “እባክህ ወደ ቤቴ ናልኝ”
ብሎ ለመነው ። 42 ምክንያቱም ዕድሜዋ ዐሥራ
ሁለት ዓመት የሆናት አንዲት ልጁ ታማ በሞት
አፋፍ ላይ ስለነበረች ነው ።
ኢየሱስም ከእርሱ ጋር አብሮ ሲሄድ ሳለ
ተከትለውት የነበሩ ብዙ ሰዎች በመጋፋት
ያጨናንቁት ነበር ። 43 ዐሥራ ሁለት ዓመት
ሙሉ ደም እየመታት የምትሠቃይ አንዲት
ሴት ነበረች ፤ እርስዋ ያላትን ገንዘብ ሁሉ ለሐ
ኪሞች በመስጠት ጨርሳ ማንም ሊያድናት
አልቻለም ። 44 እርስዋ ወደ ኢየሱስ መጥታ
በስተኋላው ቀረበችና የልብሱን ጫፍ ነካች ፤
ወዲያውኑ ደምዋ መፍሰሱን አቆመ ። 45 ኢየሱ
ስም “ማን ነው የነካኝ?” ሲል ጠየቀ ።
ሁሉም “እኛ አልነካንህም” አሉ ፤ ጴጥሮ
ስም “መምህር ሆይ! ሕዝቡ እየተጋፋ ሲከተ
ልህ እያየህ ማን ነው የነካኝ ትላለህን?” አለ ።

46 ኢየሱስ ግን “ኀይል ከእኔ መውጣቱን
ዐውቄአለሁና በእርግጥ አንድ ሰው ነክቶኛል”
አለ ። 47 ሴትዮዋም እንዳልተሰወረች ባወቀች
ጊዜ እየተንቀጠቀጠች ወደ ኢየሱስ መጥታ በእ
ግሩ ሥር ወደቀች ፤ ከዚያም በኋላ ለምን እንደ
ነካችውና እንዴት ወዲያውኑ እንደተፈወሰችም
በሕዝቡ ሁሉ ፊት ገለጠች ። 48 ኢየሱስም
“ልጄ ሆይ! እምነትሽ አድኖሻል ፤ በሰላም
ሂጂ” አላት ።
49 ኢየሱስ ገና ይህንን በመናገር ላይ ሳለ
አንድ ሰው ከምኵራብ አለቃው ከኢያኢሮስ
ቤት መጥቶ ኢያኢሮስን “ልጅህ ሞታለች ፤ እን
ግዲህ መምህሩን በከንቱ አታድክመው”
አለው ።
50 ኢየሱስ ግን ይህን ሰምቶ ኢያኢሮስን
“አይዞህ አትፍራ ፤ እመን ብቻ ፤ ልጅህ ትድና
ለች” አለው ።
51 ኢየሱስ ወደ ኢያኢሮስ ቤት በደረሰ ጊዜ
ከጴጥሮስ ፥ ከዮሐንስ ፥ ከያዕቆብ ፥ ከልጅትዋ
አባትና እናት በቀር ሌላ ማንም ከእርሱ ጋር
ወደ ውስጥ እንዲገባ አልፈቀደም ። 52 በዚያ የነ
በሩ ሰዎች ሁሉ ስለ ልጅትዋ በማዘን ያለቅሱ
ነበር ። ኢየሱስ ግን “አታልቅሱ ፤ ልጅትዋ ታን
ቀላፋለች እንጂ አልሞተችም እኮ” አላቸው ።
53 እነርሱ ግን ልጅትዋ መሞትዋን ስላወቁ
ሁሉም በማፌዝ ሳቁበት ። 54 ኢየሱስ የልጅት
ዋን እጅ ይዞ “አንቺ ልጅ ፥ ተነሺ” አላት ።
55 እርስዋም ነፍስዋ ስለተመለሰችላት ወዲያ
ውኑ ብድግ አለች ፤ ኢየሱስም “የምትበላውን
ስጡአት” ሲል አዘዘ ። 56 የልጅትዋም ወላጆች
ተገረሙ ፤ እርሱ ግን ይህን ነገር ለማንም እንዳትና
ገሩ ሲል አዘዛቸው ።

## ምዕራፍ 9

### ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት ላከ
(ማቴ. 10፥5-15፤ ማር. 6፥7-13)

1 ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ ጠርቶ
አጋንንትን የማውጣትና ደዌንም ሁሉ የመፈወስ
ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው ። 2 የእግዚአብሔርን
መንግሥት መምጣት ለሰው ሁሉ እንዲነግሩ ፥
በሽተኞችን እንዲፈውሱ ላካቸው ። 3 እንዲህም
አላቸው ፥ “ለመንገዳችሁ የሚሆን ምንም አት
ያዙ ፤ በትርም ቢሆን ፥ ከረጢትም ቢሆን ፥ ስን
ቅም ቢሆን ፥ ገንዘብም ቢሆን ፥ ቅያሬ ልብስም
እንኳ ቢሆን አትያዙ ። 4 በእንግድነት በምትገቡ
በት ቤት ሁሉ ከዚያ መንደር ወጥታችሁ እስክ
ትሄዱ ድረስ በዚያው ቆዩ ። 5 ሰዎች የማይቀበሉ
ዋችሁ ከሆነ ግን ያችን መንደር ለቃችሁ ስት
ወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ ሂዱ ፤
ይህም የማስጠንቀቂያ ምስክር ይሆንባቸዋል ።”

9፥3-5 ፦ ሉቃ. 10፥4-11 ፤ ሐ.ሥ. 13፥51 ።

6 ስለዚህ ሐዋርያቱ ከዚያ ወጥተው ወንጌ
ልን እያስተማሩና በሽተኞችን እየፈወሱ በየመን
ደሩ ሁሉ ያልፉ ነበር ።

### ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ ዝና ሰማ
(ማቴ. 14፥1-12፤ ማር. 6፥14-29)

7 የገሊላ አገረ ገዥ የነበረው ሄሮድስ ፥ ኢየ
ሱስ ያደረገውን ሁሉ በመስማቱ ተደናገረ ፤
ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች “አጥማቂው ዮሐ
ንስ ከሞት ተነሥቶአል” እያሉ ያወሩ ስለነበረ
ነው ። 8 እንዲሁም አንዳንዶቹ “ነቢዩ ኤልያስ
ተመልሶ መጥቶአል” ሲሉ ፥ ሌሎች ደግሞ
“ከቀድሞዎቹ ነቢያት አንዱ ከሞት ተነሥቶ
አል” ይሉ ነበር ። 9 ሄሮድስም በበኩሉ “እኔ
የዮሐንስን ራስ አስቈርጬ ነበር ፤ ታዲያ ይህን
ሁሉ ነገር ያደርጋል እየተባለ የሚነገርለት
እርሱ ማን ነው?” ይል ነበር ። ሊያየውም ይፈ
ልግ ነበር ።

### ኢየሱስ አምስት ሺ ሰዎች መገበ
(ማቴ. 14፥13-21፤ ማር. 6፥30-44፤
ዮሐ. 6፥1-14)

10 ሐዋርያት ከተላኩበት ተመልሰው መጡና
ያደረጉትን ሁሉ ለኢየሱስ ነገሩት ። እርሱም
በቤተ ሳይዳ ከተማ አጠገብ ወደሚገኘው ገለል
ተኛ ቦታ ብቻቸውን ይዞአቸው ሄደ ። 11 ሰዎ
ቹም ኢየሱስ የት እንደሆነ ባወቁ ጊዜ ተከተ
ሉት ፤ እርሱም ተቀበላቸውና ስለ እግዚአብሔር
መንግሥት አስተማራቸው ። ከበሽታ መዳን የሚ
ያስፈልጋቸውንም በሽተኞች ሁሉ ፈወሳቸው ።
12 ቀኑ ሊመሽ ሲል ዐሥራ ሁለቱ ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው እንዲህ አሉት ፥ “ይህ ያለንበት
ቦታ በረሓ ነው ፤ ስለዚህ ሰዎቹ በአካባቢው
ወዳሉት ከተሞችና ገጠሮች ሄደው ምግብና
ማደሪያ እንዲያገኙ አሰናብታቸው ።”
13 ኢየሱስ ግን “እናንተ ራሳችሁ የሚበሉ
ትን ስጡአቸው” አላቸው ።
እነርሱም “እኛ ያለን አምስት እንጀራና
ሁለት ዓሣ ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ሄደን ምግብ
ካልገዛን በቀር ለዚህ ሁሉ ሕዝብ አይበቃም”
አሉት ። 14 የሰዎቹም ብዛት አምስት ሺ ያህል
ነበር ።
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “ሰዎቹ በኀምሳ
በኀምሳ ፥ ተከፋፍለው እንዲቀመጡ አድርጉአ
ቸው” አላቸው ።
15 ደቀ መዛሙርቱም ልክ እርሱ እንዳዘዛ
ቸው ሰዎቹ እንዲቀመጡ አደረጉ ። 16 ከዚህም
በኋላ ኢየሱስ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ
ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና እግዚአብሔርን
አመሰገነ ፤ ቈርሶም ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀ
መዛሙርቱ ሰጠ ፤ 17 ሁሉም በልተው ጠገቡ ፤
ደቀ መዛሙርቱ ከሕዝቡ የተረፈውን ፍርፋሪ
ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ ።

### የጴጥሮስ እምነትና ምስክርነት
(ማቴ. 16፥13-19፤ ማር. 8፥27-29)

18 አንድ ቀን ኢየሱስ ብቻውን ይጸልይ
ነበር ፤ ደቀ መዛሙርቱም አጠገቡ ስለነበሩ
“ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል?” ሲል ጠየቃ
ቸው ።
19 እነርሱም “አንዳንዶች ‘አጥማቂው ዮሐ
ንስ ነው’ ፤ ሌሎች ‘ኤልያስ ነው’ ይሉሃል ።
‘ከቀድሞዎቹ ነቢያት አንዱ ከሞት ተነሥቶ
አል’ የሚሉም አሉ” ብለው መለሱለት ።
20 እናንተስ “እኔን ማን ትሉኛላችሁ?”
ብሎ ጠየቃቸው ፤
ጴጥሮስም “አንተ የእግዚአብሔር መሲሕ
ነህ” ሲል መለሰለት ። 21 ኢየሱስም ይህንን ለማ
ንም እንዳይናገሩ በጥብቅ አስጠነቀቃቸው ።

### ኢየሱስን የመከተል ሁኔታ
(ማቴ. 10፥38-39፤ 16፥24-28፤ ማር. 8፥34-38፤
ሉቃ. 14፥26-27)

22 ቀጥሎም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው ፥ “የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀ
በል ይገባዋል ፤ በሽማግሌዎችና በካህናት አለ
ቆች ፥ በሙሴ ሕግ መምህራን ዘንድ ይናቃል ፤
ይገደላልም ፤ ይሁን እንጂ በሦስተኛው ቀን
ከሞት ይነሣል ።”
23 ለሁሉም ደግሞ እንዲህ አላቸው ፥ “ሊከ
ተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ ፤ በየቀኑም
መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ ፤ 24 ከእኔ ይልቅ
ለሕይወቱ የሚሳሳ ሁሉ ያጠፋታል ፤ ስለ እኔ
ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያድናታል ።
25 ሰው የዓለምን ሀብት ሁሉ አግኝቶ ነፍሱን
ግን ቢያጠፋ ወይም ቢጐዳ ምን ይጠቅመዋል?
26 በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅም
በራሱ ክብርና በአባቱ ክብር ፥ እንዲሁም በቅዱ
ሳን መላእክቱ ክብር በሚመጣበት ጊዜ በእርሱ
ያፍርበታል ። 27 በእውነት እላችኋለሁ ፥ አሁን
እዚህ ካሉት መካከል የእግዚአብሔር መንግ
ሥት ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞት የማይነካ
ቸው አንዳንዶች አሉ ።”

### የኢየሱስ መልክ መለወጥ
(ማቴ. 17፥1-8፤ ማር. 9፥2-8)

28 ኢየሱስ ይህን ከተናገረ ከስምንት ቀን
በኋላ ጴጥሮስን ፥ ዮሐንስንና ያዕቆብን አስከትሎ

9፥7-8 ፦ ማቴ. 16፥14 ፤ ማር. 8፥28 ፤ ሉቃ. 9፥19 ። 9፥19 ፦ ማቴ. 14፥1-2 ፤ ማር. 6፥14-15 ፤ ሉቃ. 9፥7-8 ።
9፥20 ፦ ዮሐ. 6፥68-69 ። 9፥23 ፦ ማቴ. 10፥38 ፤ ሉቃ. 14፥27 ። 9፥24 ፦ ማቴ. 10፥39 ፤ ሉቃ. 17፥33 ፤ ዮሐ. 12፥25 ።
9፥28-35 ፦ 2ጴጥ. 1፥17-18 ።



ለመጸለይ ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጣ ። 29 በሚ
ጸልይበትም ጊዜ መልኩ ተለወጠ ፤ ልብሱም
ነጭ ሆኖ አንጸባረቀ ፤ 30 እነሆ በድንገት ሁለት
ሰዎች መጥተው ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር ።
እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ነበሩ ። 31 በክብር
ተገልጠው ይነጋገሩ የነበሩትም ፥ ኢየሱስ በኢየ
ሩሳሌም መከራ እንደሚቀበልና እንደሚሞት
ነበር ። 32 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስና ጓደኞቹ በእንቅ
ልፍ ተሸንፈው ተኝተው ነበር ። በነቁ ጊዜ ግን
የኢየሱስን ክብር አዩ ፤ እንዲሁም ከእርሱ ጋር
የነበሩትን ሁለቱን ሰዎች አዩ ። 33 ሁለቱ ሰዎች
ከኢየሱስ ተለይተው በሄዱ ጊዜ ጴጥሮስ ኢየሱ
ስን “መምህር ሆይ! እዚህ መሆን ለእኛ መል
ካም ነው ፤ ስለዚህ አንድ ለአንተ ፥ አንድ
ለሙሴ ፥ አንድ ለኤልያስ የሚሆኑ ሦስት ዳሶች
እንሥራ” አለው ። ጴጥሮስ ይህን ሲናገር የሚለ
ውን አያውቅም ነበር ።
34 ጴጥሮስ ይህን ሲናገር ሳለ ደመና መጥቶ
ጋረዳቸው ፤ ደመናውም በጋረዳቸው ጊዜ ፈሩ ።
35 ከደመናውም ውስጥ “የመረጥሁት ልጄ ይህ
ነው ፤ እርሱን ስሙት” የሚል ድምፅ መጣ ።
36 ድምፁም ከተሰማ በኋላ ኢየሱስ ብቻውን
ሆኖ ተገኘ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያዩትን ሁሉ
በዚያን ጊዜ ለማንም ሳይናገሩ ዝም አሉ ።

### ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ ያደረባትን ልጅ ፈወሰ
(ማቴ. 17፥14-18፤ ማር. 9፥14-27)

37 በማግሥቱ ኢየሱስና ሦስቱ ደቀ መዛሙ
ርት ከተራራው በወረዱ ጊዜ ብዙ ሰዎች ኢየሱ
ስን ተገናኙት ። 38 ከሰዎቹም መካከል አንድ
ሰው እንዲህ ሲል ጮኸ ፥ “መምህር ሆይ! ይህ
ልጅ ለኔ አንድ ብቻ ነውና እባክህ እይልኝ ፤
39 እነሆ ርኩስ መንፈስ በድንገት ይዞ ያስጮኸ
ዋል ፤ በመሬት ላይ ጥሎ አረፋ እያስደፈቀ ያን
ፈራግጠዋል ፤ ሰውነቱንም እያቈሰለ በአሳር ይለ
ቅቀዋል ። 40 ርኩሱን መንፈስ እንዲያስወጡለት
ደቀ መዛሙርትህን ጠይቄአቸው ነበር ። ነገር
ግን አልቻሉም ።”
41 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥ “እናንተ እምነት
የሌላችሁ ጠማማ ትውልድ ፤ እስከ መቼ ከእና
ንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼ እታገሣችኋ
ለሁ? እስቲ ልጅህን ወዲህ አምጣው ።”
42 ልጁም ወደ ኢየሱስ በቀረበ ጊዜ ጋኔኑ
በመሬት ላይ ጥሎ አንፈራገጠው ፤ ኢየሱስ ግን
ርኩሱን መንፈስ ገሠጸው ፤ ልጁንም ፈውሶ ለአ
ባቱ ሰጠው ። 43 ሕዝቡም ሁሉ የእግዚአብሔ
ርን ታላቅ ኀይል በማየታቸው ተገረሙ ፤

### ኢየሱስ ስለ ሞቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ
(ማቴ. 17፥22-23፤ ማር. 9፥30-32)

ሁሉም በተደረገው ነገር በመደነቅ ላይ ሳሉ
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ፤
44 “ይህን የምነግራችሁን ቃል ልብ ብላችሁ
አስተውሉ እነሆ የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተላ
ልፎ ይሰጣል ።” 45 እነርሱ ግን ይህን ነገር አላ
ስተዋሉም ፤ የንግግሩም ምስጢር ተሰውሮባ
ቸው ነበር ፤ እንዳይጠይቁትም ፈሩ ።

### ከሁሉ የሚበልጥ ማንነው?
(ማቴ. 18፥1-5፤ ማር. 9፥33-37)

46 ደቀ መዛሙርቱ “ከእኛ ከሁላችን የሚበ
ልጥ ማንነው?” በማለት ክርክር አንሥተው
ነበር ። 47 ኢየሱስ ግን የልባቸውን አሳብ
ዐውቆ ፥ አንድ ሕፃን ልጅ አመጣና በአጠገቡ
አቆመው ፤ 48 እንዲህም አላቸው ፥ “ይህንን
ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል ፤
እኔንም የሚቀበል ሁሉ የላከኝን ይቀበላል ።
ከእናንተ መካከል ከሁላችሁም የሚያንስ እርሱ
ከሁሉ የሚበልጥ ይሆናል ።”

### የማይቃወማችሁ ሁሉ ከእናንተ ጋር ነው
(ማር. 9፥38-40)

49 ከዚህም በኋላ ዮሐንስ ኢየሱስን “መም
ህር ሆይ! አንድ ሰው በስምህ አጋንንት ሲያ
ወጣ አየነው ፤ ነገር ግን ከእኛ ጋር አንተን ስለ
ማይከተል ከለከልነው” አለ ።
50 ኢየሱስም “የማይቃወማችሁ ሁሉ ከእና
ንተ ጋር ስለሆነ ተዉ ፥ አትከልክሉት” አለ ።

### የሰማርያ ሰዎች ኢየሱስን ለመቀበል አልፈለጉም

51 ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚወጣበት ቀን በተ
ቃረበ ጊዜ ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቈርጦ
ተነሣ ። 52 ከእርሱ በፊት ቀድመው የሚሄዱት
ንም መልእክተኞች ላከ ፤ እነርሱም ሁሉን
ነገር ለማዘጋጀት በሰማርያ ወደምትገኘው ወደ
አንዲት መንደር ሄዱ ። 53 ነገር ግን የዚያች
መንደር ሰዎች ሊቀበሉት አልፈለጉም ፤ ምክን
ያቱም እርሱ በዚያ አልፎ ወደ ኢየሩሳሌም
የሚሄድ መሆኑን ዐውቀው ስለነበር ነው ።
54 ደቀ መዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህን ባዩ
ጊዜ “ጌታ ሆይ![2*] ከሰማይ እሳት ወርዶ እነዚ
ህን ሰዎች ያቃጥላቸው ዘንድ እንድናዝዝ ትፈ
ቅዳለህን?” አሉት ።

2* 9፥54 አንዳንድ ቅጂዎች “ኤልያስ እንዳደረገ” የሚል ቃል ይጨምራሉ ።
9፥35 ፦ ኢሳ. 42፥1 ፤ ማቴ. 3፥17 ፣ 12፥18 ፣ ማር. 1፥11 ፤ ሉቃ. 3፥22 ። 9፥46 ፦ ሉቃ. 22፥24 ። 9፥48 ፦ ማቴ. 10፥40 ፤
ሉቃ. 10፥16 ፤ ዮሐ. 13፥20 ። 9፥54 ፦ 2ነገ. 1፥9-16 ።

55 ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ መለስ ብሎ ገሠ
ጻቸው ። [እናንተ ከምን ዐይነት መንፈስ እንደ
ሆናችሁ አታውቁም ፤ የሰው ልጅ የመጣው የሰ
ውን ሕይወት ለማዳን ነው እንጂ ለማጥፋት
አይደለም ።] 56 ከዚያም ተነሥተው ወደ ሌላ
መንደር ሄዱ ።

የኢየሱስን ተከታዮች የሚገጥማቸው ፈተና
(ማቴ. 8፥19-22)

57 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ጕዞ ቀጥለው
በመንገድ ላይ ሳሉ ፥ አንድ ሰው ኢየሱስን “እኔ
ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ እፈልጋለሁ”
አለው ።
58 ኢየሱስም “ቀበሮዎች ጕድጓድ አላቸው ፤
ወፎችም ጎጆ አላቸው ፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን
እንኳ አስጠግቶ የሚያሳርፍበት ስፍራ የለ
ውም” ሲል መለሰለት ።
59 ሌላውንም ሰው “ተከተለኝ” አለው ።
ሰውየው ግን “ጌታ ሆይ! መጀመሪያ ሄጄ
አባቴን ጠሬ እንድቀብር ፍቀድልኝ” አለው ።
60 ኢየሱስም “ሙታንን ተዋቸው ፤ ሙታኖ
ቻቸውን ይቅበሩ ፤ አንተ ግን ሂድና ስለ እግዚአ
ብሔር መንግሥት አስተምር” ሲል መለሰለት ።
61 አንድ ሌላ ሰው ደግሞ “ጌታ ሆይ! እኔ
ልከተልህ እፈልጋለሁ ፤ ነገር ግን መጀመሪያ
ሄጄ ቤተሰቤን እንድሰናበት ፍቀድልኝ”
አለው ።
62 ኢየሱስም “ለማረስ በእጁ ዕርፍ ይዞ ወደ
ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግ
ሥት የተገባ አይደለም” ሲል መለሰለት ።

## ምዕራፍ 10

### ኢየሱስ ወንጌልን እንዲያስተምሩ ሰባ ሁለት ደቀ መዛሙርትን ላከ

1 ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ ሁለት[3*] ሰዎ
ችን መረጠ ፤ እርሱ ሊሄድበት ወደአሰበውም
ከተማና ቦታ ሁሉ ቀድመውት እንዲሄዱ ሁለት
ሁለት አድርጎ ላካቸው ። 2 እንዲህም አላቸው ፥
“እነሆ መከሩ ብዙ ነው ፤ የመከሩ ሠራተኞች
ግን ጥቂቶች ናቸው ፤ ስለዚህ የመከሩ ጌታ ለመ
ከሩ ሥራ ተጨማሪ ሠራተኞችን እንዲልክ ለም
ኑት ። 3 እንግዲህ ሂዱ ፤ እነሆ እንደ በጎች
በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ ፤ 4 ለመንገዳ
ችሁ ምንም አትያዙ ፤ የገንዘብ ቦርሳም ቢሆን ፥
ከረጢትም ቢሆን ፥ ጫማም ቢሆን አትያዙ ፤
ከሰው ጋር ሰላምታ በመለዋወጥ በመንገድ ላይ
ቆማችሁ ጊዜ አታጥፉ ። 5 በገባችሁበት ቤት
ሁሉ አስቀድማችሁ ‘ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን’
በሉ ፤ 6 ሰላም ወዳድ ሰው በዚያ ቤት ቢኖር ሰላ
ማችሁ ያድርበታል ፤ አለበለዚያ ግን ሰላማችሁ
ወደ እናንተ ይመለሳል ። 7 ለሠራተኛ ደመወዝ
ይገባዋል ፤ ስለዚህ በገባችሁበት ቤት ያቀረቡላች
ሁን እየበላችሁና እየጠጣችሁ ቈዩ ፤ ከቤት ወደ
ቤትም አትዘዋወሩ ። 8 በማናቸውም ከተማ ስትገ
ቡና ሰዎችም ሲቀበሉአችሁ የሚያቀርቡላችሁን
ብሉ ። 9 በዚያችም ከተማ የሚገኙትን በሽተኞች
ፈውሱ ፤ ለሕዝቡም ‘የእግዚአብሔር መንግሥት
ወደ እናንተ ቀርባለች’ እያላችሁ ተናገሩ ።
10 ነገር ግን በማናቸውም ከተማ ስትገቡ ሰዎቹ
የማይቀበሉአችሁ ቢሆን ወደ ከተማይቱ አደባ
ባይ ውጡና እንዲህ በሉአቸው ፥ 11 ‘እነሆ በእግ
ራችን ላይ ያለውን የከተማችሁን ትቢያ እንኳ
እናራግፍላችኋለን ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር
መንግሥት ወደ እናንተ እንደቀረበች ዕወቁ ።’
12 በፍርድ ቀን ከዚህች ከተማ ይልቅ ለሰዶም
ከተማ ቅጣቱ ይቀልላታል እላችኋለሁ ።”

### ባለማመናቸው የተወቀሱ ከተሞች
(ማቴ. 11፥20-24)

13 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ወዮልሽ
ኮራዚን ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ ፤ በእናንተ የተደ
ረጉት ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርገው
ቢሆን ኖሮ ፥ በዚያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የሐዘን
ልብስ ለብሰውና ዐመድ ላይ ተቀምጠው ገና
ድሮ ንስሓ በገቡ ነበር ። 14 ስለዚህ በፍርድ ቀን
ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀ
ልላቸዋል ። 15 አንቺም ቅፍርናሆም ፥ እስከ
ሰማይ ከፍ ለማለት ፈልገሻልን? ታዲያ እኮ
ወደ ሲኦል ትወርጂለሽ ።”
16 እንደገናም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
“እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል ፤ እናንተን
የማይቀበል እኔን አይቀበልም ፤ እኔን የማይቀበ
ልም የላከኝን አይቀበልም” አላቸው ።

### ሰባ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከተላኩበት ተመልሰው መጡ

17 ሰባ ሁለቱ[4*] ደቀ መዛሙርት ከተላኩበት
በጣም ደስ ብሎአቸው ተመለሱ ፤ ወደ ኢየሱ
ስም ቀርበው “ጌታ ሆይ! በአንተ ስም አጋን
ንት እንኳ ታዘዙልናል” አሉት ።

[3*] 10፥1 ሰባ ሁለት ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ሰባ” ይላሉ ። [4*] 10፥17 ሰባ ሁለት ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ሰባ” ይላሉ
(ቍ. 1 ተመልከት) ።

9፥61 ፦ 1ነገ. 19፥20 ። 10፥2 ፦ ማቴ. 9፥37-38 ። 10፥3 ፦ ማቴ. 10፥16 ። 10፥4-11 ፦ ማቴ. 10፥7-14 ፤
ማር. 6፥8-11 ፤ ሉቃ. 9፥3-5 ። 10፥7 ፦ 1ቆሮ. 9፥14 ፤ 1ጢሞ. 5፥18 ። 10፥10-11 ፦ ሐ.ሥ. 13፥51 ።
10፥12 ፦ ዘፍ. 19፥24-28 ፤ ማቴ. 11፥24 ፤ 10፥15 ። 10፥13 ፦ ኢሳ. 23፥1-8 ፤ ሕዝ. 26፥1–28፥26 ፤ ኢዩ. 3፥4-8 ፤
አሞጽ 1፥9-10 ፤ ዘካ. 9፥2-4 ። 10፥15 ፦ ኢሳ. 14፥13-15 ። 10፥16 ፦ ማቴ. 10፥40 ፤ ማር. 9፥37 ፤ ሉቃ. 9፥48 ፤
ዮሐ. 13፥20 ።



18 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “ሰይጣን
እንደ መብረቅ ተወርውሮ ከሰማይ ሲወድቅ አየ
ሁት ፤ 19 እነሆ እባብንና ጊንጥን እንድትረ
ግጡ ፥ የጠላትን ኀይል እንድትቋቋሙ ሥል
ጣን ሰጥቻችኋለሁ ፤ የሚጐዳችሁ ምንም ነገር
የለም ። 20 ነገር ግን ስማችሁ በሰማይ መዝገብ
ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ እንጂ አጋንንት ስለታዘ
ዙላችሁ አትደሰቱ ።”

### ኢየሱስ ደስታውን ገለጠ
(ማቴ. 11፥25-27፤ 13፥16-17)

21 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተደ
ስቶ እንዲህ አለ ፥ “የሰማይና የምድር ጌታ የሆ
ንህ አባት ሆይ! ይህንን ነገር ከጥበበኞችና ከዐ
ዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው
አመሰግንሃለሁ ፤ አዎ! አባት ሆይ! ይህን ለማድ
ረግ የአንተ በጎ ፈቃድ ሆኖአል ።
22 “ሁሉ ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል ፤ ወልድ
ማን መሆኑን ከአብ በቀር ማንም የሚያውቅ
የለም ፤ እንዲሁም አብ ማን መሆኑን ከወልድ
በቀር ፥ ወይም ወልድ ሊገልጥለት ከሚፈቅድ
ለት ሰው በቀር ሌላ ማንም የሚያውቅ
የለም ።”
23 ቀጥሎም ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
መለስ ብሎ ለብቻቸው እንዲህ አላቸው ፥ “እና
ንተ የምታዩትን የሚያዩ የታደሉ ናቸው ። 24 በእ
ውነቱ ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት እናንተ የም
ታዩትን ለማየት ተመኝተው ነበር ፤ ነገር ግን አላ
ዩም ፤ እናንተ የምትሰሙትንም ለመስማት ተመ
ኝተው ነበር ፤ ነገር ግን አልሰሙም ።”

### ርኅሩኁ ሳምራዊ

25 አንድ ቀን አንድ የሙሴ ሕግ መምህር
ወደ ኢየሱስ መጣ ፤ ሊፈትነውም ፈልጎ “መም
ህር ሆይ! የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን
ማድረግ ይገባኛል?” ሲል ጠየቀው ። 26 ኢየሱ
ስም “በሙሴ ሕግ ምን ተጽፎአል? አንብበህስ
እንዴት ትረዳዋለህ?” አለው ።
27 ሰውየውም “ሕጉማ ‘እግዚአብሔር አም
ላክህን በፍጹም ልብህ ፥ በፍጹም ነፍስህ ፥ በፍ
ጹም ኀይልህ ፥ በፍጹም አሳብህ ውደድ ፤’ እን
ዲሁም ‘ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ
ውደድ’ ይላል” አለው ።
28 ኢየሱስም “በትክክል መልሰሃል ፤ እንግ
ዲህ አንተም ይህን አድርግ ፤ የዘላለም ሕይወት
ንም ታገኛለህ” አለው ።
29 የሕግ መምህሩ ግን ራሱን ጻድቅ ለማድ
ረግ ፈልጎ “ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?”
ሲል ጠየቀው ።
30 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፤
“አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወ
ርድ በመንገድ ላይ ሳለ ወንበዴዎች አግኝተ
ውት ልብሱን ገፈፉት ፤ ከደበደቡትም በኋላ
ሊሞት ሲያጣጥር ጥለውት ሄዱ ። 31 እንደ አጋ
ጣሚ አንድ ካህን በዚያ መንገድ ይሄድ ነበር ፤
ተደብድቦ የተጣለውን ሰው ባየው ጊዜ ምንም
ሳያደርግለት በሌላ በኩል አልፎ ሄደ ። 32 እንዲ
ሁም ከካህናት ወገን የሆነ አንድ ሌዋዊ በዚያ
መንገድ ይሄድ ነበር ፤ እርሱም ሰውየውን
ባየው ጊዜ ምንም ሳያደርግለት በሌላ በኩል
አልፎ ሄደ ። 33 አንድ ሳምራዊ ግን በዚያ
በኩል ሲያልፍ ወደ ሰውየው መጣ ፤ ባየውም
ጊዜ ራራለት ፤ 34 ወደ እርሱም ቀርቦ ዘይትና
የወይን ጠጅ በቍስሉ ላይ አፈሰሰ ፤ በጨርቅም
ጠምጥሞ አሠረለት ፤ ከዚያም በኋላ በገዛ ራሱ
አህያ ላይ አስቀምጦት ወደ አንድ የእንግዶች
ማደርያ ቤት ወሰደው ፤ በዚያም በልዩ ጥንቃቄ
ተከባከበው ፤ 35 በማግሥቱም ሁለት ብር አው
ጥቶ ለእንግዳ ማደርያው ባለቤት ሰጠና ‘ይህን
ሰው በጥንቃቄ አስታምልኝ ፤ ተጨማሪ ወጪ
ብታደርግም በምመለስበት ጊዜ እከፍልሃለሁ’
አለው ።
36 “ታዲያ ፥ ከእነዚህ ከሦስት ሰዎች በወንበ
ዴዎቹ ተደብድቦ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ
የሆነለት የትኛው ይመስልሃል?”
37 የሕግ መምህሩም “ያ የራራለትና የረዳው
ነዋ!” ሲል መለሰ ፤
ኢየሱስም “እንግዲያውስ ሂድ ፤ አንተም
እንዲሁ አድርግ” አለው ።

### ኢየሱስ በማርታና በማርያም ቤት

38 ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መንገዱን
ቀጥሎ ወደ አንዲት መንደር ደረሰ ፤ በዚያም
ማርታ የምትባል አንዲት ሴት በቤትዋ ተቀበለ
ችው ፤ 39 እርስዋ ማርያም የምትባል እኅት ነበ
ረቻት ፤ ይህች ማርያም በኢየሱስ እግር ሥር
ተቀምጣ ንግግሩን ታደምጥ ነበር ። 40 ማርታ
ግን ምግብ በማዘጋጀት በብርቱ ትደክም ነበር ፤
ስለዚህ ወደ ኢየሱስ ቀርባ “ጌታ ሆይ! ይህች
እኅቴ ሥራውን ሁሉ ለእኔ ትታ ብቻዬን ስደ
ክም እያየህ ዝም ትላለህን? እባክህ እንድታግ
ዘኝ ንገራት” አለችው ።
41 ጌታ ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት ፥
“ማርታ! ማርታ! አንቺ በብዙ ነገር ትጨነቂያ
ለሽ ፤ ትታወኪያለሽም ፤ 42 ነገር ግን ተፈላጊው
አንድ ነገር ብቻ ነው ፤ ማርያም የሚሻለውን
ነገር መርጣለች ፤ እርሱንም ከእርስዋ የሚወስ
ድባት ማንም የለም ።”

10፥19 ፦ መዝ. 91፥13 ። 10፥22 ፦ ዮሐ. 3፥35 ፤ 10፥15 ። 10፥25-28 ፦ ማቴ. 22፥35-40 ፤ ማር. 12፥28-34 ።
10፥27 ፦ ዘሌ. 19፥18 ፤ ዘዳ. 6፥5 ። 10፥28 ፦ ዘሌ. 18፥5 ። 10፥33-34 ፦ 2ዜ.መ. 28፥15 ።
10፥38-39 ፦ ዮሐ. 11፥1 ።

## ምዕራፍ 11

### ኢየሱስ ስለ ጸሎት አስተማረ
(ማቴ. 6፥9-13፡ 7፥7-11)

[1]አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ስፍራ ይጸልይ
ነበር፤ ጸሎቱንም ባበቃ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ
አንዱ “ጌታ ሆይ! ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን
ጸሎት እንዳስተማራቸው አንተም እኛን መጸ
ለይ አስተምረን?” አለው።
[2]ኢየሱስም “ስትጸልዩ እንዲህ በሉ አላ
ቸው፤

‘[በሰማይ የምትኖር] አባታችን ሆይ!
ስምህ ይቀደስ፥
መንግሥትህ ትምጣ፤
[3]የዕለት እንጀራችንን በየቀኑ ስጠን፤
[4]እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥
በደላችንን ይቅር በልልን፥
ወደ ፈተናም አታግባን።’ ”

[5]ቀጥሎም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ
አላቸው፥ “ለምሳሌ ከእናንተ አንዱ ወዳጅ
ይኖረዋል፤ እርሱም በእኩለ ሌሊት ወደዚያ
ወደ ወዳጁ ቤት ሄዶ ‘ወዳጄ ሆይ! እባክህ
ሦስት እንጀራ አበድረኝ፤ [6]ወዳጄ የሆነ አንድ
ሰው ከሩቅ መንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት
ምንም ምግብ የለኝም’ ቢለው፥ [7]ታዲያ ያ
ወዳጁ ከውስጥ ሆኖ ‘እባክህ አታስቸግረኝ፤ በሩ
ተቈልፎአል፤ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ተኝ
ተዋል፤ ስለዚህ ተነሥቼ የፈለግኸውን እንጀራ
ልሰጥህ አልችልም’ ይለዋልን? [8]ምንም እንኳ
ስለ ወዳጅነቱ ተነሥቶ ሊሰጠው ባይፈልግም፥
ስለነዘነዘው ተነሥቶ የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሰ
ጠዋል፥ እላችኋለሁ።
[9]“ስለዚህ እኔም እናንተን የምላችሁ ይህን
ነው፥ ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላ
ችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤
[10]ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚ
ፈልግም ያገኛል፤ መዝጊያ ለሚያንኳኳም ይከ
ፈትለታል። [[11]ከእናንተስ አባት ሆኖ ልጁ ዳቦ
ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ማን ነው?]
ዓሣስ ቢለምነው እባብ ይሰጠዋልን? [12]ወይስ
እንቍላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? [13]እና
ንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም
ነገር መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ የሚኖር
አባታችሁማ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እን
ዴት አብልጦ አይሰጣቸውም!”

### ኢየሱስና ብዔልዜቡል
(ማቴ. 12፥22-30፡ ማር. 3፥20-27)

[14]አንድ ቀን ኢየሱስ የማያናግር ጋኔን ከአ
ንድ ድዳ ሰው ያስወጣ ነበር፤ ጋኔኑም በወጣ
ጊዜ ድዳው ሰው መናገር ጀመረ፤ ሕዝቡም
በዚህ ነገር እጅግ ተደነቁ። [15]አንዳንዶች ግን
“አጋንንትን የሚያስወጣው የአጋንንት አለቃ
በሆነው በብዔልዜቡል ነው” አሉ።
[16]ሌሎች ደግሞ ሊፈትኑት ፈልገው ከሰማይ
አንድ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።
[17]ኢየሱስ ግን አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው፥ “አንድ መንግሥት ተከፍሎ እርስ በርስ
የሚለያይና የሚጋጭ ከሆነ ያ መንግሥት ይጠ
ፋል፤ እንዲሁም አንድ ቤተሰብ እርስ በርሱ
ከተለያየ ይወድቃል። [18]ስለዚህ የሰይጣን መን
ግሥት እርስ በርሱ የሚለያይና የሚጋጭ ከሆነ
እንዴት ጸንቶ መቆም ይችላል? እናንተ ግን
‘እርሱ አጋንንትን የሚያስወጣ በብዔልዜቡል
ነው’ ትሉኛላችሁ። [19]ታዲያ እኔ አጋንንትን
በብዔልዜቡል የማስወጣ ከሆንሁ ልጆቻችሁስ
በማን ያስወጡአቸዋል? ስለዚህ የገዛ ልጆቻችሁ
እንኳ ይፈርዱባችኋል። [20]እንግዲህ እኔ አጋን
ትን በእግዚአብሔር ኀይል የማስወጣ ከሆነ፥
የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መምጣ
ትዋን ዕወቁ።
[21]“አንድ ኀይለኛ ሰው የጦር መሣሪያ ይዞ
ቤቱን የሚጠብቅ ከሆነ ንብረቱ አይዘረፍም፤
[22]ነገር ግን ከእርሱ የበለጠ ኀይለኛ ሰው
መጥቶ ካሸነፈው የተማመነበትን የጦር መሣሪያ
ይወስድበታል ንብረቱንም ሁሉ ዘርፎ ያካፍ
ላል።
[23]“ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ እኔን ይቃወ
ማል፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል።

### የርኩስ መንፈስ በሰው ውስጥ ተመልሶ መግባት
(ማቴ. 12፥43-45)

[24]“ርኩስ መንፈስ ከሰው ውስጥ በወጣ ጊዜ
የሚያርፍበት ቦታ በመፈለግ ውሃ በሌለበት በደ
ረቅ ምድር ሁሉ ይዞራል፤ የሚያርፍበት ቦታ
ካላገኘ ግን ‘ወደወጣሁበት ቤቴ ተመልሼ
ልሂድ’ ይላል። [25]ስለዚህ ተመልሶ ሲመጣ ጸድ
ቶና ተዘጋጅቶ ያገኘዋል። [26]ከዚህ በኋላ ሄዶ
ከእርሱ ይብስ የከፉ ሌሎች ሰባት አጋንንት ይዞ
ይመጣል፤ ቀድሞ እርሱ በነበረበት ቤትም ገብ
ተው በዚያ ይኖራሉ፤ የዚያም ሰው የመጨረሻ
ሁኔታ ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ ይሆናል።”

### እውነተኛ ደስታ

[27]ኢየሱስ ይህን በሚናገርበት ጊዜ አንዲት
ሴት ከሕዝቡ መካከል ድምፅዋን ከፍ አድርጋ
“አንተን ወልዳ ያጠባች እናት እንዴት የተባረ
ከች ናት” አለች።
[28]ኢየሱስ ግን “የተባረኩስ የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት
ናቸው” አላት።

11፥15 ፦ ማቴ. 9፥34፡ 10፥25። 11፥16 ፦ ማቴ. 12፥38፡ 16፥1፡ ማር. 8፥11። 11፥23 ፦ ማር. 9፥40።



### የዮናስ ምልክትነት
(ማቴ. 12፥38-42)

[29]ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው በተሰበ
ሰቡ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “የዚህ ዘመን
ሰዎች እንዴት ክፉዎች ናቸው፤ ምልክት ለማ
የት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምል
ክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጣቸውም።
[30]ነቢዩ ዮናስ ለነነዌ ከተማ ሰዎች ምልክት
እንደነበረ፥ እንዲሁም የሰው ልጅ ለዚህ ዘመን
ሰዎች ምልክት ይሆናል። [31]የደቡብ ንግሥት
በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን ሰዎች ጋር ተነሥታ
በእነርሱ ላይ ትፈርዳለች፤ ምክንያቱም እርስዋ
የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከዓለም ዳርቻ
መጥታለች፤ ነገር ግን እነሆ ከሰሎሞን የሚበ
ልጥ እዚህ አለ! [32]እንዲሁም የነነዌ ከተማ
ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን ሰዎች ጋር ተነ
ሥተው በእነርሱ ላይ ይፈርዱባቸዋል፤ ምክንያ
ቱም የነነዌ ሰዎች የዮናስን ስብከት በሰሙ ጊዜ
በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሓ ገብተዋል፤
ነገር ግን እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ!”

### ኢየሱስ ስለ ብርሃን አስተማረ
(ማቴ. 5፥15፡ 6፥22-23)

[33]ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “መብ
ራት አብርቶ በስውር የሚያስቀምጠው፥ ወይም
እንቅብ የሚደፋበት ማንም የለም፤ ይልቅስ
ሰዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ እንዲታያቸው ከፍ
አድርጎ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል። [34]የሰውነ
ትህ መብራት ዐይንህ ነው፤ ዐይንህ ጤናማ
ከሆነ ሰውነትህ ሁሉ በብርሃን የተሞላ ይሆ
ናል፤ ዐይንህ ግን ታማሚ ከሆነ ሰውነትህ ሁሉ
ጨለማ ይሆናል። [35]ስለዚህ በአንተ ያለው ብር
ሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ። [36]እንግዲህ
ሰውነትህ ሁሉ ምንም ጨለማ ሳይኖርበት በብር
ሃን የተሞላ ከሆነ ሁለመናህ ደማቅ መብራት
ለአንተ እንደሚያንጸባርቅ ዐይነት ይሆናል።”

### ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን ተወቀሱ
(ማቴ. 23፥1-36፡ ማር. 12፥38-40)

[37]ኢየሱስ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ አንድ
ፈሪሳዊ ምሳ ጋበዘው፤ ወደ ፈሪሳዊው ቤት
ገብቶ ምሳ ለመብላት በማእድ ተቀመጠ።
[38]ኢየሱስ ምሳ ከመብላቱ በፊት እጁን ስላልታ
ጠበ ፈሪሳዊው ተደነቀ። [39]ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ
እንዲህ አለው፥ “እናንተ ፈሪሳውያን የብርጭቆ
ውንና የሳሕኑን ውጪውን አጥርታችሁ ታጥባላ
ችሁ፤ በውስጣችሁ ግን ቅሚያና ክፋት ሞልቶ
ባችኋል። [40]እናንተ ሞኞች፤ የውጪውን የፈ
ጠረ አምላክ የውስጡንስ አልፈጠረምን? [41]በብ
ርጭቆአችሁና በሳሕናችሁ ያለውን ለድኾች
ስጡ፤ ከዚህ በኋላ ሁሉ ነገር ንጹሕ ይሆን
ላችኋል።
[42]“እናንተ ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ምክንያ
ቱም በአንድ በኩል ከአዝሙድና ከጤናዳም፤
ከልዩ ልዩ ጥቃቅን አትክልቶችም ዐሥራት ታወ
ጣላችሁ፤ በሌላ በኩል ግን እውነተኛ ፍርድንና
የእግዚአብሔርን መውደድ ትተዋላችሁ፤ ያንን
ስታደርጉ፥ ይህንን መተው አልነበረባችሁም።
[43]“እናንተ ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ምክንያ
ቱም በምኵራብ ውስጥ በክብር ወንበር ላይ
መቀመጥ ትወዳላችሁ፤ እንዲሁም በአደባባ
ይና በገበያ ቦታ ሰው ሁሉ እጅ እንዲነሣችሁ
ትፈልጋላችሁ። [44]ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄ
ዱበትን ምልክት የሌለው መቃብር ስለምትመ
ስሉ ወዮላችሁ!”
[45]ከሕግ መምህራንም አንዱ ኢየሱስን
“መምህር ሆይ! ይህንን ስትል እኛንም መስደ
ብህ ነው እኮ!” አለው።
[46]ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “እናንተም የሕግ
መምህራን ወዮላችሁ! በሰው ላይ ከባድ ሸክም
ትጭናላችሁ፤ እናንተ ግን ሸክሙን በጣታችሁ
እንኳ አትነኩትም። [47]እንዲሁም አባቶቻችሁ
ለገደሉአቸው ነቢያት መቃብሮቻቸውን በማስ
ጌጥ የምትሠሩ ስለሆናችሁ ወዮላችሁ! [48]እንግ
ዲህ አባቶቻችሁ ለገደሉአቸው ነቢያት መቃብ
ሮቻቸውን በማሠራታችሁ እናንተ የክፉ ሥራ
ቸው ተባባሪዎችና ምስክሮች ናችሁ። [49]በዚ
ህም ምክንያት የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ
ትላለች፥ ‘ነቢያትንና ሐዋርያትን ወደ እነርሱ
እልካለሁ፤ አንዳንዶችን ይገድላሉ፤ የቀሩት
ንም ያሳድዳሉ፤ [50]ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ
ስለ ፈሰሰው የነቢያት ደም የዚህ ዘመን ሰዎች
በፍርድ ይጠየቁበታል።’ [51]በእርግጥ እነግ
ራችኋለሁ፥ ከአቤል ጀምሮ በመሠዊያውና
በቤተ መቅደሱ መካከል እስከተገደለው እስከ
ዘካርያስ ድረስ፥ ስለፈሰሰው የነቢያት ደም
የዚህ ዘመን ሰዎች በፍርድ ይጠየቁበታል።
[52]“እናንተ የሕግ መምህራን ወዮላችሁ!
የዕውቀት በር መክፈቻ የሆነውን የእውነት
ቍልፍ ይዛችኋል፤ ነገር ግን እናንተ ራሳችሁ
አልገባችሁበትም፤ መግባት የሚፈልጉትንም
እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።”
[53]ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ሊሄድ በተነሣ ጊዜ
የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ይቃወሙ
ትና ብዙ ጥያቄም ያቀርቡለት ጀመር፤ [54]ይህ
ንንም ያደረጉት በንግግሩ ሊያጠምዱት ፈል
ገው ነው።

11፥29 ፦ ማቴ. 16፥4፡ ማር. 8፥12። 11፥30 ፦ ዮናስ 3፥4። 11፥31 ፦ 1ነገ. 10፥1-10፡ 2ዜ.መ. 9፥1-12።
11፥32 ፦ ዮናስ 3፥5። 11፥33 ፦ ማቴ. 5፥15፡ ማር. 4፥21፡ ሉቃ. 8፥16። 11፥42 ፦ ዘሌ. 27፥30።
11፥51 ፦ ዘፍ. 4፥8፡ 2ዜ.መ. 24፥20-21።

## ምዕራፍ 12

### ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ግብዝነት ተጠንቀቁ አለ
(ማቴ. 10፥26-27)

1 በዚያን ጊዜ በብዙ ሺ የሚቈጠሩ ሰዎች
ተሰበሰቡ፤ ከብዛታቸውም የተነሣ እርስ በርሳ
ቸው እየተጋፉ ይረጋገጡ ነበር፤ ኢየሱስም በቅ
ድሚያ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ይል ጀመር፥
"ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠንቀቁ፤ ይኸውም ከግ
ብዝነታቸው ራቁ ማለቴ ነው። 2 የተሸፈነ ሳይገ
ለጥ አይቀርም፤ የተሰወረውም ሳይታወቅ አይቀ
ርም። 3 ስለዚህ በጨለማ የተናገራችሁት ሁሉ
በብርሃን ይሰማል፤ በዝግ ቤት ውስጥ በሹክሹ
ክታ በጆሮ የተናገራችሁትም በሰገነት ላይ
በይፋ ይነገራል።

### ማንን መፍራት እንደሚገባ
(ማቴ. 10፥28-31)

4 "ለእናንተ ለወዳጆቼ እንዲህ እላችኋለሁ፥
ሥጋን ከመግደል በቀር ሌላ ምንም ማድረግ
የማይችሉትን አትፍሩ፤ 5 ነገር ግን ማንን መፍ
ራት እንደሚገባችሁ እነግራችኋለሁ፤ ይኸውም
ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን
ያለውን እግዚአብሔርን ነው፤ አዎ! እርሱን
ብቻ ፍሩ እላችኋለሁ።
6 "አምስት ድንቢጦች በዐሥር ሳንቲም
ይሸጡ የለምን? ከእነርሱ አንድዋ እንኳ በእግ
ዚአብሔር ፊት የተረሳች አይደለችም። 7 የእናን
ተም የራሳችሁ ጠጕር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ
ነው፤ ስለዚህ አትፍሩ፤ እናንተ እኮ ከብዙ
ድንቢጦች ትበልጣላችሁ።"

### ስለ ክርስቶስ መመስከር ይገባል
(ማቴ. 10፥32-33፤ 12፥32፤ 10፥19-20)

8 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ "ሳያፍር
በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔም ደግሞ በእግ
ዚአብሔር መላእክት ፊት እመሰክርለታለሁ
እላችኋለሁ። 9 በሰው ፊት የሚክደኝን እኔም
ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት እክደዋ
ለሁ።
10 "በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር
ቢኖር በደሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ
ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ቢኖር ግን
በደሉ ይቅር አይባልለትም።
11 "ሰዎች በየምኵራቡ ሲወስዱዋችሁ፥ በገ
ዥዎችና በባለሥልጣኖች ፊት ለፍርድ ሲያቀር
ቡአችሁ 'ምን እንመልሳለን? እንዴትስ እንናገ
ራለን?' ብላችሁ አትጨነቁ። 12 ምክንያቱም
ልትናገሩት የሚገባችሁን በዚያን ሰዓት መንፈስ
ቅዱስ ይነግራችኋል።"

### የሀብታሙ ሰው ሞኝነት

13 ከሕዝቡም መካከል አንድ ሰው ኢየሱስን
"መምህር ሆይ! አባታችን ያወረሰንን ርስት እን
ዲያካፍለኝ እባክህ ለወንድሜ ንገረው" አለው።
14 ኢየሱስ ግን "አንተ ሰው፥ በእናንተ መካ
ከል ፈራጅ እንድሆንና ርስት እንዳካፍል ማን
ሾመኝ?" ሲል መለሰለት። 15 ቀጥሎ ለሁሉም
እንዲህ አላቸው፥ "የሰው ሕይወት በሀብት
ብዛት አይደለም፤ ስለዚህ ከመጐምዠትና ከስግ
ብግብነት ተጠበቁ፤ ተጠንቀቁም።"
16 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ይህን ምሳሌ እን
ዲህ ሲል ነገራቸው፥ "እርሻው ብዙ ሰብል
ያስገኘለት አንድ ሀብታም ሰው ነበር፤ 17 እር
ሱም በአሳቡ፥ 'ይህን ሁሉ እህል የማከማችበት
ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ?' እያለ ያሰላስል
ነበር። 18 እንዲህም አለ፥ 'የማደርገው ይህ
ነው፤ ጐተራዎቼን ሁሉ አፈርስና ሌሎች ትል
ልቅ ጐተራዎች እሠራለሁ፤ በዚያ እህሌንና
ንብረቴን ሁሉ ሰብስቤ አከማቻለሁ። 19 ከዚህም
በኋላ ራሴን፦ እነሆ ለብዙ ዓመት የሚበቃህ
ብዙ ሀብት አለህ፤ እንግዲህ ዕረፍት በማድረግ
ተዝናና፥ ብላ ጠጣ፥ ደስ ይበልህ! እላለሁ'
አለ። 20 እግዚአብሔር ግን 'አንተ ሞኝ! ዛሬ
በዚህች ሌሊት ነፍስህ ከአንተ ትወሰዳለች፤
ታዲያ ይህ ያከማቸኸው ሀብት ሁሉ ለማን ይሆ
ናል?' አለው።
21 "ለራሱ በምድር ላይ ሀብትን የሚያከ
ማች፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ድኻ የሆነ
ሰው እንዲሁ ይሆናል።"

### እምነትን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ
(ማቴ. 6፥25-34)

22 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ
እንዲህ አለ፥ "ስለዚህ 'ምን እንበላለን? ምንስ
እንለብሳለን?' በማለት ስለኑሮአችሁ አትጨነቁ
እላችኋለሁ። 23 ምክንያቱም ከምግብ ሕይ
ወት፥ ከልብስም ሰውነት ይበልጣል። 24 እስቲ
ቍራዎችን ተመልከቱ፥ እነርሱ አይዘሩም
ወይም አያጭዱም፤ የእህል ማከማቻ ቦታ
ወይም ጐተራ የላቸውም፤ ይሁን እንጂ እግዚአ
ብሔር ይመግባቸዋል፤ እናንተማ ከወፎች የም
ትበልጡ ናችሁ እኮ። 25 ለመሆኑ ከእናንተ በማ
ሰብና በመጨነቅ በዕድሜው ላይ አንድ ቀን5*
መጨመር የሚችል ማን ነው? 26 እንግዲህ ይህን
ትንሹን ነገር እንኳ ማድረግ የማትችሉ ከሆና
ችሁ፥ ስለምን በሌላው ነገር ትጨነቃላችሁ?

5* 12፥25 በዕድሜው ላይ አንድ ቀን፦ በአንዳንድ ትርጒም "በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ" የሚል ይገኛል።
12፥1፦ ማቴ. 16፥6፤ ማር. 8፥15። 12፥2፦ ማር. 4፥22፤ ሉቃ. 8፥17። 12፥10፦ ማቴ. 12፥32፤ ማር. 3፥29።
12፥11-12፦ ማቴ. 10፥19-20፤ ማር. 13፥11፤ ሉቃ. 21፥14-15።



27 የዱር አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ እስቲ
ተመልከቱ፤ እነርሱ በሥራ አይደክሙም፤ አይ
ፈትሉም፤ ይሁን እንጂ ሰሎሞን እንኳ በዚያ
ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አንዷቱ እንዲህ
ያጌጠ ልብስ አልለበሰም። 28 ታዲያ እግዚአብ
ሔር ዛሬ ታይቶ ነገ በእሳት ውስጥ የሚጣለውን
የዱር ሣር እንዲህ አስጊጦ የሚያለብሰው ከሆነ፥
እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እናንተንማ እን
ዴት አብልጦ አያለብሳችሁም?
29 "ስለዚህ 'ምን እንበላለን፥ ምንስ እንጠጣ
ለን?' እያላችሁ በአሳብ አትወዛወዙ። 30 ይህንን
ለማግኘትማ የዚህ ዓለም ሰዎችም ይጨነቁበ
ታል፤ ለእናንተ ግን ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋ
ችሁ የሰማይ አባታችሁ ያውቃል። 31 ይልቅስ
የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤ የሚያስ
ፈልጓችሁም ነገሮች ሁሉ ይጨመሩላችኋል።

### በምድር ላይ ሀብት ማከማቸት አይገባም
(ማቴ. 6፥19-21)

32 "እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ ወገ
ኖቼ አትፍሩ፤ ምክንያቱም የሰማይ አባታችሁ
መንግሥትን ሊሰጣችሁ ፈቅዶአል። 33 ያላች
ሁን ሁሉ ሸጣችሁ ገንዘቡን ለድኾች ስጡ፤
የማያረጅ የገንዘብ ቦርሳም አዘጋጅታችሁ ገንዘባ
ችሁን ሌባ በማይደርስበት፥ ብል በማይበላበትና
ከቶም በማያልቅበት ቦታ፥ በመንግሥተ ሰማይ
አስቀምጡ። 34 ምክንያቱም ገንዘባችሁ ባለበት
ቦታ ልባችሁም በዚያው ይሆናል።"

### የአገልጋዮች ትጋት

35 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ "ባውር
ታጥቃችሁ ሁልጊዜ ለሥራ ተዘጋጁ፤ መብራታ
ችሁም የበራ ይሁን። 36 በዚህም አኳኋን ጌታ
ቸው ከሠርግ ቤት መመለሱን የሚጠባበቁ አገል
ጋዮችን ምሰሉ፤ እነርሱ ጌታቸው በድንገት
መጥቶ በሩን በሚያንኳኳበት ጊዜ ፈጥነው ለመ
ክፈት ዝግጁዎች ናቸው። 37 እነዚያ ጌታቸው
ድንገት በመጣ ጊዜ ነቅተው ሲጠብቁ የሚያገ
ኛቸው አገልጋዮች እንዴት የተመሰገኑ ናቸው!
በእውነት እላችኋለሁ፥ እርሱ ባውር ታጥቆ
በማእድ ያስቀምጣቸዋል፤ በማስተናበርም ያገለ
ግላቸዋል። 38 ጌታቸው በእኩለ ሌሊት ወይም
ከእኩለ ሌሊት በኋላ በመጣ ጊዜ ነቅተውና
ተግተው ሲጠብቁት የሚያገኛቸው አገልጋዮች
የተመሰገኑ ናቸው! 39 ደግሞም ይህንን ዕወቁ፤
ሰው ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ለይቶ ቢያውቅ
ኖሮ ሌባው ቤቱን ቈፍሮ ሲገባ አይተውም
ነበር። 40 የሰው ልጅ ባላሰባችሁበት ሰዓት በድ
ንገት ይመጣል፤ ስለዚህ እናንተም ተዘጋጅታ
ችሁ ጠብቁ።"

### የደጉና የክፉው አገልጋይ ምሳሌ
(ማቴ. 24፥45-51)

41 ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ! ይህን ምሳሌ የም
ትናገረው ለእኛ ነውን? ወይስ ለሁሉም ነው?"
ሲል ኢየሱስን ጠየቀው።
42 ጌታ ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፥
"ታዲያ ቤተሰቦቹን በደንብ እንዲያስተዳድርለ
ትና ለአገልጋዮቹም ምግባቸውን በወቅቱ እንዲ
ሰጣቸው ጌታው የሚሾመው ታማኝና ብልህ
መጋቢ ማን ነው? 43 ጌታው ከሄደበት ሲመለስ
ልክ እንደታዘዘው ሲፈጽም የሚያገኘው አገል
ጋይ እንዴት የተመሰገነ ነው! 44 በእውነት
እላችኋለሁ፥ ጌታው ያን አገልጋይ የንብረቱ
ሁሉ ኀላፊ አድርጎ ይሾመዋል። 45 ነገር ግን ያ
አገልጋይ 'ጌታዬ ቶሎ አይመጣም፥ ይዘገያል'
ብሎ በማሰብ እየበላ፥ እየጠጣ፥ እየሰከረም
ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮችን መምታት ይጀም
ራል። 46 ይሁን እንጂ ጌታው ባልታሰበበት
ቀንና ባልተጠበቀበት ሰዓት በድንገት ይመ
ጣል፤ አገልጋዩንም በብርቱ ይቀጣዋል፤ ዕድ
ሉም ከወስላቶች ጋር እንዲሆን ያደርጋል።
47 "የጌታውን ፈቃድ እያወቀ ያልተዘጋጀ፥
ወይም የጌታውን ትእዛዝ ያልፈጸመ አገልጋይ
በብርቱ ይቀጣል። 48 ነገር ግን የጌታውን
ፈቃድ ባለማወቅ ቅጣት የሚያመጣበትን ነገር
አድርጎ ቢገኝ ቅጣቱ ይቀልለታል፤ ምክንያ
ቱም ብዙ ከተሰጠው ሰው፥ ብዙ ይፈለግበ
ታል፤ ብዙ ዐደራም ከተሰጠው ሰው፥ ብዙ
ይጠበቅበታል።"

### ሁሉን ነገር ትቶ ኢየሱስን መከተል
(ማቴ. 10፥34-36)

49 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ "እነሆ
እኔ በምድር ላይ እሳት አምጥቻለሁ፤ ታዲያ
ቶሎ ቢቀጣጠልልኝ እንዴት በወደድሁ ነበር!
50 ነገር ግን እኔ የምጠመቀው የመከራ ጥምቀት
አለኝ፤ እርሱም እስኪፈጸም ድረስ ዕረፍት የለ
ኝም። 51 እኔ በምድር ላይ ሰላምን ያመጣሁ
ይመስላችኋልን? እኔስ ያመጣሁት መለያየትን
እንጂ ሰላምን አይደለም፥ እላችኋለሁ። 52 ከአ
ሁን ጀምሮ በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ ያሉ አም
ስት ሰዎች ይለያያሉ፤ ሦስቱ በሁለቱ ላይ፥
ሁለቱም በሦስቱ ላይ ተነሥተው ይጣላሉ።
53 አባት በልጁ ላይ፥ ልጅም በአባቱ ላይ፥
እናት በሴት ልጅዋ ላይ፥ ሴት ልጅም በእና
ትዋ ላይ፥ ዐማት በምራትዋ ላይ፥ ምራትም
በዐማትዋ ላይ እንዲሁ በጥል ተነሣሥተው ይለ
ያያሉ።"

12፥27፦ 1ነገ. 10፥4-7፤ 2ዜ.መ. 9፥3-6። 12፥35፦ ማቴ. 25፥1-13። 12፥36፦ ማር. 13፥34-36።
12፥39-40፦ ማቴ. 24፥43-44። 12፥50፦ ማር. 10፥38። 12፥53፦ ሚክ. 7፥6።

### የጊዜውን ሁኔታ ስለማወቅ
(ማቴ. 16፥2-3)

54 ደግሞም ኢየሱስ ለሕዝቡ እንዲህ አለ፥
“ደመና በስተ ምዕራብ በኩል ሲታዩ ወዲያውኑ
‘እንሆ ዛሬ ሊዘንም ነው!’ ትላላችሁ፤ በእርግ
ጥም ይዘንማል። 55 እንዲሁም ነፋስ በስተ
ደቡብ በኩል በሚነፍስበት ጊዜ ‘ዛሬ ሙቀት
ይሆናል’ ትላላችሁ፥ በእርግጥም ይሆናል።
56 እናንተ ግብዞች የምድሩንና የሰማዩን መልክ
በመመልከት የሚሆነውን ታውቃላችሁ፤ ታዲያ
በዚህ በአሁኑ ዘመን የሚሆነውን ለምን አታው
ቁም?”

### ከባላጋራ ጋር ስለ መስማማት
(ማቴ. 5፥25-26)

57 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “እንግ
ዲህ ስለምን እናንተ ራሳችሁ ትክክለኛውን
ነገር ፀውቃችሁ አትፈርዱም? 58 ባላጋራህ ከስ
ሶህ ወደ ፍርድ ቤት በሚወስድህ ጊዜ ገና በመ
ንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ለመስማማት ተጣ
ጣር፤ አለበለዚያ እርሱ ወደ ዳኛ ጐትቶ ይወስ
ድሃል፤ ዳኛውም ለፖሊስ አሳልፎ ይሰጥሃል፤
ፖሊሱም ወደ እስር ቤት ያገባሃል። 59 መቀጮ
ህን ሁሉ ጨርሰህ ሳትከፍል ከእስር ቤት መው
ጣት እንደማትችልም እነግርሃለሁ።”

## ምዕራፍ 13
### ንስሐ የማይገባ ሁሉ ይጠፋል

1 በዚያን ጊዜ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው
“የገሊላ ሰዎች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
በሚያቀርቡበት ጊዜ ጲላጦስ ገደላቸው፤ ደማ
ቸውም ከመሥዋዕታቸው ጋር ተደባለቀ” ሲሉ
አወሩለት። 2 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላ
ቸው፥ “ታዲያ፥ እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ
ሁሉ ጥፋት የደረሰባቸው፥ ከሌሎቹ የገሊላ
ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ኃጢአተኞች ስለነበሩ
ይመስላችኋልን? 3 አይደለም! በኃጢአታችሁ
ተጸጽታችሁ ንስሐ ባትገቡ፥ እናንተም እንደእ
ነርሱ ትጠፋላችሁ እላችኋለሁ። 4 በሰሊሆም
ግንብ ተደርምሶባቸው ስለሞቱት ዐሥራ ስም
ንት ሰዎች ምን ታስባላችሁ? እነርሱ በኢየሩሳ
ሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ የባሱ ኃጢአተ
ኞች ይመስሉአችኋልን? 5 አይደለም! በኃጢአ
ታችሁ ተጸጽታችሁ ንስሓ ባትገቡ እናንተም
እንደእነርሱ ትጠፋላችሁ እላችኋለሁ።”

### የማታፈራ የበለስ ዛፍ ምሳሌ

6 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራ
ቸው፥ “አንድ ሰው በአትክልቱ ውስጥ የተተከ
ለች አንዲት የበለስ ዛፍ ነበረችው፤ ከዚያች የበ
ለስ ዛፍ ፍሬ አገኛለሁ ብሎ ቢሄድ ምንም ሳያ
ገኝ ቀረ። 7 ስለዚህ አትክልተኛውን ‘እነሆ ከዚ
ህች የበለስ ዛፍ ፍሬ ለማግኘት ሦስት ዓመት
ሙሉ ተመላለስሁ፤ ግን ምንም ፍሬ አላገኘሁ
ባትም፤ አሁንስ ቍረጣት፤ ስለምን የአትክል
ቱን ቦታ በከንቱ ይዛ መሬት ታበላሻለች?’
አለው። 8 አትክልተኛው ግን እንዲህ ሲል መለ
ሰለት፥ ‘ጌታዬ ሆይ! እስቲ ለዚህ ዓመት
ደግሞ ተዋት፤ ዙሪያዋን ኰትኵቼ ማዳበሪያ
አደርግላታለሁ፤ 9 ለመጪው ዓመት ፍሬ ብት
ሰጥ መልካም ነው፤ አለበለዚያ ግን ትቈረጣ
ለች።’”

### ኢየሱስ አንዲት ጐባጣ ሴት
### በሰንበት ቀን ፈወሰ

10 ኢየሱስ በሰንበት ቀን በምኵራብ ያስተ
ምር ነበር፤ 11 ከዚያም ከዐሥራ ስምንት ዓመት
ጀምሮርኩስ መንፈስ ያጐበጣት አንዲት ሴት
ነበረች፤ እርስዋ ወገብዋ በመጕበጡ ቀና ለማ
ለት በጭራሽ አትችልም ነበር። 12 ኢየሱስ
ባያት ጊዜ ጠራትና “አንቺ ሴት ከበሽታሽ ተፈ
ውሰሻል” አላት። 13 በእጁም ዳሰሳት፤ ወዲያ
ውም ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም አመ
ሰገነች።
14 ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለፈወሰ የምኵራቡ
አለቃ ተቈጣና ለሕዝቡ “በሳምንት ውስጥ
ሥራ የሚሠራባቸው ስድስት ቀኖች አሉ፤ በእነ
ዚህ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈወሱ፤ በሰንበት
ቀን ግን አይሆንም” ብሎ ተናገረ።
15 ጌታ ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፥
“እናንተ ግብዞች! ከእናንተስ እያንዳንዱ በሰን
በት ቀን በሬውን ከተዘጋበት አውጥቶ ወይም
አህያውን ከታሰረበት ፈትቶ ውሃ ወደሚያጠጣ
በት ቦታ ይወስደው የለምን? 16 እነሆ የአብር
ሃም ዘር የሆነች ይህች ሴት ዐሥራ ስምንት
ዓመት ሙሉ በሰይጣን ታስራ ስትሠቃይ ኖራ
ለች፤ ታዲያ እርስዋ ታስራ ከምትሠቃይበት
በሽታ በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን?”
17 በዚህም ንግግሩ ኢየሱስ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ
አሳፈራቸው፤ ሕዝቡ ግን ኢየሱስ ባደረገው
ድንቅ ነገር ሁሉ ተደሰቱ።

### የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ
(ማቴ. 13፥31-32፤ ማር. 4፥30-32)

18 ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “የእግዚአብሔር
መንግሥት በምን ምሳሌ ትገለጻለች? ወይስ
ከምን ጋር አነጻጽራታለሁ? 19 አንድ ሰው በአ
ትክልቱ ውስጥ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመስላ
ለች፤ እርስዋ አድጋ ዛፍ ታህላለች፤ ወፎችም
በቅርንጫፎችዋ ላይ ጎጆአቸውን ይሠራሉ።”

13፥14 ፦ ዘጸ. 20፥9-10፤ ዘዳ. 5፥13-14።



### የእርሾው ምሳሌ
(ማቴ. 13፥33)

20 ኢየሱስ እንደገና እንዲህ አለ፥ “የእግዚአ
ብሔርን መንግሥት ከምን ጋር አነጻጽራታለሁ?
21 የእግዚአብሔር መንግሥት አንዲት ሴት
ሊጡ በሙሉ እንዲቦካ በሦስት መስፈሪያ
ዱቄት ውስጥ የለወሰችውን እርሾ ትመስላ
ለች።”

### ስለ ጠባብዋ በር
(ማቴ. 7፥13-14፡21-23)

22 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
ሲሄድ ሳለ፥ በየከተማውና በየገጠሩ እያስተማረ
ያልፍ ነበር። 23 በዚያን ጊዜ አንድ ሰው “ጌታ
ሆይ! የሚድኑ ጥቂቶች ሰዎች ናቸውን?” ሲል
ጠየቀው፤
ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥ 24 “በጠ
ባብዋ በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ በዚህችም በር
መግባት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን
መግባት አይችሉም እላችኋለሁ። 25 የቤቱ ጌታ
ተነሥቶ በሩን ይዘጋዋል፤ እናንተም በደጅ
ቆማችሁ በሩን በማንኳኳት ‘ጌታ ሆይ! እባክህ
ክፈትልን!’ ማለት ትጀምራላችሁ፤ እርሱም
‘ከየት እንደመጣችሁ አላውቅም!’ ሲል ይመል
ስላችኋል። 26 በዚያን ጊዜ እናንተ ‘ከአንተ ጋር
አብረን በልተናል፤ አብረን ጠጥተናል፤ በአደባ
ባያችንም አስተምረሃል እኮ!’ ትሉታላችሁ።
27 እርሱም እንደገና ‘ከየት እንደመጣችሁ አላ
ውቅም! እናንተ ዐመፀኞች ሁሉ ከእኔ ራቁ!’
ይላችኋል። 28 አብርሃምን፥ ይስሐቅን፥ ያዕቆ
ብን ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግ
ሥት ታዩአቸዋላችሁ፤ እናንተ ግን በውጪ
ተጥላችሁ ስትቀሩ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆ
ንባችኋል። 29 ብዙ ሰዎች ከምሥራቅና ከምዕ
ራብ፥ ከሰሜንና ከደቡብ ይመጣሉ፤ በእግዚአ
ብሔር መንግሥትም በማእድ ይቀመጣሉ።
30 ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ፤ ፊተኞ
ችም ኋለኞች ይሆናሉ።”

### ኢየሱስ ኢየሩሳሌምን ወቀሰ
(ማቴ. 23፥37-39)

31 በዚያን ጊዜ አንዳንድ ፈሪሳውያን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው “ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋ
ልና ከዚህ ወጥተህ ወደ ሌላ ስፍራ ሂድ”
አሉት።
32 ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፥ “ሄዳችሁ
ያንን ቀበሮ ‘ዛሬና ነገ አጋንንትን አስወጣለሁ፤
በሽተኞችን እፈውሳለሁ፤ በሦስተኛው ቀንም
ሥራዬን እጨርሳለሁ’ ይላል በሉት። 33 ይሁን
እንጂ ዛሬና ነገ ከነገ ወዲያም መንገዴን ወደ
ኢየሩሳሌም መቀጠል አለብኝ፤ ምክንያቱም
ነቢይ ከኢየሩሳሌም በቀር በሌላ ቦታ መሞት
አይገባውም።
34 “ኢየሩሳሌም! ኢየሩሳሌም! አንቺ ነቢያ
ትን ትገድያለሽ፤ ወደ አንቺ የተላኩትንም
መልእክተኞች በድንጋይ ትወግሪያለሽ፤ ዶሮ
ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበ
ስብ፥ እኔም ስንት ጊዜ ልጆችሽን መሰብሰብ
ፈለግሁ፤ እናንተ ግን እምቢ አላችሁ። 35 ስለ
ዚህ ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀራል፤ እናንተ ‘በእ
ግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው’ እስክ
ትሉ ድረስ ከቶ አታዩኝም እላችኋለሁ።”

## ምዕራፍ 14
### ኢየሱስ እንደገና አንድ በሽተኛ
### በሰንበት ቀን ፈወሰ

1 በሰንበት ቀን ኢየሱስ ከፈሪሳውያን አለቆች
ወደ አንዱ ቤት ምሳ ሊበላ ገባ፤ ፈሪሳውያን
እርሱ የሚያደርገውን ለማየት አተኵረው ይመለ
ከቱት ነበር። 2 በዚያን ጊዜ በሕመም ምክንያት
መላ ሰውነቱ ያበጠበት አንድ ሰው በኢየሱስ
ፊት ነበር። 3 ኢየሱስም የሙሴ ሕግ መምህራን
ንና ፈሪሳውያንን “በሰንበት ቀን መፈወስ በሕግ
ተፈቅዶአልን፥ ወይስ አልተፈቀደም?” ሲል
ጠየቃቸው።
4 እነርሱ ግን ምንም ሳይመልሱ ዝም አሉ፤
ኢየሱስ የታመመውን ሰው ይዞ ፈወሰውና አሰና
በተው። 5 ቀጥሎም ኢየሱስ “ከእናንተ በሰንበት
ቀን ልጁ ወይም በሬው በጕድጓድ ውስጥ ቢወ
ድቅበት ወዲያውኑ የማያወጣው ማን ነው?”
ሲል ጠየቃቸው። 6 እነርሱ ግን ምንም መልስ
መስጠት አልቻሉም።

### ስለ ትሕትናና ስለ መስተንግዶ

7 ኢየሱስ ለግብዣ የተጠሩ ሰዎች የከበሬታ
ስፍራ ለመያዝ ሲሽቀዳደሙ አየ፤ ስለዚህ ይህን
ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፥ 8 “አንድ ሰው
ለሠርግ ግብዣ ሲጠራህ፥ ተሽቀዳድመህ በክ
ብር ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ የበ
ለጠ ክብር ያለው ሰው ተጠርቶ ይሆናል፤
9 ታዲያ ሁለታችሁንም የጋበዛችሁ ሰው፥ ወደ
አንተ መጥቶ ‘ይህን ስፍራ ለዚህ ሰው ልቀቅ
ለት’ ይልሃል፤ ያን ጊዜ በታላቅ ሐፍረት ወደ
ዝቅተኛው ቦታ ወርደህ ትቀመጣለህ። 10 ነገር
ግን ለግብዣ ስትጠራ ሄደህ በዝቅተኛ ስፍራ
ተቀመጥ፤ በዚያን ጊዜ የጠራህ ሰው ወደ አንተ
መጥቶ ‘ወዳጄ ሆይ! ወደ ከፍተኛው ስፍራ

13፥27 ፦ መዝ. 6፥8። 13፥28 ፦ ማቴ. 22፥13፤ 25፥30። 13፥28-29 ፦ ማቴ. 8፥11-12።
13፥30 ፦ ማቴ. 19፥30፤ 20፥16፤ ማር. 10፥31። 13፥35 ፦ መዝ. 118፥26፤ ኤር. 22፥5። 14፥5 ፦ ማቴ. 12፥11።
14፥8-10 ፦ ምሳ. 25፥6-7።

ወጥተህ ተቀመጥ’ ይልሃል፤ ያን ጊዜም በሌ
ሎች ተጋባዦች ሁሉ ፊት ክብር ታገኛለህ።
11 ምክንያቱም ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ
ዝቅ ይላል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ
ይላል።” 12 ኢየሱስ ጋባዡን ሰው ደግሞ እን
ዲህ አለው፣ “የምሳ ወይም የራት ግብዣ በም
ታደርግበት ጊዜ ብድራቸውን ለመመለስ በተራ
ቸው ይጋብዙኛል ብለህ ተስፋ በማድረግ ወዳ
ጆችህን፣ ወንድሞችህን፣ ዘመዶችህን፣ ሀብታ
ሞች ጐረቤቶችህንም አትጥራ፤ 13 ነገር ግን
ግብዣ በምታደርግበት ጊዜ ድኾችን፣ አካለ
ስንኩሎችን፣ ሽባዎችን፣ ዕውሮችንም ጥራ።
14 ይህን ብታደርግ እነርሱ ውለታ ለመክፈል
ስለማይችሉ ትመሰገናለህ። በጻድቃን ትንሣኤ
ጊዜ እግዚአብሔር ይከፍልሃል።”

### የትልቁ ግብዣ ምሳሌ
(ማቴ. 22፥1-10)

15 በማእድ ተቀምጠው ከነበሩት አንዱ ኢየ
ሱስ የተናገረውን ሰምቶ፣ “በእግዚአብሔር
መንግሥት በማእድ መቀመጥ የሚችል እንዴት
የታደለ ነው!” አለ።
16 ኢየሱስ ግን እንዲህ አለው፣ “አንድ ሰው
ትልቅ የራት ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰዎችን
ጠራ፤ 17 የግብዣው ሰዓት በደረሰ ጊዜ ‘እነሆ
ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶአልና ወደ ግብዣ ኑ!’ ብሎ
እንዲነግራቸው ጋባዡ አገልጋዩን ወደ ተጠሩት
ሰዎች ላከው። 18 ነገር ግን እያንዳንዱ ተጋባዥ
ከግብዣው ለመቅረት ምክንያት መፍጠር
ጀመረ፤ አንዱ ‘መሬት ስለገዛሁ ሄጄ ማየት አለ
ብኝ፤ ስለዚህ መምጣት አልችልምና ይቅርታ
አድርግልኝ’ አለው። 19 ሌላው ‘አምስት ጥንድ
በሬዎች ስለገዛሁ እነርሱን መፈተን አለብኝ፤
ስለዚህ መምጣት አልችልምና ይቅርታ አድርግ
ልኝ’ አለ። 20 ሌላው ደግሞ ‘ሚስት አግብቼ
ሙሽራ ስለሆንሁ ልመጣ አልችልም’ አለ።
21 “አገልጋዩም ወደ ቤት ተመልሶ ይህን
ሁሉ ለጌታው ነገረው፤ የቤቱም ጌታ ተቈጥቶ
አገልጋዩን ‘ቶሎ ብለህ ወደ ከተማው ጐዳናዎ
ችና ስላች መንገዶች ሂድ፤ ድኾችን፣ አካለ
ስንኩሎችን፣ ዕውሮችን፣ አንካሶችንም ጠርተህ
ወዲህ አምጣልኝ’ አለው። 22 አገልጋዩም ተመ
ልሶ መጣና ጌታውን ‘ጌታዬ ሆይ! እነሆ ያዘዝ
ኸኝን ሁሉ ፈጽሜአለሁ፤ ሆኖም ገና ትርፍ
ቦታ አለ’ አለው። 23 ስለዚህ የቤቱ ጌታ አገልጋ
ዩን እንዲህ አለው፣ ‘ቤቴ እንዲሞላ ወደ ገጠር
በሚወስዱት ጐዳናዎችና ስላች መንገዶች
ሂደህ ሌሎች እንዲመጡ አድርግ፤ 24 ከእነዚያ
ከተጠሩት ሰዎች አንዱ እንኳ ድግሴን አይቀም
ስም’ አለ እላችኋለሁ።”

### ኢየሱስን መከተል መሥዋዕትነትን ይጠይቃል
(ማቴ. 10፥37-38)

25 ብዙ ሰዎች ከኢየሱስ ጋር አብረው ይሄዱ
ነበር፤ እርሱም ወደ እነርሱ መለስ ብሎ እን
ዲህ አላቸው፣ 26 “ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባ
ቱንና እናቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹ
ንና እኅቶቹን፣ የራሱንም ሕይወት እንኳ ከእኔ
አብልጦ የሚወድ ከሆነ የእኔ ደቀ መዝሙር
ሊሆን አይችልም። 27 የራሱን መስቀል ተሸክሞ
የማይከተለኝ የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይች
ልም።
28 “ከእናንተ አንዱ ሕንጻ መሥራት ቢፈ
ልግ፣ ለሥራው ማስፈጸሚያ ምን ያህል ገንዘብ
እንደሚያስፈልገው በመጀመሪያ ተቀምጦ ያስ
ባል። 29 መሠረቱን ጥሎ የሕንጻውን ሥራ መፈ
ጸም ያልቻለ እንደሆነ ግን በጅምር የቀረውን
ቤት የሚያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል፤ 30 ‘እነሆ
ይህ ሰው ቤት መሥራት ጀምሮ መጨረስ አል
ቻለም’ እያሉ ያፌዙበታል።
31 “ወይም ዐሥር ሺ ወታደር ያለውን
አንድ ንጉሥ ሃያ ሺ ወታደር አስከትቶ ከሚመ
ጣበት ሌላ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት ቢፈልግ
መጀመሪያ ጠላቱን ለመቋቋም የሚችል መሆ
ኑን ለማወቅ ተቀምጦ ይማከራል። 32 የማይችል
ከሆነ ግን ሊወጋው የመጣውን ንጉሥ ገና
በሩቅ ሳለ ይህ ንጉሥ የሰላም መልእክተኞች
ልኮ ዕርቅ ይጠይቃል። 33 እንዲሁም ከእናንተ
ያለውን ሁሉ ያልተወ ማንም ሰው የእኔ ደቀ
መዝሙር መሆን አይችልም።”

### የማይጠቅም ጨው
(ማቴ. 5፥13፤ ማር. 9፥50)

34 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ “ጨው
መልካም ነው፤ የጨውነቱን ጣዕም ካጣ ግን
በምን ሊጣፍጥ ይችላል? 35 እንዲህ ዐይነቱ
ጨው ለእርሻ መሬትም ሆነ ለማዳበሪያ የማይ
ጠቅም ስለሆነ ወዲያ አውጥተው ይጥሉታል፤
እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።”

## ምዕራፍ 15

### ጠፍቶ የተገኘው በግ
(ማቴ. 18፥12-14)

1 ቀራጮችና ኃጢአተኞች ሁሉ ትምህርቱን
ለመስማት ተሰብስበው ወደ ኢየሱስ መጥተው
ነበር። 2 ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን
ግን ይህንን አይተው “ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀ
በላል፤ ከእነርሱም ጋር አብሮ ይበላል” እያሉ
በኢየሱስ ላይ ማጕረምረም ጀመሩ። 3 ስለዚህም
ኢየሱስ ይህን ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው።



4 “ከእናንተ መቶ በግ ያለው ሰው አንድ በግ
ቢጠፋበት ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?
ዘጠና ዘጠኙን በዱር ትቶ ያን የጠፋውን እስኪ
ያገኝ ድረስ ሊፈልገው ይሄድ የለምን? 5 ባገኘ
ውም ጊዜ ደስ ብሎት በትከሻው ይሸከመውና
መልሶ ያመጣዋል። 6 ወደ ቤቱም በደረሰ
ጊዜ፣ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት
ጠርቶ ‘የጠፋውን በጌን አግኝቼ ደስ ብሎኛልና
ደስ ይበላችሁ!’ ይላቸዋል። 7 ንስሓ መግባት
ከማያስፈልጋቸው ዘጠና ዘጠኝ ደጋግ ሰዎች
ይልቅ፣ ንስሓ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ ምክን
ያት በመንግሥተ ሰማይ እንዲሁ ደስታ ይሆናል
እላችኋለሁ።”

### ጠፍቶ የተገኘው የወርቅ መሐለቅ

8 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ “ዐሥር
የወርቅ መሐለቅ ያላት ሴት አንድ መሐለቅ
ቢጠፋባት ምን የምታደርግ ይመስላችኋል?
መብራት አብርታ፣ ቤትዋን ጠርጋ እስክታገ
ኘው ድረስ በየሥርቻው አጥብቃ ትፈልግ የለ
ምን? 9 ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆችዋንና ጐረቤቶ
ችዋን በአንድነት ጠርታ ‘የጠፋውን መሐለቄን
አግኝቼው ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ!’ ትላ
ቸዋለች። 10 ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ
ምክንያት በሰማይ መላእክት ዘንድ እንዲሁ
ደስታ ይሆናል እላችኋለሁ።”

### ጠፍቶ የተገኘው ልጅ

11 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ “አንድ
ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፤ 12 ታናሹም አባ
ቱን ‘አባባ! ከሀብትህ ከፍለህ ድርሻዬን አሁኑኑ
ስጠኝ’ አለው። ስለዚህ አባትየው ሀብቱን ለሁ
ለት ልጆቹ አካፈለ። 13 ከጥቂት ቀን በኋላ ታና
ሽየው ድርሻውን ሸጦና ለውጦ ገንዘቡን ያዘና
ወደ ሩቅ አገር ሄደ፤ በዚያም አገር ገንዘቡን
ሁሉ በከንቱ አባከነ። 14 ገንዘቡንም ሁሉ ከጨ
ረሰ በኋላ በዚያ አገር ብርቱ ረሀብ በመግባቱ
በችግር ላይ ወደቀ። 15 ከችግሩም የተነሣ ከዚያ
አገር ሰዎች ወደ አንዱ ተጠጋ፤ ሰውየውም የዐ
ሳማ እረኛ አደረገው። 16 ልጁም ረሀቡ ስለጠና
በት ዐሳማዎቹ ከሚመገቡት ብጣሪ አሠር
ሆዱን ለመሙላት ይመኝ ነበር፤ ግን ይህንኑም
እንኳ የሚሰጠው አልነበረም። 17 በዚህ ጊዜ
ልጁ ስሕተቱን ተገንዝቦ እንዲህ ሲል አሰበ፣
‘በአባቴ ቤት ተቀጥረው የሚሠሩ አገልጋዮች
እንጀራ እስኪጠግቡ በልተው ይተርፋቸዋል፤
እኔ ግን እዚህ በረሀብ መሞቴ ነው፤ 18 ተነ
ሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና፦ አባባ! በእግዚአብ
ሔርና በአንተ ፊት በድያለሁ፤ 19 ከእንግዲህ
ወዲህ ያንተ ልጅ ልባል አይገባኝም፤ ነገር ግን
ከቅጥረኞች አገልጋዮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ
ልበለው።’ 20 ስለዚህ ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ።
“አባቱም ገና በሩቅ ሳለ ልጁን አየው፤ ራራ
ለትም ወደ እርሱ ሮጠ፤ እቅፍ አድርጎም
ሳመው። 21 ልጁም ‘አባባ፣ በእግዚአብሔርና
በአንተ ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ልጅህ ልባል አይገባኝም’ አለ። 22 አባቱ ግን
አገልጋዮቹን ጠርቶ እንዲህ አለ፣ ‘ቶሎ ብላ
ችሁ ጥሩ ልብስ አምጡና አልብሱት፤ በጣቱ
ቀለበት፣ በእግሩም ጫማ አድርጉለት፤ 23 የሰባ
ውን ሰንጋ አምጡና እረዱ፤ እንብላ፤ እንደ
ስት፤ 24 ምክንያቱም ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፣
እነሆ አሁን በሕይወት አለ፤ ጠፍቶ ነበር፣
ተገኘ’፤ መደሰትም ጀመሩ።
25 “በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጅ ለሥራ ወደ
እርሻ ወጥቶ ነበር፤ ተመልሶ ሲመጣ ወደ ቤቱ
በተቃረበ ጊዜ የሙዚቃና የዘፈን ድምፅ ሰማ፤
26 ከአገልጋዮቹ አንዱን ጠርቶ ‘ምንድን ነው
ነገሩ?’ ብሎ ጠየቀው። 27 አገልጋዩም ‘ወንድ
ምህ ተመልሶ ስለመጣ ነው፤ አባትህ በደኅና
ስላገኘው የሰባውን ሰንጋ ዐርዶለታል’ አለው።
28 “ታላቅ ወንድሙም በጣም ተቈጥቶ
‘ወደ ቤት አልገባም’ አለ። ስለዚህ አባቱ ወደ
ደጅ ወጥቶ እንዲገባ ለመነው፤ 29 ልጁ ግን ለአ
ባቱ እንዲህ ሲል መለሰ፣ ‘እነሆ ይህን ያህል
ዓመት አገለገልሁህ፤ ከቶ ከትእዛዝህ ዝንፍ ብዬ
አላውቅም፤ ታዲያ እኔ ከጓደኞቼ ጋር የምደሰ
ትበት አንድ ጥቦት እንኳ ሰጥተኸኝ አታው
ቅም። 30 ይህ ልጅህ ግን ሀብትህን ከአመንዝራ
ሴቶች ጋር አባክኖ በተመለሰ ጊዜ የሰባውን
ሰንጋ ዐረድህለት።’ 31 አባቱም እንዲህ አለው፣
‘ልጄ ሆይ! አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤
የእኔ የሆነ ሁሉ የአንተ ነው። 32 ይህ ወንድ
ምህ ግን ሞቶ ነበር፣ አሁን በሕይወት አለ፤
ጠፍቶ ነበር፣ አሁን ተገኘ፤ ስለዚህ በጣም
ልንደሰት ይገባናል።’”

## ምዕራፍ 16

### ብልኅ መጋቢ

1 ደግሞም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አለ፣ “አንድ ሀብታም ሰው ቤቱን የሚያስተዳ
ድርለት መጋቢ ነበረው፤ ሰዎች ‘ይህ መጋቢ
ንብረትህን ያባክናል’ ብለው ለሀብታሙ ሰው
ነገሩት። 2 ሀብታሙም ሰው መጋቢውን አስጠ
ርቶ ‘ይህ የምሰማብህ ነገር ምንድነው? ከእንግ
ዲህ ወዲህ መጋቢዬ ልትሆን አትችልምና በመ
ጋቢነትህ የሠራህበትን የንብረቴን ሒሳብ አቅር
ብልኝ’ አለው። 3 መጋቢውም በልቡ እንዲህ
ሲል አሰበ፣ ‘አሁን እንግዲህ ጌታዬ ከመጋቢ
ነት ሥራዬ ሊያሰናብተኝ ነው፤ ታዲያ ምን
ባደርግ ይሻላል? ማረስ እንደሆን አልችልም፤
መለመን ያሳፍረኛል፤ 4 ቆይ፣ የማደርገውን
ዐውቃለሁ፤ ከመጋቢነት ሥራዬ ስሰናበት በቤ
ታቸው የሚቀበሉኝ ወዳጆች እንዲኖሩኝ አደር
ጋለሁ።’

14፥11 ፦ ማቴ. 23፥12፤ ሉቃ. 18፥14። 14፥26 ፦ ማቴ. 10፥37። 14፥27 ፦ ማቴ. 10፥38፤ 16፥24፤ ማር. 8፥34፤
ሉቃ. 9፥23። 15፥1-2 ፦ ሉቃ. 5፥29-30።

5 “ስለዚህ የጌታውን ባለዕዳዎች ሁሉ አንድ
በአንድ ጠርቶ ፥ የመጀመሪያውን ‘ለጌታዬ የም
ትከፍለው ምን ያህል ዕዳ አለብህ?’ ሲል ጠየ
ቀው ፤ 6 እርሱም ‘መቶ ማድጋ ዘይት ዕዳ አለ
ብኝ’ አለ ። መጋቢው ‘ይኸው መዝገብህ ፥ ቶሎ
ተቀመጥና ኀምሳ ማድጋ ብለህ ጻፍ’ አለው ።
7 ሁለተኛውንም ጠርቶ ፥ ‘የአንተስ ዕዳ ምን
ያህል ነው?’ አለው ። እርሱም ‘መቶ ዳውላ
ስንዴ ዕዳ አለብኝ’ ሲል መለሰ ። መጋቢውም
‘ይኸው መዝገብህ! ሰማኒያ ዳውላ ብለህ ጻፍ’
አለው ። 8 ሀብታሙም ሰው እምነት ያጐደለ
ውን መጋቢ በብልኀነቱ አደነቀው ፤ ይህም ከእ
ግዚአብሔር ሰዎች ይልቅ የዓለም ሰዎች በዓለ
ማዊ ኑሮአቸው ብልኆች መሆናቸውን ያሳ
ያል ።”

## ገንዘብን በአግባቡ
## ማዋል እንደሚገባ

9 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ስለዚህ
በዚህ ዓለም ሀብት ወዳጆች አብጁ እላችኋ
ለሁ ፤ ይህን ብታደርጉ ገንዘባችሁ አልቆባችሁ
ባዶ እጃችሁን ስትቀሩ ወዳጆቻችሁ ለዘላለም
በሚኖሩበት ቤት ይቀበሉአችኋል ። 10 በትንሽ
ነገር የታመነ ሰው በትልቅ ነገርም የታመነ
ይሆናል ፤ በትንሽ ነገር የማይታመን ሰው ግን
በትልቅ ነገርም አይታመንም ። 11 ታዲያ የዚህን
ዓለም ሀብት በማስተዳደር የማትታመኑ ከሆና
ችሁ ፥ እውነተኛውን ሀብትማ ማን አምኖ ይሰ
ጣችኋል? 12 ደግሞም በሌላው ሰው ሀብት የማ
ትታመኑ ከሆነ ፥ ለእናንተ የሚሆነውንስ ሀብት
ማን ይሰጣችኋል?
13 “አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሁለት ጌታ ማገ
ልገል አይችልም ፤ ይህ ከሆነ አንዱን ጠልቶ ሌላ
ውን ይወድዳል ፤ አንዱን አክብሮ ሌላውን ይን
ቃል ፤ እንዲሁም የገንዘብ ተገዥ የሆነ ሰው የእ
ግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ከቶ አይችልም ።”
14 ፈሪሳውያን ገንዘብ ወዳጆች ስለነበሩ ኢየ
ሱስ የተናገረውን ሁሉ ሰምተው አፌዙበት ።
15 እርሱ ግን እንዲህ አላቸው ፥ “እናንተ ራሳች
ሁን በሰው ፊት ጻድቅ ታስመስላላችሁ ፤ እግዚ
አብሔር ግን ልባችሁን ያውቃል ፤ ምክንያቱም
በሰው ፊት የተከበረ መስሎ የሚታይ ሁሉ ፥
በእግዚአብሔር ፊት የተዋረደና የተናቀ
ነው ።”

## ስለ ሙሴ ሕግና ስለ ጋብቻ
(ማቴ. 11፥12-13፤ 5፥31-32፤ ማር. 10፥11-12)

16 ኢየሱስ ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ ፥
“የሙሴ ሕግና የነቢያት መጻሕፍት እስከ አጥ
ማቂው ዮሐንስ ድረስ ሲነገሩ ቆይተው ነበር ፤
ከዚያም ወዲህ የሚነገረው የእግዚአብሔር መን
ግሥት የምሥራች ቃል ነው ፤ እያንዳንዱም
ሰው ወደዚያች መንግሥት ለመግባት ብርቱ
ጥረት ያደርጋል ። 17 ይሁን እንጂ ከሕግ አን
ዲቱ ነጥብ እንኳ ከምትጠፋ ሰማይና ምድር
ቢያልፍ ይቀልላል ።
18 “ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ
ያመነዝራል ፤ እንዲሁም ከባልዋ የተፋታችውን
ሴት የሚያገባ ያመነዝራል ።”

## ሀብታሙ ሰውና
## ድኻው አልዓዛር

19 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፤ “ቀይ
ከፋይና ቀጭን ልብስ የሚለብስ አንድ ሀብታም
ሰው ነበር ፤ እርሱም በየቀኑ ተድላና ደስታ
በማድረግ በቅንጦት ይኖር ነበር ። 20 መላ ሰው
ነቱ በቍስል የተወረሰ አልዓዛር የሚባል አንድ
ድኻ ደግሞ በሀብታሙ ቤት ደጃፍ ተኝቶ
ነበር ፤ 21 ይህም ድኻ ከሀብታሙ ማእድ የሚወ
ድቀውን ፍርፋሪ ለመመገብ ይመኝ ነበር ፤
ውሾችም እየመጡ ቍስሉን ይልሱ ነበር ።
22 “ከዚህም በኋላ ድኻው ሰው ሞተ ፤ መላ
እክትም ወደ አብርሃም አጠገብ ወሰዱት ፤ እን
ዲሁም ሀብታሙ ሰው ሞተና ተቀበረ ። 23 በሲ
ኦልም ሲሠቃይ ሳለ ፥ ቀና ብሎ አብርሃምንና
አጠገቡም የነበረውን አልዓዛርን በሩቅ አያ
ቸው ። 24 ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ ፥
‘አብርሃም አባት ሆይ! እባክህ ራራልኝ ፤ በዚህ
በእሳት ውስጥ በብርቱ እሠቃያለሁና የጣቱን
ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያርስልኝ አልዓ
ዛርን ላክልኝ ።’
25 “አብርሃም ግን እንዲህ አለው ፥ ‘ልጄ
ሆይ! አንተ በምድራዊ ሕይወትህ ዘመን ብዙ
መልካም ነገር አግኝተህ እንደተደሰትህ አስታ
ውስ ፤ አልዓዛር ግን በችግር ላይ ነበር ፤ ስለዚህ
አሁን እርሱ እዚህ ሲደሰት አንተ ትሠቃያለህ ።
26 ከዚህም ሁሉ በላይ በእኛና በእናንተ መካ
ከል ትልቅ ገደል አለ ፤ ስለዚህ ከእኛ ወደ እና
ንተ ፥ ከእናንተም ወደ እኛ መሻገር የሚችል
ማንም የለም ።’ 27 ሀብታሙም እንዲህ አለ ፥
‘አባት ሆይ! እንግዲያውስ እባክህ አልዓዛርን
ወደ አባቴ ቤት ላከው ፤ 28 እዚያ አምስት ወን
ድሞች ስላሉኝ ፥ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ወደ
ሥቃይ ቦታ እንዳይመጡ ሄዶ ያስጠንቅቃ
ቸው ።’
29 “አብርሃም ግን ‘ለእነርሱ የሙሴና የነቢ
ያት መጻሕፍት አሉላቸው ፤ እነርሱን ይስሙ’
አለው ። 30 ሀብታሙም ሰው ‘አብርሃም አባት
ሆይ! ይህ የሚበቃ አይደለም ፤ ነገር ግን አንድ

16፥13 ፦ ማቴ. 6፥24 ። 16፥16 ፦ ማቴ. 11፥12-13 ። 16፥17 ፦ ማቴ. 5፥18 ። 16፥18 ፦ ማቴ. 5፥32 ፤
1ቆሮ. 7፥10-11 ።



ሰው ከሞት ተነሥቶ ቢሄድና ቢነግራቸው ተጸ
ጽተው ንስሓ ይገባሉ’ አለ ። 31 አብርሃምም
‘የሙሴና የነቢያት መጻሕፍት የሚሉትን ካልሰ
ሙማ ፥ አንድ ሰው ከሞት ተነሥቶ ቢነግራቸ
ውም አያምኑትም’ አለው ።”

# ምዕራፍ 17

## ስለ መሰናክል ፥ ስለ ይቅርታ ፥ ስለ እምነት
(ማቴ. 18፥6-7፥21-22፤ ማር. 9፥42)

1 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ ፥
“ሰዎችን አሰናክሎ ወደ ኃጢአት የሚጥል
ነገር መምጣቱ ከቶ አይቀርም ፤ ነገር ግን የኃ
ጢአትን መሰናክል ለሚያመጣው ሰው ወዮ
ለት! 2 ማንም ሰው ከእነዚህ ታናናሽ ልጆች
አንዱን አሰናክሎ ኃጢአት ከሚያሠራ ይልቅ ፥
ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ላይ ታስሮ
ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር ። 3 ስለዚህ
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ፤ ወንድምህ ቢበድልህ
ገሥጸው ፤ በበደሉ ከተጸጸተም ይቅር በለው ፥
4 በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድልህና በቀን ሰባት
ጊዜም ወደ አንተ እየመጣ ‘በበደሌ ተጸጽቼአ
ለሁ’ ቢልህ ይቅር በለው ።”
5 ሐዋርያቱም ጌታ ኢየሱስን “እባክህ እም
ነት ጨምርልን” አሉት ። 6 ጌታ ኢየሱስም
“የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራ
ችሁ ፥ ይህን የሾላ ዛፍ ‘ከዚህ ተነቅለህ በባሕር
ውስጥ ተተከል!’ ብትሉት ይታዘዝላችኋል”
አላቸው ።

## የአገልጋይ ግዳጅ

7 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ከእናንተ
አንዱ በእርሻ ሥራ የተሠማራ ወይም በጎች
የሚጠብቅ አገልጋይ ቢኖረው ፥ አገልጋዩ ከሥ
ራው በተመለሰ ጊዜ ወዲያውኑ ‘ና ተቀመጥና
ራትህን ብላ’ ይለዋልን? 8 ይልቅስ ፥ ‘በል!
ራቴን አዘጋጅልኝ ፥ እስክበላና እስክጠጣም አደ
ግድገህ አገልግለኝ ፤ ከዚህ በኋላ አንተ ደግሞ
ትመገባለህ’ ይለው የለምን? 9 ታዲያ አገልጋዩ
የታዘዘውን ስለፈጸመ ጌታው የሚያመሰግነው
ይመስላችኋልን? 10 እናንተም እንዲሁ የታዘዛች
ሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ ‘የማንጠቅም አገ
ልጋዮች ነን ፤ የፈጸምነውም ግዳጃችንን ብቻ
ነው’ በሉ ።”

## ኢየሱስ ዐሥር
## ለምጻሞችን አዳነ

11 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በሰማር
ያና በገሊላ መካከል ያልፍ ነበር ፤ 12 ወደ አን
ዲት መንደርም በገባ ጊዜ ዐሥር ለምጻሞች
ወደ እርሱ መጥተው በሩቅ ቆሙ ፤ 13 ድምፃቸ
ውንም ከፍ አድርገው “ኢየሱስ ሆይ! መምህር
ሆይ! እባክህ ራራልን!” እያሉ ጮኹ ።
14 ኢየሱስም አያቸውና “ሂዱ! ሰውነታች
ሁን ለካህናት አሳዩ” አላቸው ፤
እነርሱም በመሄድ ላይ ሳሉ ከለምጻቸው
ነጹ ። 15 ከእነርሱም አንዱ ከለምጹ መንጻቱን
ባየ ጊዜ በከፍተኛ ድምፅ እግዚአብሔርን እያ
መሰገነ ተመለሰ ። 16 ኢየሱስንም እያመሰገነ በእ
ግሩ ሥር በግምባሩ ተደፋ ፤ እርሱ የሰማርያ
ሰው ነበር ። 17 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥ “ከለ
ምጽ የነጹት ሰዎች ዐሥር አልነበሩምን?
ታዲያ ዘጠኙ የት አሉ? 18 እግዚአብሔርን ለማ
መስገን ተመልሶ የመጣ ከዚህ ከባዕድ ሰው
በቀር ሌላ የለምን?” 19 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ
ያን ሰው “ተነሥና ሂድ ፥ እምነትህ አድኖሃል”
አለው ።

## የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት
(ማቴ. 24፥23-28፥37-41)

20 ፈሪሳውያን ኢየሱስን “የእግዚአብሔር
መንግሥት መቼ ትመጣለች?” ሲሉ ጠየቁት ፤
እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “የእግዚአ
ብሔር መንግሥት የምትመጣው ሰዎች በሚጠ
ባበቁት ዐይነት አይደለም ፤ 21 እንዲሁም ‘እነሆ
እዚህ ናት ወይም እዚያ ናት’ የምትባል አይደ
ለችም ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግ
ሥት በመካከላችሁ ስለሆነች ነው ።”
22 ቀጥሎም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እን
ዲህ አለ ፥ “ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን እንኳ
ምነው ባየን የምትሉበት ቀን ይመጣል ፤ ነገር
ግን አታዩም ። 23 ሰዎች ‘እነሆ ክርስቶስ እዚህ
ነው! ወይም እዚያ ነው!’ ይሉአችኋል ፤ ነገር
ግን እነርሱ የሚሉትን አትመኑ ፤ አትከተሉአቸ
ውም ። 24 መብረቅ በሰማይ ላይ ሲበርቅ ከዳር
እስከ ዳር እንደሚያበራ የሰው ልጅ በሚመጣበ
ትም ቀን እንዲሁ ይሆናል ፤ 25 ነገር ግን የሰው
ልጅ አስቀድሞ ብዙ መከራ ሊቀበል ፥ በዚህ
ዘመን ሰዎችም ሊናቅና ሊነቀፍ ግድ ነው ።
26 በኖኅ ዘመን እንደሆነው ዐይነት የሰው ልጅ
በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል ። 27 ኖኅ
ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ሲበ
ሉና ሲጠጡ ፥ ሲጋቡም ነበር ፤ በዚያን ጊዜ
የጥፋት ውሃ መጣና አጥለቅልቆ ሁሉንም አጠ
ፋቸው ። 28 እንዲሁም ደግሞ በሎጥ ዘመን እን
ደሆነው ዐይነት ይሆናል ፤ በዚያን ጊዜ ሰዎች
ሲበሉና ሲጠጡ ፥ ሲሸጡና ሲገዙ ፥ አትክልት
ሲተክሉና ቤትም ሲሠሩ ነበር ። 29 ነገር ግን
ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ቀን እሳትና ዲን ከሰ
ማይ ዘንቦ ሁሉንም አጠፋ ፤ 30 የሰው ልጅ
በሚገለጥበት ቀንም እንዲሁ ይሆናል ።

17፥3 ፦ ማቴ. 18፥15 ። 17፥14 ፦ ዘሌ. 14፥1-32 ። 17፥26 ፦ ዘፍ. 6፥5-8 ። 17፥27 ፦ ዘፍ. 7፥6-24 ።
17፥28-29 ፦ ዘፍ. 18፥20-19፥25 ።

31 “በዚያን ቀን በቤቱ ጣራ ላይ ያለ ሰው
በቤቱ ውስጥ ያለውን ዕቃ ለመውሰድ አይው
ረድ ፤ በእርሻም ቦታ ያለ ሰው ወደ ቤቱ አይመ
ለስ ። 32 የሎጥን ሚስት አስታውሱ! 33 ሕይወ
ቱን ለማዳን የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል ፤ ሕይወ
ቱን አሳልፎ የሚሰጥ ሁሉ ያድናታል ። 34 በዚ
ያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተ
ኛሉ ፤ ከእነርሱም አንዱ ይወሰዳል ፥ ሌላው
ይቀራል እላችኋለሁ ። 35 ሁለት ሴቶች በአንድ
ቦታ አብረው ይፈጫሉ ፥ አንድዋ ትወሰዳለች
ሌላዋ ትቀራለች ። [36 ሁለት ሰዎች በአንድ
እርሻ ቦታ ይሠራሉ ፤ አንዱ ይወሰዳል ፥ ሌላው
ይቀራል ።”][6*]
37 ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስን “ጌታ ሆይ!
ወዴት ነው የሚወሰዱት” ሲሉ ጠየቁት ።
እርሱም “በድን ባለበት አሞራዎች ይሰበሰ
ባሉ” ሲል መለሰላቸው ።

## ምዕራፍ 18

### ድኻዋ መበለትና ዐመፀኛው ዳኛ

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሳይታክቱ ዘወትር
መጸለይ እንደሚገባቸው ለማስተማር ይህን
ምሳሌ ነገራቸው ፥ 2 “በአንዲት ከተማ እግዚአ
ብሔርን የማይፈራ ፥ ሰውንም የማያፍር አንድ
ዳኛ ነበረ ። 3 አንዲት መበለትም በዚያች ከተማ
ትኖር ነበር ፤ እርስዋ ወደ ዳኛው እየመጣች
‘ከባላጋራዬ ጋር ስላለኝ ክርክር ፍርድ ስጠኝ’
ትለው ነበር ። 4 እርሱም ፍርድ ሳይሰጣት ብዙ
ጊዜ ቆየ ፤ በኋላ ግን እንዲህ ሲል አሰበ ፥
‘ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ባልፈራ ፥ ሰው
ንም ባላፍር ፥ 5 ይህች መበለት ስለነዘነዘችኝ
እፈርድላታለሁ ፤ አለበለዚያ ግን ዘወትር እየተ
መላለሰች ታሰለቸኛለች ።’ ”
6 ቀጥሎም ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ዐመ
ፀኛው ዳኛ የተናገረውን አስተውሉ ፤ 7 እግዚአ
ብሔር ታዲያ ቀንና ሌሊት እየጮኹ ለሚለም
ኑት ሕዝቦቹ አይፈርድላቸውምን? ችላ በማለ
ትስ ዕርዳታውን ያዘገይባቸዋልን? 8 ሳይዘገይ
በፍጥነት ይፈርድላቸዋል እላችኋለሁ ። ነገር
ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ
እምነትን ያገኝ ይሆን?”

### ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ

9 ቀጥሎም ኢየሱስ ጻድቃን ነን እያሉ ለሚ
መኩና ሌሎችንም ለሚንቁ ሰዎች ይህን ምሳሌ
ተናገረ ፥ 10 “ሁለት ሰዎች ለመጸለይ ወደ ቤተ
መቅደስ ሄዱ ፤ አንዱ ፈሪሳዊ ሲሆን ሌላው
ቀራጭ ነበር ።
11 “ፈሪሳዊው ቆሞ እንዲህ ሲል በልቡ
ጸለየ ፥ ‘እግዚአብሔር ሆይ! እኔ እንደ ሌሎች
ሰዎች ቀማኛ ፥ ዐመፀኛ ፥ አመንዝራ ስላልሆ
ንሁ አመሰግንሃለሁ ፤ ይልቁንም እንደዚህ እንደ
ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ ። 12 እኔ በሳ
ምንት ሁለት ቀን እጾማለሁ ፤ ከማገኘው ሁሉ
ዐሥራት እያወጣሁ እሰጣለሁ ።’
13 “ቀራጩ ግን በሩቅ ቆመና ፥ ቀና ብሎ
ወደ ሰማይ ለማየት እንኳ አልደፈረም ፤ ነገር
ግን በእጁ ደረቱን እየመታ ‘አምላክ ሆይ!
እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ!’ ይል ነበር ።
14 ጽድቅን አግኝቶ ወደ ቤቱ የተመለሰው ይህ
ቀራጭ ነው እንጂ ፈሪሳዊው አይደለም እላችኋ
ለሁ ። ምክንያቱም ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ
ዝቅ ይላል ፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ
ይላል ።”

### ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ
(ማቴ. 19፥13-15፤ ማር. 10፥13-16)

15 ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ሕፃናትን
ወደ እርሱ አመጡ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህን
ባዩ ጊዜ ሰዎቹን ተቈጡአቸው ። 16 ኢየሱስ ግን
ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አለ ፥ “የእ
ግዚአብሔር መንግሥት እንደእነዚህ ላሉት ስለ
ሆነች ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ ፤ አትከልክሉአ
ቸው ። 17 በእውነት እላችኋለሁ ፥ የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት እንደ ሕፃን በየዋህነት ያልተቀ
በላት ሰው ከቶ አይገባባትም ።”

### የሀብታሙ ሰው ጥያቄ
(ማቴ. 19፥16-30፤ ማር. 10፥17-31)

18 ከአይሁድ አለቆች አንዱ ኢየሱስን “ደግ
መምህር ሆይ! የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት
ምን ማድረግ ይገባኛል!” ብሎ ጠየቀው ።
19 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ለምን
ደግ ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር
ማንም ደግ የለም ። 20 ትእዛዛትን ታውቃለህ ፤
እነርሱም ‘አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስ
ረቅ ፥ በሐሰት አትመስክር ፥ አባትህንና እናት
ህን አክብር’ የተባሉት ናቸው ።”
21 ሰውየውም “እነዚህንማ ትእዛዞች ከሕፃን
ነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ” አለው ።
22 ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ ሰውየውን እን
ዲህ አለው ፥ “እንግዲያውስ ገና አንድ ነገር
ማድረግ ይቀርሃል ፤ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ገንዘቡን
ለድኻ ስጥ ፤ በመንግሥተ ሰማያትም የሀብት
መዝገብ ታገኛለህ ፤ ከዚያም በኋላ መጥተህ ተከ
ተለኝ ።” 23 ሰውየው ግን በጣም ሀብታም ስለነ
በረ ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ ። 24 ኢየሱስም

[6*] 17፥36 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 36 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በማቴ. 24፥40 ያለውን ይመስላል ።
17፥31 ፦ ማቴ. 24፥17-18 ፤ ማር. 13፥15-16 ። 17፥32 ፦ ዘፍ. 19፥26 ። 17፥33 ፦ ማቴ. 10፥39 ፤ 16፥25 ፤ ማር. 8፥35 ፤
ሉቃ. 9፥24 ፤ ዮሐ. 12፥25 ። 18፥14 ፦ ማቴ. 23፥12 ፤ ሉቃ. 14፥11 ። 18፥20 ፦ ዘጸ. 20፥12-16 ፤ ዘዳ. 5፥16-20 ።



ሰውየው እንዳዘነ አይቶ እንዲህ አለ ፥ “ለሀብታ
ሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት
እንዴት አስቸጋሪ ነው! 25 እንዲያውም ሀብ
ታም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚ
ገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀ
ልላል ።”
26 ይህን የሰሙ ሰዎች “ታዲያ በዚህ ሁኔታ
ማን ሊድን ይችላል?” አሉ ።
27 ኢየሱስ ግን “በሰው ዘንድ የማይቻል
ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል” አለ ።
28 ጴጥሮስም “እነሆ እኛ ያለንን ሁሉ
ትተን ተከትለንሃል” አለው ።
29 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፤ “በእውነት
እላችኋለሁ ፥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት
ብሎ ቤቱን ወይም ሚስቱን ወይም ወንድሞ
ቹን ወይም ወላጆቹን ወይም ልጆቹን የሚተው
ሰው የበለጠ ያገኛል ። 30 ይኸውም አሁን በዚህ
ዓለም በብዙ እጥፍ ይቀበላል ፤ በሚመጣውም
ዓለም የዘላለምን ሕይወት ያገኛል ማለት
ነው ።”

### ኢየሱስ ስለሞቱ ሦስተኛ ጊዜ ተናገረ
(ማቴ. 20፥17-19፤ ማር. 10፥32-34)

31 ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ አቅ
ርቦ እንዲህ አላቸው ፥ “እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም
መሄዳችን ነው ፤ ስለ ሰው ልጅ በነቢያት የተጻ
ፈው ሁሉ በዚያ ይፈጸማል ። 32 እርሱ ለአረማ
ውያን ተላልፎ ይሰጣል ፤ እነርሱም ያላግጡበ
ታል ፤ ይሰድቡታል ፤ ይተፉበታል ። 33 ከገረፉ
ትም በኋላ ይገድሉታል ፤ ነገር ግን በሦስተኛው
ቀን ከሞት ይነሣል ።”
34 ደቀ መዛሙርቱ ግን ከዚህ ሁሉ ነገር አን
ዱንም አልተረዱም ፤ የንግግሩም ምስጢር ተሰ
ውሮባቸው ስለ ነበር ምን ማለቱ እንደሆነ አላ
ወቁም ።

### ኢየሱስ በኢያሪኮ አንድ ዐይነ ስውር ፈወሰ
(ማቴ. 20፥29-34፤ ማር. 10፥46-52)

35 ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ በቀረበ ጊዜ አንድ
ዐይነ ስውር ምጽዋት እየለመነ በመንገድ ዳር
ተቀምጦ ነበር ፤ 36 በአጠገቡ የሚያልፉትን
የብዙ ሰዎች ድምፅ በሰማ ጊዜ ዐይነ ስውሩ
“ይህ ምንድን ነው?” ብሎ ጠየቀ ።
37 ሰዎቹም “እነሆ የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚህ
በኩል እያለፈ ነው” ብለው ነገሩት ።
38 በዚያን ጊዜ ዐይነ ስውሩ “የዳዊት ልጅ
ኢየሱስ ሆይ! እባክህ ማረኝ” እያለ ጮኸ ።
39 ቀድመው እፊት እፊት ይሄዱ የነበሩት
ሰዎች “ዝም በል!” ብለው ገሠጹት ። እርሱ
ግን ድምፁን በይበልጥ ከፍ አድርጎ “የዳዊት
ልጅ ሆይ! እባክህ ራራልኝ!” ይል ነበር ።
40 ስለዚህ ኢየሱስ ቆመና “ወደ እኔ አም
ጡት” ብሎ አዘዘ ። ዐይነ ስውሩም ወደ እርሱ
በመጣ ጊዜ ፥ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጠየቀው ፥
41 “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?”
ዐይነ ስውሩም “ጌታ ሆይ! ማየት እፈልጋ
ለሁ” አለው ።
42 ኢየሱስም “እይ! እምነትህ አድኖሃል”
አለው ።
43 ዐይነ ስውሩም ወዲያውኑ ማየት ቻለ ፤
እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ኢየሱስን መከተል
ጀመረ ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይህን ባዩ ጊዜ እግዚአ
ብሔርን አመሰገኑ ።

## ምዕራፍ 19

### ኢየሱስና ዘኬዎስ

1 ኢየሱስ ጕዞውን በመቀጠል ወደ ኢያሪኮ
ከተማ ገባ ፤ በከተማውም መካከል አልፎ ሄደ ።
2 በዚያም ዘኬዎስ የሚባል ሰው ነበረ ፤ እርሱ
የቀራጮች አለቃና ሀብታም ሰው ነበረ ።
3 እርሱ ኢየሱስ የቱ እንደሆነ ለማየት ይፈልግ
ነበር ፤ ነገር ግን ቁመቱ አጭር በመሆኑ ከሕ
ዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም ። 4 ኢየ
ሱስ በዚያ በኩል ያልፍ ስለነበር ዘኬዎስ ኢየሱ
ስን ለማየት ብሎ ከሕዝቡ ፊት ቀደመና በአ
ንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ ። 5 ኢየሱስም ወደዚያ
ስፍራ በደረሰ ጊዜ ቀና ብሎ ተመለከተና ዘኬዎ
ስን “ዘኬዎስ ሆይ! ዛሬ በአንተ ቤት መዋል
ይገባኛልና ፈጥነህ ከዛፉ ውረድ” አለው ።
6 ዘኬዎስም ቶሎ ብሎ ወረደና በደስታ ኢየሱ
ስን በቤቱ ተቀበለው ። 7 ይህን የተመለከቱ
ሰዎች ሁሉ “ይህ ሰው ወደ ኃጢአተኛ ቤት
ሊጋበዝ ገባ!” ብለው በኢየሱስ ላይ አጕረመ
ረሙ ።
8 ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታ ኢየሱስን እንዲህ
አለው ፥ “ጌታ ሆይ! እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ
እኩሌታውን ለድኾች እሰጣለሁ ፤ በማታለል
ከሰው ላይ የወሰድኩትም ገንዘብ ቢኖር ፥ አራት
እጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ ።”
9 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥ “ይህ ሰው ደግሞ
የአብርሃም ዘር ነውና ዛሬ ደኅንነት ለዚህ ቤት
ሆኖአል ፤ 10 ምክንያቱም የሰው ልጅ የጠፋውን
ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአል ።”

### የዐሥሩ አገልጋዮች ምሳሌ
(ማቴ. 25፥14-30)

11 ሰዎቹ ይህን በመስማት ላይ ሳሉ ኢየሱስ
አንድ ምሳሌ ደግሞ ነገራቸው ፤ ምክንያቱም

19፥10 ፦ ማቴ. 18፥11 ። 19፥11-27 ፦ ማቴ. 25፥14-30 ።

እርሱ ወደ ኢየሩሳሌም ስለተቃረበ ሰዎቹ የእግ
ዚአብሔር መንግሥት አሁኑኑ የምትገለጥ መስ
ሎአቸው ነበር ። 12ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ
አለ ፥ “የንጉሥነትን ሥልጣን ተቀብሎ ለመመ
ለስ ወደ ሩቅ አገር የሄደ አንድ ክቡር ሰው
ነበረ ፤ 13እርሱ ከመሄዱ በፊት ከአገልጋዮቹ
ዐሥሩን ጠርቶ ለእያንዳንዱ መቶ መቶ ብር
ሰጣቸውና ‘ተመልሼ እስክመጣ ድረስ በዚህ
ገንዘብ ነግዱ’ አላቸው ። 14የአገሩ ሰዎች ግን
ይጠሉት ስለነበር ይህ ሰው በእኛ ላይ እንዲነ
ግሥ አንፈልግም ሲሉ እርሱ ከሄደ በኋላ መል
እክተኞችን ላኩበት ።
15“ያ ሰው ንጉሥ ሆኖ በተመለሰ ጊዜ ቦተ
ሰጣቸው ገንዘብ ነግደው ምን ያህል እንዳተረፉ
ለማወቅ አገልጋዮቹን አስጠራቸው ። 16የመጀ
መሪያው አገልጋይ ቀርቦ ‘ጌታ ሆይ! በሰጠኸኝ
ገንዘብ ነግጄ እነሆ ዐሥር እጥፍ አትርፌአለሁ’
አለው ። 17ጌታውም ‘አንተ ታማኝ አገልጋይ!
መልካም አደረግህ! በትንሽ ነገር ስለታመንህ
እኔ ደግሞ በዐሥር ከተሞች ላይ ሾሜሃለሁ’
አለው ። 18ሁለተኛውም አገልጋይ ቀርቦ ‘ጌታ
ሆይ! በሰጠኸኝ ገንዘብ ነግጄ እነሆ አምስት
እጥፍ አትርፌአለሁ’ አለው ። 19ጌታው ይህኛ
ውንም ‘አንተንም ደግሞ በአምስት ከተሞች
ላይ ሾሜሃለሁ’ አለው ።
20“ሌላውም አገልጋይ ቀርቦ እንዲህ አለ ፥
‘ጌታዬ ሆይ! የሰጠኸኝ ገንዘብ ይኸውልህ ፤
በጨርቅ ቋጥሬ አስቀምጬው ነበር ። 21ምክን
ያቱም አንተ ያላስቀመጥከውንና የራስህ ያልሆነ
ውን የምትወስድ ፥ ያልዘራኸውንም የምትሰበ
ስብ ፥ ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቄ ስለፈራሁህ
ነው ።’ 22ጌታውም እንዲህ አለው ፥ ‘አንተ
መጥፎ አገልጋይ! በአነጋገርህ እፈርድብሃለሁ ፤
እኔ የራሴ ያልሆነውን የምወስድና ያልዘራሁ
ትን የምሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆኔን ዐውቃለሁ
ብለህ የለምን? 23ታዲያ ገንዘቤን ትርፍ በሚያ
ስገኝልኝ በባንክ ለምን አላስቀመጥከውም
ነበር? እኔ ተመልሼ ስመጣ ከነትርፉ እወስ
ደው ነበር ።’ 24ከዚህ በኋላ ጌትየው በዚያ
ቆመው የነበሩትን ‘የዚህን ሰው ገንዘብ ወስዳ
ችሁ ዐሥር ጊዜ እጥፍ ላተረፈው አገልጋይ
ስጡት’ አላቸው ። 25እነርሱም ‘ጌታ ሆይ!
እርሱ እኮ ዐሥር ጊዜ እጥፍ ትርፍ ገንዘብ
አለው’ አሉት ። 26ጌትየው እንዲህ አላቸው ፥
‘ላለው ሁሉ ይበልጥ ይሰጠዋል ፤ ከሌለው ሰው
ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል እላችኋ
ለሁ ። 27እንድነግሥ ያልፈለጉትን እነዚያን
ጠላቶቼን ግን እዚህ አምጥታችሁ በፊቴ ግደሉ
አቸው ።’” 28ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ከተናገረ
በኋላ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም በመቀጠል
ከደቀ መዛሙርቱ ፊት ፊት ይሄድ ነበር ።

### ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ
(ማቴ. 21፥1-11፤ ማር. 11፥1-11፤
ዮሐ. 12፥12-19)

29ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ አጠገብ
ወደሚገኙት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀ
ረበ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ ሲል
ላካቸው ፤ 30“በፊታችሁ ወደምትገኘው መን
ደር ሂዱ ፤ እዚያም በደረሳችሁ ጊዜ ገና ማንም
ሰው ያልተቀመጠበትን የአህያ ውርንጫ ታስሮ
ታገኛላችሁ ፤ ፈትታችሁ ወዲህ አምጡት ።
31ማንም ሰው ፥ ‘ለምን ትፈቱታላችሁ?’ ብሎ
ቢጠይቃችሁ ‘ጌታ ስለሚያስፈልገው ነው’ ብላ
ችሁ መልሱለት ።”
32የተላኩትም ሄደው ሁሉም ነገር ልክ ኢየ
ሱስ እንዳላቸው ሆኖ አገኙ ። 33ውርንጫውን
በሚፈቱበት ጊዜ ባለቤቶቹ “ስለምን ትፈቱታላ
ችሁ?” አሉአቸው ። 34እነርሱም “ጌታ ስለሚ
ያስፈልገው ነው” አሉ ። 35ውርንጫውንም
ወደ ኢየሱስ አመጡ ፤ ልብሳቸውንም በውርን
ጫው ጀርባ ላይ አንጥፈው ኢየሱስ እንዲቀመጥ
በት አደረጉ ። 36ኢየሱስ ሲሄድ ሳለ ፥ ሰዎች
ሸማቸውን በመንገዱ ላይ ያነጥፉለት ነበር ።
37ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ሊደርስ
በተቃረበ ጊዜ የደብረ ዘይትን ተራራ ቁልቁል
በመውረድ ላይ ነበር ፤ በዚያን ጊዜ ኢየሱስን
ይከተሉት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ስላዩአቸው
ተአምራት በደስታ ተሞልተው ስለነበር ድምፃ
ቸውን ከፍ አድርገው እግዚአብሔርን ማመስገን
ጀመሩ ። 38እንዲህ ይሉም ነበር ፥ “በእግዚአብ
ሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው!
ሰላም በሰማይ ፥ ክብርም ለእግዚአብሔር በአር
ያም ይሁን!”
39በሕዝቡ መካከል የነበሩት ፈሪሳውያን
ግን ኢየሱስን “መምህር ሆይ! ደቀ መዛሙርት
ህን ዝም አሰኛቸው” አሉት ።
40ኢየሱስም “እነርሱ እንኳ ዝም ቢሉ ድን
ጋዮች ይጮኻሉ እላችኋለሁ” ሲል መለሰላ
ቸው ።

### ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ አለቀሰ

41ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ቀርቦ
ከተማይቱን በተመለከተ ጊዜ አለቀሰላት ።
42እንዲህም አለ ፥ “አንቺ እንኳ ለሰላምሽ የሚ
ያስፈልገውን ነገር ዛሬ ምነው ዐውቀሽ ቢሆን
ኖሮ! አሁን ግን ይህ ነገር ከዐይንሽ ተሰውሮብ
ሻል ፤ 43ጠላቶችሽ በዙሪያሽ ዐጥር ዐጥረውና
ከብበው በዚህም በዚያም አንቺን የሚያስጨንቁ
በት ቀን ይመጣል ። 44አንቺንና በውስጥሽ ያሉ
ትንም ልጆችሽን በመሬት ላይ ጥለው ያወድ
ማሉ ፤ ሳይፈርስ የሚቀር አንድ ድንጋይ እንኳ

19፡26 ፦ ማቴ. 13፥12 ፤ ማር. 4፥25 ፤ ሉቃ. 8፥18 ። 19፡38 ፦ መዝ. 118፥26 ።



በቦታው አይተውልሽም ፤ ምክንያቱም እግዚአ
ብሔር አንቺን ሊጐበኝና ሊያድን የመጣበትን
ጊዜ ባለማወቅሽ ነው ።”

### ኢየሱስ በቤተ መቅደስ የሚገበያዩትን ሰዎች አባረረ
(ማቴ. 21፥12-17፤ ማር. 11፥15-19፤
ዮሐ. 2፥13-22)

45ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በዚያ
የሚገበያዩትን ሰዎች ማባረር ጀመረ ፤ 46እንዲ
ህም አላቸው ፥ “‘ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል’
ተብሎ ተጽፎአል ፤ እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ
አደረጋችሁት ።”
47ኢየሱስ በየቀኑ በቤተ መቅደስ ያስተምር
ነበር ፤ የካህናት አለቆችና የሙሴ ሕግ መምህ
ራን ሌሎችም የሕዝብ መሪዎች ሊገድሉት ይፈ
ልጉ ነበር ። 48ነገር ግን ይህን ለመፈጸም ምን
ማድረግ እንደሚገባቸው አላወቁም ፤ ምክንያ
ቱም ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን ለመስማት በመፈ
ለግ ልባቸው ተሰቅሎ ስለነበር ነው ።

## ምዕራፍ 20

### ስለ ኢየሱስ ሥልጣን የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 21፥23-27፤ ማር. 11፥27-33)

1አንድ ቀን ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ተገኝቶ
ሕዝቡን ያስተምርና ወንጌልንም ያበሥር
ነበር ፤ በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆችና የሙሴ
ሕግ መምህራን ሽማግሌዎችም ወደ እርሱ
መጡ ፤ 2እንዲህም ሲሉ ጠየቁት ፥ “በል እስቲ
ንገረን! እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን
ሥልጣን ነው? ወይስ እነዚህን እንድታደርግ
ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው?” 3ኢየሱስም እን
ዲህ አላቸው ፥ “እኔም አንድ ጥያቄ እጠይ
ቃችኋለሁ ፤ በሉ እስቲ መልሱልኝ ፤ 4የዮሐንስ
ጥምቀት ከእግዚአብሔር ነበረን ወይስ ከሰው?”
5እነርሱም እንዲህ እያሉ እርስ በርሳቸው
ተነጋገሩ ፥ “‘ከእግዚአብሔር ነው’ ብንል ፥
‘ታዲያ ለምን አላመናችሁበትም?’ ይለናል ፤
6‘ከሰው ነው’ ብንል ደግሞ ፥ ሕዝቡ በድንጋይ
ይወግሩናል ፤ ምክንያቱም ሁሉም ዮሐንስ
ነቢይ መሆኑን ያምናሉ ።” 7ስለዚህ “ከየት
እንደሆነ አናውቅም” ሲሉ መለሱለት ። 8ኢየሱ
ስም “እንግዲያውስ እኔም በምን ሥልጣን እነ
ዚህን ነገሮች እንደማደርግ አልነግራችሁም”
አላቸው ።

### የወይኑ አትክልት ገበሬዎች ምሳሌ
(ማቴ. 21፥33-46፤ ማር. 12፥1-12)

9ቀጥሎም ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ለሕዝቡ
ተናገረ ፥ “አንድ ሰው የወይን አትክልት
ተከለ ፤ ለገበሬዎች አከራየውና ወደ ሌላ አገር
ሄደ ፤ ሳይመለስም ብዙ ጊዜ ቆየ ። 10ወይኑ
ባፈራ ጊዜ የወይኑ አትክልት ባለቤት ከፍሬው
ድርሻውን እንዲቀበልለት አንድ አገልጋይ ወደ
ገበሬዎቹ ላከ ፤ ገበሬዎቹ ግን አገልጋዩን ደብ
ድበው ባዶ እጁን ሰደዱት ። 11እንዲሁም ሌላ
አገልጋይ ቢልክ እርሱንም ደበደቡት ፤ አዋርደ
ውም ባዶ እጁን ሰደዱት ፤ 12እንደገናም ሦስ
ተኛ አገልጋይ ቢልክ እርሱንም ደብድበው አቆ
ሰሉትና አውጥተው ጣሉት ። 13ከዚህም በኋላ
የወይኑ አትክልት ባለቤት ‘እንግዲህ ምን ላድ
ርግ? የምወድደውን ልጄን ልላክዋ! እርሱን
ምናልባት ያከብሩት ይሆናል’ አለ ። 14ነገር
ግን ገበሬዎቹ ባዩት ጊዜ እርስ በርሳቸው እን
ዲህ ተባባሉ ፥ ‘ይህማ ወራሹ ነው ፤ ኑ እንግደ
ለው ፤ ርስቱም ለእኛ ይሆናል ።’ 15ስለዚህ
ልጁን ከወይኑ አትክልት ቦታ ወደ ውጪ አው
ጥተው ገደሉት ። ታዲያ እንግዲህ የወይኑ አት
ክልት ጌታ በእነዚህ ገበሬዎች ላይ ምን የሚያ
ደርግ ይመስላችኋል? 16የወይኑ አትክልት ባለ
ቤት ራሱ ይመጣል ፤ ገበሬዎቹንም ይገድላል ፤
የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ገበሬዎች ይሰ
ጣል ።” ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ “ይህስ ከቶ
አይሁን!” አሉ ።
17ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ እን
ዲህ አለ ፤
“ታዲያ ፥
‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማእዘን
ራስ ሆነ’
ተብሎ የተጻፈው ምንን ያመለክታል? 18በዚያ
ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይሰበራል ፤ ድን
ጋዩ በላዩ ላይ የሚወድቅበት ሰው ግን ይፈጨፈጨ
ቃል ።”

### ግብር ስለመክፈል የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 22፥15-22፤ ማር. 12፥13-17)

19የሙሴ ሕግ መምህራንና የካህናት አለቆች
ይህን ምሳሌ በእነርሱ ላይ እንደተናገረ ዐው
ቀው በዚያን ሰዓት ሊይዙት ፈልገው ነበር ።
ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ ። 20ስለዚህ ኢየሱስን
ለመያዝ ምቹ ጊዜ ይጠብቁ ነበር ። ለገዥው
ሥልጣንና ፍርድ አሳልፈው ለመስጠት የሚያስ
ችላቸውን ቃል ከእርሱ ለማግኘት ይፈልጉ
ነበር ፤ ስለዚህ ጻድቃን መስለው በንግግሩ የሚ
ያጠምዱትን ሰላዮች ላኩበት ። 21ሰላዮቹም
ወደ ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት ፥
“መምህር ሆይ! አንተ የምትናገረውንና የምታ
ስተምረውን እውነት መሆኑን እናውቃለን ፤ የእ
ግዚአብሔርን መንገድ በእውነት ታስተምራለህ
እንጂ ለማንም አታዳላም ። 22እስቲ ንገረን!
በሕጋችን መሠረት ለሮም ቄሳር ግብር መክፈል
ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም?”

19፡46 ፦ ኢሳ. 56፥7 ፤ ኤር. 7፥11 ። 19፡47 ፦ ሉቃ. 21፥37 ። 20፡9 ፦ ኢሳ. 5፥1 ። 20፡17 ፦ መዝ. 118፥22 ።

23 ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው ፤ 24 “እስቲ ገንዘቡን አሳዩኝ ፤ በዚህ
ገንዘብ ላይ የተቀረጸው መልክና የተጻፈው ስም
የማን ነው?”
እነርሱም “የቄሳር ነው” አሉት ።
25 ኢየሱስም “እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄ
ሳር ፥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ”
አላቸው ።
26 እነርሱም በሕዝቡ ፊት በንግግሩ ሊያጠ
ምዱት አልቻሉም ፤ ስለዚህ በመልሱ ተደን
ቀው ዝም አሉ ።

ስለሙታን መነሣት የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 22፥23-33፤ ማር. 12፥18-27)

27 “ሙታን አይነሡም” የሚሉ ሰዱቃውያን
ወደ ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት ፥
28 “መምህር ሆይ! ሙሴ እንዲህ ሲል ጽፎል
ናል ፥ ‘አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ከሚስቱ
በሞት ቢለይ ወንድሙ ሴትዮዋን አግብቶ
ለሟቹ ዘር ያትርፍለት ።’ 29 ሰባት ወንድማማ
ቾች ነበሩ ፤ የሁሉም ታላቅ ሚስት አግብቶ
ልጅ ሳይወልድ ሞተ ። 30 ተከታይ ወንድሙም
ያችኑ ሴት አገባት ፤ 31 ሦስተኛውም አገባት ፤
በዚህ አኳኋን ሰባቱም አግብተዋት ልጆች ሳይ
ወልዱ ሞቱ ። 32 ከሁሉም በኋላ ሴትዮዋ
ሞተች ። 33 ሰባቱም በየተራ አግብተዋታልና
ታዲያ ሙታን በሚነሡበት ጊዜ ለየትኛው
ሚስት ትሆናለች?”
34 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“የዚህ ዓለም ሰዎች ያገባሉ ይጋባሉ ፤ 35 ከሙ
ታን ተነሥተው በሚመጣው ዓለም ለመኖር
የተገባቸው ሰዎች ግን አይጋቡም ። 36 ምክንያ
ቱም እንደ መላእክት ስለሚሆኑ አይሞቱም ፤
ከሞት ስለተነሡም የእግዚአብሔር ልጆች
ናቸው ። 37 ስለሙታን ትንሣኤ ግን ሙሴም ስለ
ቍጥቋጦው እሳት በተናገረው ታሪክ ውስጥ ገል
ጦታል ፤ በዚያም ታሪክ ውስጥ ሙሴ እግዚአብ
ሔርን ‘የአብርሃም አምላክ ፥ የይስሐቅ አም
ላክ ፥ የያዕቆብ አምላክ’ ብሎ ጠርቶታል ።
38 ስለዚህ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው
እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ፤ ምክንያ
ቱም ሁሉም ለእርሱ በሕይወት ይኖራሉ ።”
39 ከሙሴ ሕግ መምህራንም አንዳንዶቹ
“መምህር ሆይ! መልካም ተናገርህ!” አሉ ።
40 ከዚያም ወዲህ ለኢየሱስ ጥያቄ ሊያቀርብለት
የደፈረ ማንም የለም ።

ኢየሱስ ስለ ራሱ ያቀረበው ጥያቄ
(ማቴ. 22፥41-46፤ ማር. 12፥35-37)

41 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥
“እንዴት መሲሕን የዳዊት ልጅ ነው ይሉ
ታል? 42-43 ዳዊት እኮ ራሱ በመዝሙር መጽ
ሐፍ ውስጥ
‘እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለመሲሑ)
ጠላቶችህን በሥልጣንህ ሥር
እስካደርግልህ ድረስ
በቀኜ ተቀመጥ አለው’ ይላል ።
44 እንግዲህ ዳዊት ራሱ ጌታ ብሎ ከጠራው
ታዲያ መሲሕ ለዳዊት እንዴት ልጁ ሊሆን
ይችላል?”

ኢየሱስ ከሙሴ ሕግ መምህራን ተጠንቀቁ አለ
(ማቴ. 23፥1-36፤ ማር. 12፥38-40)

45 ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙት ሳሉ ኢየሱስ ደቀ
መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ፥ 46 “ረዣዥም
ልብስ ለብሰው ወዲያና ወዲህ መዞርን ፥ በገበ
ያም የክብር ሰላምታ መቀበልን ፥ በምኵራብ
የከበሬታን ወንበር ፥ በግብዣም የክብር ስፍራን
ከሚወድዱ ከሙሴ ሕግ መምህራን ተጠንቀቁ ።
47 እነርሱም ለታይታ በሚያቀርቡት ረዥም
ጸሎት እያመካኙ የመበለቶችን ቤት ይበዘብ
ዛሉ ፤ ስለዚህ እነርሱ የባሰ ፍርድ ያገኛቸ
ዋል ።”

## ምዕራፍ 21

የመበለቲቱ ስጦታ
(ማር. 12፥41-44)

1 ኢየሱስ ቀና ብሎ ሲመለከት ሀብታሞች
መባቸውን በምጽዋት መቀበያ ሣጥን ውስጥ
ሲያገቡ አየ ። 2 እንዲሁም አንዲት ድኻ መበ
ለት ሁለት ሳንቲም የሚያህል የናስ ገንዘብ በሣ
ጥኑ ውስጥ ስታስገባ አየ ። 3 እንዲህም አለ ፥
“በእውነት እላችኋለሁ ፤ ይህች ድኻ መበለት
ከሁሉም ይልቅ አብልጣ ሰጥታለች ። 4 ምክንያ
ቱም እነርሱ የሰጡት ከሀብታቸው የተረፋቸ
ውን ነው ፤ እርስዋ ግን ድኻ ሆና ሳለች ምንም
ሳታስቀር ያላትን ሁሉ ሰጠች ።”

ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ የኢየሱስ ትንቢት
(ማቴ. 24፥1-2፤ ማር. 13፥1-2)

5 አንዳንድ ሰዎች “ይህ ቤተ መቅደስ እን
ዴት ውብ ነው ፤ በከበሩ ድንጋዮችና ለእግዚአ
ብሔር በቀረቡ ስጦታዎች አጊጦአል” እያሉ
ይነጋገሩ ነበር ። 6 ኢየሱስ ግን “ይህ የምታዩት
ሁሉ ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮ የማይቀ
ርበት ጊዜ ይመጣል ፤ እነዚህ ድንጋዮች ሁሉ
አንድ ቀን ይፈርሳሉ ።”
7 እነርሱም “መምህር ሆይ! ይህ የሚሆነው
መቼ ነው? ይህስ የሚሆንበት ጊዜ መቃረቡን
የምናውቅበት ምልክት ምንድን ነው?” ሲሉ
ጠየቁት ።

20፡27 ፦ ሐ.ሥ. 23፥8 ። 20፡28 ፦ ዘዳ. 25፥5 ። 20፡37 ፦ ዘጸ. 3፥6 ። 20፥42-43 ፦ መዝ. 110፥1 ።



ኢየሱስ የመከራና የደስታ
ጊዜ እንደሚመጣ ተናገረ
(ማቴ. 24፥3-14፤ ማር. 13፥3-13)

8 ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “እንዳ
ትሳሳቱ ተጠንቀቁ ፤ ብዙዎች ‘እኔ ክርስቶስ
ነኝ! እነሆ ጊዜው ቀርቦአል!’ እያሉ በስሜ
ይመጣሉ ፤ እነርሱን አትከተሉአቸው ። 9 ስለ
ጦርነትና ስለ ሁከት በምትሰሙበት ጊዜም አት
ደንግጡ ፤ አስቀድሞ ይህ ይሆን ዘንድ ይገባል ፤
ይሁን እንጂ ፍጻሜው ወዲያውኑ አይሆንም ።”
10 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ሕዝብ
በሕዝብ ላይ ፥ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነ
ሣል ። 11 በየቦታውም ብርቱ የምድር መና
ወጥ ፥ ረሀብና በሽታ ይሆናል ። የሚያስፈሩ ነገ
ሮችና ታላላቅ ምልክቶች በሰማይ ላይ ይታ
ያሉ ። 12 ነገር ግን ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት
ሰዎች እናንተን ይይዙአችኋል ፤ ያሳድዱ
አችኋል ፤ ወደ ምኵራብና ወደ ወህኒ ቤትም
አሳልፈው ይሰጡአችኋል ፤ ስለ ስሜም ወደ ነገ
ሥታትና ወደ ገዥዎች ይወስዱአችኋል ።
13 ይህም ስለ ስሜ ለመመስከር መልካም አጋ
ጣሚ ይሆንላችኋል ። 14 ስለዚህ በሚቀርብባ
ችሁ ክስ ስለምትሰጡት መልስ መጨነቅ እንደ
ማይገባችሁ አስቀድማችሁ ልብ አድርጉ ።
15 ምክንያቱም ከጠላቶቻችሁ ማንም ሊቋቋመ
ውና ሊቃወመው የማይችለውን ቃልና ጥበብ
እኔ እሰጣችኋለሁ ። 16 ወላጆቻችሁና ወንድሞቻ
ችሁ ዘመዶቻችሁና ወዳጆቻችሁም ሳይቀሩ አሳ
ልፈው ይሰጡአችኋል ፤ ከእናንተ አንዳንዶቹ
ይገደላሉ ። 17 ስለ ስሜም በሰው ሁሉ ዘንድ
የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ። 18 ነገር ግን ከራሳ
ችሁ ጠጕር አንዲት እንኳ አትጠፋም ። 19 በት
ዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ታድናላችሁ ።”

ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት ተናገረ
(ማቴ. 24፥15-21፤ ማር. 13፥14-19)

20 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ኢየሩሳ
ሌም በጠላት ወታደሮች ተከብባ ባያችሁ ጊዜ
ለመጥፋት እንደተቃረበች ዕወቁ ፤ 21 በዚያን
ጊዜ በይሁዳ አገር ያሉ ወደ ተራራዎች
ይሽሹ ፤ በከተማይቱ ውስጥ ያሉ ከዚያ
ይውጡ ፤ ከከተማ ውጪ ያሉትም ወደ ከተማ
ይቱ አይግቡ ። 22 ምክንያቱም ስለዚህ ጥፋት
የተጻፈው ትንቢት እንዲፈጸም ይህ የበቀልና
የቅጣት ጊዜ ነው ። 23 በዚያን ጊዜ ለነፍሰጡሮ
ችና ለሚያጠቡ እመጫቶች ወዮላቸው! ምክን
ያቱም በምድር ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል ፤
በዚህም ሕዝብ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ይመ
ጣል ። 24 ከእነርሱም ብዙዎች በሰይፍ ይገደ
ላሉ ፤ ሌሎችም ተማርከው ወደየአገሩ ይወሰ
ዳሉ ። የአረማውያን ዘመን እስኪፈጸም ድረስ
ኢየሩሳሌም በአረማውያን የተረገጠች ትሆና
ለች ።”

የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት
(ማቴ. 24፥29-31፤ ማር. 13፥24-27)

25 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በፀሐ
ይና በጨረቃ ፥ በከዋክብትም ላይ ድንቅ ምልክ
ቶች ይታያሉ ፤ በምድርም ላይ ሕዝቦች ሁሉ
ከባሕርና ከማዕበሉ አስደንጋጭ ድምፅ የተነሣ
ፈርተው ይጨነቃሉ ። 26 በዓለም ላይ የሚመጣ
ውን ነገር በመጠባበቅ ሰዎች በፍርሃት ይሸበ
ራሉ ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የሰማይ ኀይ
ሎች ይናወጣሉ ፤ 27 ከዚህም በኋላ የሰው ልጅ
በታላቅ ኀይልና ክብር በደመና ላይ ሆኖ
ሲመጣ ይታያል ። 28 ይህ ሁሉ መሆን በሚጀም
ርበት ጊዜ ደኅንነታችሁ ቀርቦአልና ቀና ብላ
ችሁ ወደ ላይ ተመልከቱ ።”

የበለስ ዛፍ ምሳሌ
(ማቴ. 24፥32-35፤ ማር. 13፥28-31)

29 ቀጥሎም ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ነገራ
ቸው ፥ “የበለስን ዛፍና የሌሎችንም ዛፎች
ሁኔታ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ፤ 30 ቅጠሎቻ
ቸው ሲያቈጠቍጡ ባያችሁ ጊዜ ጸደይ እንደቀ
ረበ ታውቃላችሁ ። 31 በዚህ ዐይነት ይህ ሁሉ
ነገር መሆን ሲጀምር ባያችሁ ጊዜ የእግዚአብ
ሔር መንግሥት ልትመጣ መቃረብዋን ዕወቁ ።
32 “በእውነት እላችኋለሁ ፥ ይህ ሁሉ እስኪ
ፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም ። 33 ሰማ
ይና ምድር ያልፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል ።”

ተግቶ ስለመጠበቅ

34 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በመብ
ልና በመጠጥ ብዛት በስካርም በመባከንና ስለ
ዓለማዊ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝል
ተጠንቀቁ ። አለበለዚያ ያ ቀን እንደ ወጥመድ
በድንገት ይመጣባችኋል ። 35 ምክንያቱም ያ
ቀን በምድር ላይ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ በድ
ንገት ያጠምዳቸዋል ። 36 ስለዚህ ከሚመጣው
ክፉ ነገር ሁሉ ለማምለጥ ኀይል እንድታገኙና
በሰው ልጅ ፊት ለመቆም እንድትችሉ እየጸለያ
ችሁ ዘወትር ትጉ ።”
37 ኢየሱስ በየቀኑ በቤተ መቅደስ ያስተምር
ነበር ፤ ሲመሽ ግን ደብረ ዘይት ወደምትባል
ተራራ ላይ እየወጣ ያድር ነበር ። 38 ሰዎቹ
ሁሉ ኢየሱስን ለመስማት ጠዋት በማለዳ ወደ
ቤተ መቅደስ ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር ።

21፥14-15 ፦ ሉቃ. 12፥11-12 ። 21፥22 ፦ ሆሴዕ 9፥7 ። 21፥25 ፦ ኢሳ. 13፥10 ፤ ሕዝ. 32፥7 ፤ ኢዩ. 2፥31 ፤ ራእ. 6፥12-13 ። 21፥27 ፦ ዳን. 7፥13 ፤ ራእ. 1፥7 ። 21፥37 ፦ ሉቃ. 19፥47 ።

## ምዕራፍ 22

### በክርስቶስ ላይ የተደረገ ሤራ
(ማቴ. 26፡1-5፤ ማር. 14፡1-2፤ ዮሐ. 11፡45-53)

1 ፋሲካ የተባለው የቂጣ በዓል የሚከበርበት
ቀን ተቃርቦ ነበር ፤ 2 የካህናት አለቆችና የሙሴ
ሕግ መምህራን ሕዝቡን ስለፈሩ ኢየሱስን ይዘው
የሚገድሉበትን ዘዴ በስውር ይፈልጉ ነበር ።

### ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ
(ማቴ. 26፡14-16፤ ማር. 14፡10-11)

3 በዚያን ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ በሆነው
በአስቆሮታዊው ይሁዳ ሰይጣን ገባበት ። 4 ስለ
ዚህ ይሁዳ ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ቤተ
መቅደስ ዘብ አዛዦች ሄዶ ኢየሱስን እንዴት
አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ከእነርሱ ጋር ተነጋ
ገረ ። 5 እነርሱም በነገሩ ተደስተው ገንዘብ ሊሰ
ጡት ተዋዋሉ ። 6 በውሉ ተስማምቶ ሕዝቡ ሳያ
ውቅ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ምቹ ጊዜ
ይፈልግ ነበር ።

### ኢየሱስ የአይሁድን የፋሲካ ራት ለመብላት ተዘጋጀ
(ማቴ. 26፡17-25፤ ማር. 14፡12-21፤
ዮሐ. 13፡21-30)

7 ከዚህ በኋላ የፋሲካ በግ የሚታረድበት
የቂጣ በዓል ደረሰ ። 8 ኢየሱስ "የፋሲካውን
ራት እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን" ሲል ጴጥ
ሮስንና ዮሐንስን ላካቸው ።
9 እነርሱም "የፋሲካውን ራት የት እንድናዘ
ጋጅ ትፈልጋለህ?" ሲሉ ጠየቁት ።
10 እርሱም እንዲህ አላቸው ፤ "በፊታችሁ
ወዳለችው ከተማ ስትገቡ እነሆ የውሃ እንሥራ
የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ፤ እርሱን ተከትላ
ችሁ ወደሚገባበት ቤት ሂዱ ። 11 የቤቱንም
ጌታ 'መምህራችን ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲ
ካን ራት የምበላበት ቤት የት ነው? ይልሃል'
በሉት ። 12 እርሱም በሰገነት ላይ ያለውን ተን
ጥፎ የተዘጋጀ ሰፊ አዳራሽ ያሳያችኋል ፤ በዚያ
አዘጋጁ ።"
13 ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ሄደው ሁሉ
ነገር ልክ ኢየሱስ እንዳላቸው ሆኖ አገኙ ፤ የፋ
ሲካውንም ራት በዚያ አዘጋጁ ።

### የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት (የጌታ ራት)
(ማቴ. 26፡26-30፤ ማር. 14፡22-26፤
1 ቆሮ. 11፡23-25)

14 የራት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ከሐዋር
ያት ጋር በማእድ ተቀመጠ ። 15 እንዲህም አላ
ቸው ፤ "መከራ ከመቀበሌ በፊት ከእናንተ ጋር
ይህን የፋሲካ ራት ለመብላት እጅግ እመኝ
ነበር ፤ 16 የዚህ ነገር እውነተኛ ምስጢር በእግ
ዚአብሔር መንግሥት ፍጹም ሆኖ እስኪገለጥ
ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ ይህን የፋሲካ ራት ከቶ
አልበላም እላችኋለሁ ።"
17 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጽዋውን አንሥቶ
የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ እንዲህም አለ ፤ "እን
ካችሁ ይህንን ተካፈሉ ፤ 18 በእውነት እላችኋ
ለሁ ከአሁን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት
እስከትመጣ ድረስ ከዚህ የወይን ፍሬ ጭማቂ
አልጠጣም ።"
19 ቀጥሎም ኢየሱስ ኅብስት አንሥቶ የምስ
ጋና ጸሎት አደረገ ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ
"እንካችሁ ፤ ይህ ለእናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ
ነው ፤ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት" ብሎ ሰጣ
ቸው ። 20 እንዲሁም ከራት በኋላ ጽዋውን አን
ሥቶ ሰጣቸውና እንዲህ አላቸው ፤ "ይህ ጽዋ
ስለ እናንተ በሚፈስሰው ደሜ የሚፈጸም አዲስ
ኪዳን ነው ።
21 "ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ
እነሆ ከእኔ ጋር በማእድ ነው ። 22 የሰው ልጅ
ስለ እርሱ አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ወደ
ሞት መሄዱ አይቀርም ፤ ዳሩ ግን የሰውን ልጅ
አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት!"
23 እነርሱም "ከእኛ መካከል ይህን ነገር
የሚያደርግ የትኛው ነው!" በማለት እርስ በር
ሳቸው ተጠያየቁ ።

### ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

24 ቀጥሎም እነርሱ "ከሁላችን የሚበልጥ
ማን ነው?" እያሉ እርስ በርሳቸው ይከራከሩ
ጀመር ። 25 ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው ፤
"የዚህ ዓለም ነገሥታት በሕዝቡ ላይ ሥልጣን
አላቸው ፤ ገዥዎችም የሕዝቡ በጎ አድራጊዎች
ይባላሉ ፤ 26 እናንተ ግን እንደ እነርሱ ልትሆኑ
አይገባም ፤ ይልቅስ ከእናንተ መካከል ትልቅ
የሆነ እንደ ትንሽ ይሁን ፤ አለቃ የሆነም እንደ
አገልጋይ ይሁን ። 27 በማእድ ተቀምጦ ከሚመገ
በውና ቆሞ ከሚያገለግለው የትኛው ነው
ትልቅ? ትልቅ የሚባለው በማእድ የተቀመ
ጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደ
አገልጋይ ነኝ ። 28 እናንተ በመከራዬ ጊዜ ሁሉ
ከእኔ ጋር ጸንታችሁ ቆይታችኋል ። 29 ስለዚህ
አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔም እናንተን እሾ
ማችኋለሁ ። 30 በመንግሥቴም በማእድ ተቀም
ጣችሁ ትበላላችሁ ፤ ትጠጣላችሁ ፤ በዙፋን
ላይ ተቀምጣችሁ ፤ በዐሥራ ሁለቱም የእስራ
ኤል ነገዶች ላይ ተሾማችሁ ትፈርዳላችሁ ።"

22፡1 ፡- ዘጸ. 12፡1-27 ። 22፡20 ፡- ኤር. 31፡31-34 ። 22፡21 ፡- መዝ. 41፡9 ። 22፡24 ፡- ማቴ. 18፡1 ፤ ማር. 9፡34 ፤ ሉቃ. 9፡46 ። 22፡25-26 ፡- ማቴ. 20፡25-27 ፤ ማር. 10፡42-44 ። 22፡26 ፡- ማቴ. 23፡11 ፤ ማር. 9፡35 ። 22፡27 ፡- ዮሐ. 13፡12-15 ። 22፡30 ፡- ማቴ. 19፡28 ።



### ኢየሱስ የጴጥሮስን መካድ አስቀድሞ ተናገረ
(ማቴ. 26፡31-35፤ ማር. 14፡27-31፤
ዮሐ. 13፡36-38)

31 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፤ "ስምዖን!
ስምዖን! እነሆ ገበሬ ስንዴውን ከገለባ አበጥሮ
እንደሚለይ እንዲሁም ሰይጣን እናንተን ሊያበ
ጥራችሁ ወይም ሊፈትናችሁ ተመኘ ። 32 ነገር
ግን የአንተ እምነት እንዳይጠፋ እኔ ጸልያለሁ ፤
አንተም ተጸጽተህ ወደ እኔ በተመለስህ ጊዜ
ወንድሞችህን አጽና ።"
33 ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ! ለእስራትም ሆነ
ለሞት ከአንተ ጋር አብሬ ለመሄድ ዝግጁ
ነኝ!" አለ ።
34 ኢየሱስ ግን "ጴጥሮስ ሆይ! ዛሬ ዶሮ ሳይ
ጮኽ 'አላውቀውም' ብለህ ሦስት ጊዜ ትክደኛ
ለህ እልሃለሁ" አለው ።
35 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
"የገንዘብ ቦርሳ ከረጢት ፤ ጫማም ሳትይዙ በላ
ክሁአችሁ ጊዜ የጐደለባችሁ ነገር ነበርን?"
አላቸው ።
እነርሱም "ምንም የጐደለብን ነገር አልነበ
ረም" ሲሉ መለሱለት ።
36 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፤ "አሁን ግን
የገንዘብ ቦርሳም ሆነ ከረጢት ያለው ይያዝ ፤
ሰይፍም የሌለው ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ ።
37 'ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ!' የሚለው የመጽ
ሐፍ ቃል በእኔ ላይ መፈጸም አለበት ፤ እላችኋ
ለሁ ፤ ምክንያቱም ስለ እኔ አስቀድሞ የተጻፈው
ሁሉ መፈጸም ስለሚገባው ነው ።"
38 ደቀ መዛሙርቱም "ጌታ ሆይ! እነሆ
እዚህ ሁለት ሰይፎች አሉ!" አሉት ።
እርሱም "ይበቃል!" አላቸው ።

### ኢየሱስ በደብረ ዘይት ጸለየ
(ማቴ. 26፡36-46፤ ማር. 14፡32-42)

39 ኢየሱስ ከከተማ ወጥቶ እንደ ልማዱ ወደ
ደብረ ዘይት ሄደ ፤ ደቀ መዛሙርቱም አብረ
ውት ሄዱ ። 40 እዚያም በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ
"ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ" አላቸው ።
41 ከዚህ በኋላ የድንጋይ ውርወራ ያህል ከእ
ነርሱ ራቅ ብሎ ሄደ ፤ ተንበርክኮም እንዲህ
ሲል ጸለየ ፤ 42 "አባት ሆይ! ፈቃድህ ቢሆን
ይህን የመከራ ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ ፤ ግን የአ
ንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይ
ሁን ።" 43 በዚያን ጊዜ የሚያበረታው መልአክ
ከሰማይ መጥቶ ታየው ። 44 ልቡም በጣም ተጨ
ንቆ በብርቱ ይጸልይ ነበር ፤ ላቡም እንደ ደም
ሆኖ ወደ መሬት ይንጠባጠብ ነበር ። ↠
45 ከጸሎቱ ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
መጣ ፤ ከሐዘን ብዛት የተነሣ ተኝተው አገኛቸ
ውና እንዲህ አላቸው ፤ 46 "ስለምን ትተኛላ
ችሁ? ይልቅስ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሡና
ጸልዩ ።"

### ኢየሱስ በጠላቶቹ እጅ ተያዘ
(ማቴ. 26፡47-56፤ ማር. 14፡43-50፤
ዮሐ. 18፡3-11)

47 ኢየሱስ ይህን ሲናገር ሳለ እነሆ ብዙ
ሰዎች መጡ ፤ መሪያቸው ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
የሆነው ይሁዳ ነበር ፤ ይሁዳ ሊስመው ወደ
ኢየሱስ ቀረበ ። 48 ኢየሱስ ግን "ይሁዳ ሆይ!
የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህን?"
አለው ።
49 ከኢየሱስ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርት
የነገሩን ሁኔታ ባዩ ጊዜ "ጌታ ሆይ! በሰይፍ
እንምታቸውን?" አሉ ። 50 ከእነርሱም አንዱ
የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ በሰይፍ መታና ቀኝ
ጆሮውን ቈረጠ ።
51 ኢየሱስ ግን "ይህስ አያስፈልግም!
ተዉ!" አለ ፤ የሰውየውንም ጆሮ ዳስሶ አዳ
ነው ።
52 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሊይዙት የመጡትን
የካህናት አለቆች የቤተ መቅደስ አዛዦችንና
የሕዝብ ሽማግሌዎችንም እንዲህ አላቸው ፤
"እኔን እንደ ወንበዴ ልትይዙ ሰይፍና ዱላ ይዛ
ችሁ መጣችሁን? 53 በየቀኑ በቤተ መቅደስ ከእ
ናንተ ጋር ስገኝ አልያዛችሁኝም ነበር ፤ አሁን
ግን የእናንተ ጊዜና የጨለማው ሥልጣን ጊዜ
ነው ።"

### ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ
(ማቴ. 26፡57-58፡69-75፤
ማር. 14፡53-54፡66-72፤
ዮሐ. 18፡12-18፡25-27)

54 ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ኢየሱስን ይዘው ወሰዱ
ትና ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት አመጡት ፤ ጴጥሮ
ስም ራቅ ብሎ ይከተለው ነበር ። 55 ሰዎቹ በግ
ቢው ውስጥ እሳት አቀጣጥለው በአንድነት ተቀ
ምጠው ነበር ። ጴጥሮስም መጥቶ አብሮ ተቀ
መጠ ። 56 ጴጥሮስ በእሳቱ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ
አንዲት ልጃገረድ አየችው ፤ ወደ እርሱ ትኵር
ብላ ተመልክታም "ይህም እኮ ከኢየሱስ ጋር
ነበር!" አለች ። 57 ጴጥሮስ ግን "አንቺ ሴት!
እኔ አላውቀውም" ሲል ካደ ። 58 ከጥቂት ጊዜ
በኋላ አንድ ሌላ ሰው ጴጥሮስን አየውና "አን
ተም እኮ ከእነርሱ አንዱ ነህ!" አለው ።
ጴጥሮስ ግን "አንተ ሰው! አይደለሁም!"
አለ ።

22፡35 ፡- ማቴ. 10፡9-10 ፤ ማር. 6፡8-9 ፤ ሉቃ. 9፡3 ፤ 10፡4 ። 22፡37 ፡- ኢሳ. 53፡12 ።
22፡53 ፡- ሉቃ. 19፡47 ፤ 21፡37 ።

59 አንድ ሰዓት ያህል ቆይቶም አንድ ሌላ
ሰው ጴጥሮስን "ይህ ሰው ገሊላዊ ነውና በእር
ግጥ ከእርሱ ጋር ነበረ!" በማለት አጥብቆ ተና
ገረ ።
60 ጴጥሮስ ግን "አንተ ሰው! የምትለውን
አላውቅም!" አለ ።
ይህን ሲናገር ሳለ ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ ።
61 በዚህ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ዞር ብሎ ጴጥሮስን
አየው ፤ ጴጥሮስም "ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ" በማለት ጌታ ኢየሱስ የተናገረ
ውን ቃል አስታወሰ ። 62 ወደ ውጪ ወጥቶም
ምርር ብሎ አለቀሰ ።
63 በዚያን ጊዜ ኢየሱስን ይዘውት የነበሩ
ሰዎች በኢየሱስ ላይ ያፌዙበትና ይደበድቡትም
ነበር ። 64 ፊቱንም እየሸፈኑ "ማን ነው የመ
ታህ? ነቢይ ከሆንህ እስቲ ዕወቅ" ይሉት
ነበር ። 65 ብዙ ነገር እየተናገሩ ይሰድቡት
ነበር ።

ኢየሱስ ወደ ፍርድ ሸንጎ ቀረበ
(ማቴ. 26፥59-66፤ ማር. 14፥55-64፤
ዮሐ. 18፥19-24)

66 በነጋ ጊዜም የሕዝብ ሽማግሌዎች ፥ የካህ
ናት አለቆችና የሙሴ ሕግ መምህራን በአንድ
ነት ተሰበሰቡ ፤ ኢየሱስንም ወደ ሸንጎአቸው
አመጡት ። 67 እንዲህም አሉት ፥ "እስቲ ንገ
ረን! አንተ መሲሕ ነህን?"
እርሱ ግን እንዲህ አላቸው ፥ "ብነግራችሁ
አታምኑኝም ፤ 68 ጥያቄም ባቀርብላችሁ አትመ
ልሱልኝም ፤ 69 ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው
ልጅ በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ይቀመጣል ።"
70 ሁሉም በአንድነት "ታዲያ አንተ የእግዚ
አብሔር ልጅ ነህን?" ሲሉ ጠየቁት ።
እርሱም "አዎ እናንተ እንዳላችሁት ነኝ"
አላቸው ።
71 እነርሱም "እንግዲህ ምን ምስክር ያስፈ
ልገናል? እነሆ ከአፉ የወጣውን ቃል እኛ ራሳ
ችን ሰምተናል!" አሉ ።

## ምዕራፍ 23

ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ቀረበ
(ማቴ. 27፥1-2፤11-14፤ ማር. 15፥1-5፤
ዮሐ. 18፥28-38)

1 የሸንጎው አባሎች ሁሉ ተነሥተው ኢየሱ
ስን ወሰዱትና በጲላጦስ ፊት አቀረቡት ፤ 2 እን
ዲህ እያሉም ይከስሱት ጀመር ፥ "ይህ ሰው
ሕዝባችንን ሲያስት አገኘነው ፤ ለሮም ንጉሠ
ነገሥት ለቄሳር ግብር እንዳይሰጥ ይከለክላል ፤
ደግሞ 'እኔ ንጉሥ መሲሕ ነኝ' እያለ ይናገ
ራል ።"
3 ጲላጦስም "አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን?" ሲል ኢየሱስን ጠየቀው ።
ኢየሱስም "አዎ አንተ እንዳልኸው ነኝ"
አለው ።
4 በዚያን ጊዜ ጲላጦስ ለካህናት አለቆችና
ለሕዝቡም "በዚህ ሰው ምንም በደል አላገኘሁ
በትም!" አለ ።
5 እነርሱ ግን "ይህ ሰው ከገሊላ ጀምሮ እስ
ከዚህ ድረስ በይሁዳ አገር ሁሉ እያስተማረ
ሕዝቡን ለሁከት ያስነሣል" እያሉ በጥብቅ ከሰ
ሱት ።

ኢየሱስ በሄሮድስ ፊት ቀረበ

6 ጲላጦስም ገሊላ የሚለውን ቃል በሰማ
ጊዜ "ይህ የገሊላ ሰው ነውን?" ብሎ ጠየቀ ።
7 ኢየሱስ የመጣው ከሄሮድስ ግዛት መሆኑን
ጲላጦስ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ላከው ፤ ሄሮድ
ስም በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበር ። 8 ሄሮ
ድስ ኢየሱስን ባየ ጊዜ እጅግ ደስ አለው ፤ ምክ
ንያቱም ስለ ኢየሱስ ይሰማ ነበርና ሊያየው
ብዙ ጊዜ ይመኝ ነበር ፤ እንዲሁም ኢየሱስ
ተአምር ሲያደርግ ለማየት ተስፋ ያደርግ
ነበር ። 9 ስለዚህ ሄሮድስ ኢየሱስን ብዙ ጥያቄ
ጠየቀው ፤ ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰለ
ትም ። 10 የካህናት አለቆችና የሙሴ ሕግ መም
ህራን እዚያ ቆመው በብርቱ ይከስሱት ነበር ።
11 ሄሮድስም ከጭፍሮቹ ጋር ሆኖ በንቀት አፌዘ
በት ፤ ጌጠኛ ልብስ አልብሶም ወደ ጲላጦስ
መልሶ ላከው ። 12 በዚያን ቀን ሄሮድስና ጲላ
ጦስ ወዳጆች ሆኑ ፤ ከዚያ በፊት ግን ጠበኞች
ነበሩ ።

ኢየሱስ የሞት ፍርድ ተፈረደበት
(ማቴ. 27፥15-26፤ ማር. 15፥6-15፤
ዮሐ. 18፥39-40፤ 19፥1-16)

13 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ የካህናት አለቆችን ፥
የሕዝብ መሪዎችንና ሕዝቡንም ጭምር በአንድ
ነት ጠራ ፤ 14 እንዲህም አላቸው ፥ "'ሕዝቡን
ለሁከት ያነሣሣል!' ብላችሁ ይህን ሰው ወደ
እኔ አመጣችሁት ፤ እኔም እነሆ በፊታችሁ መር
ምሬው ካቀረባችሁበት ክስ ሁሉ በዚህ ሰው
ላይ ምንም በደል አላገኘሁበትም ። 15 እንዲ
ሁም ሄሮድስ ምንም በደል ስላላገኘበት ወደ
እኛ መልሶ ልኮታል ፤ እንግዲህ ይህ ሰው
ለሞት የሚያደርሰው ምንም ነገር አላደረገም ።
16 ስለዚህ በግርፋት እንዲቀጣ አድርጌ እለቅቀ
ዋለሁ ።" [17 በየዓመቱ በፋሲካ በዓል ጲላጦስ
አንድ እስረኛ ለሕዝቡ መፍታት ነበረበት ።][7*]
18 ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ "ይህን ሰው አስወግ
ደው! በርባንን ግን ፍታልን!" እያሉ ጮኹ ።
19 በርባን በከተማ ውስጥ ብጥብጥ በማስነሣትና

[7*] 23፥17 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 17 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በማር. 15፥6 ያለውን ይመስላል ።



ሰው በመግደል ምክንያት በወህኒ ቤት የታሰረ
ሰው ነበር ።
20 ጲላጦስ ኢየሱስን ፈትቶ ሊለቀው ፈልጎ
እንደገና ለሕዝቡ ተናገረ ። 21 ሕዝቡ ግን "ስቀ
ለው! ስቀለው!" እያለ ጮኸ ።
22 ጲላጦስም ሦስተኛ ጊዜ እንዲህ አላ
ቸው ፥ "ይህ ሰው ያደረገው በደል ከቶ ምንድን
ነው? እኔ ለሞት የሚያደርስ ምንም ነገር አላገ
ኘሁበትም ፤ ስለዚህ በግርፋት እንዲቀጣ አድ
ርጌ እለቅቀዋለሁ ።"
23 እነርሱ ግን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
"ስቀለው!" እያሉ ጮኹ ፤ ጩኸታቸውም
በረታ ። 24 በዚህም ምክንያት የጠየቁት እንዲደ
ረግላቸው ጲላጦስ ፈረደ ። 25 ብጥብጥ በማስነሣ
ትና ሰው በመግደል ታስሮ የነበረውን በርባንን
በጥያቄአቸው መሠረት ለቀቀው ፤ ኢየሱስን ግን
እንደፈለጉት አሳልፎ ሰጣቸው ።

ኢየሱስ ተሰቀለ
(ማቴ. 27፥32-44፤ ማር. 15፥21-32፤
ዮሐ. 19፥17-27)

26 ስለዚህ ኢየሱስን ወሰዱት ፤ ይዘውት
ሲሄዱ ሳሉም የቀሬና ሰው የሆነውን ስምዖንን
ከገጠር ወደ ከተማ ሲገባ አገኙት ፤ እርሱን
ይዘው የኢየሱስን መስቀል አሸከሙትና ኢየሱ
ስን እንዲከተል አደረጉት ።
27 ብዙ ሰዎችም ኢየሱስን ይከተሉ ነበር ፤
ከእነርሱም መካከል በብርቱ አዝነው የሚያለቅ
ሱለት ሴቶች ነበሩ ። 28 ኢየሱስ ግን ወደ እነ
ርሱ መለስ ብሎ እንዲህ አላቸው ፥ "እናንተ
የኢየሩሳሌም ሴቶች! ስለ ራሳችሁና ስለ ልጆቻ
ችሁ አልቅሱ እንጂ ስለ እኔ አታልቅሱ! 29 ምክ
ንያቱም 'መኻኖች የሆኑ ሴቶች ፥ ያልወለዱ
ማሕፀኖችና ያላጠቡ ጡቶች እንዴት የታደሉ
ናቸው!' የሚባልበት ቀን ይመጣል ። 30 በዚያን
ጊዜ ሰዎች ተራራዎችን ፥ 'በላያችን ውደቁ!'
ኮረብቶችንም ፥ 'ሸሽጉን!' ማለት ይጀምራሉ ።
31 እንግዲህ ይህ ሁሉ ነገር በእርጥብ እንጨት
ላይ የሚደረግ ከሆነ በደረቅ እንጨት ላይማ
ምን ይደረግ ይሆን?" 32 እንዲሁም ከኢየሱስ
ጋር የሚገደሉትን ሁለት ወንጀለኞች ይዘው
ሄዱ ። 33 ቀራንዮ ወይም የራስ ቅል ወደ ተባለ
ስፍራም በደረሱ ጊዜ በዚያ ኢየሱስን ሰቀሉት ፤
እንዲሁም ሁለቱን ወንጀለኞች በኢየሱስ ግራና
ቀኝ ሰቀሉአቸው ። 34 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ
"አባት ሆይ! የሚያደርጉትን ስለማያውቁ
ይቅር በላቸው!" አለ ።
ወታደሮቹም ዕጣ ተጣጥለው የኢየሱስን
ልብስ ተከፋፈሉ ። 35 ሕዝቡ ቆሞ ይመለከት
ነበር ፤ የአይሁድ አለቆችም "ሌሎችንስ አዳነ
እንግዲህ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው
መሲሕ ከሆነ እስቲ ራሱን ያድን!" እያሉ ያፌ
ዙበት ነበር ።
36 ወታደሮቹም እንዲሁ አፌዙበት ፤ ወደ
እርሱም ቀርበው ሆምጣጤ ሰጡት ። 37 እንዲ
ሁም "አንተ የአይሁድ ንጉሥ ከሆንህ እስቲ
ራስህን አድን" ይሉት ነበር ።
38 "ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው!" የሚል
ጽሑፍም በኢየሱስ ራስጌ በመስቀሉ ላይ
አኖሩ ።

ከኢየሱስ ጋር የተሰቀሉት ሁለት ወንጀለኞች
(ማቴ. 27፥38-44፤ ማር. 15፥27-32)

39 ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉት ወንጀለኞች
አንዱ ኢየሱስን "አንተ መሲሕ አይደለህምን?
እስቲ በል ራስህንና እኛን አድን!" እያለ ይሰድ
በው ነበር ።
40 ሌላው ወንጀለኛ ግን እንዲህ ብሎ ገሠ
ጸው ፥ "አንተ ደግሞ በሞት ፍርድ ላይ እያለህ
እንኳ እግዚአብሔርን አትፈራምን? 41 እኛ ባደ
ረግነው በደል ምክንያት ቅጣት መቀበላችን
የተገባ ፍርድ ነው ፤ ይህ ሰው ግን ምንም
ጥፋት አላደረገም ።" 42 ቀጥሎም ኢየሱስን
"ጌታ ሆይ! ወደ መንግሥትህ ስትገባ አስታው
ሰኝ!" አለው ።
43 ኢየሱስም "በእውነት እልሃለሁ ፥ ዛሬ
ውኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ!" አለው ።

ኢየሱስ ሞተ
(ማቴ. 27፥45-56፤ ማር. 15፥33-41፤
ዮሐ. 19፥28-30)

44 እነሆ ይህ የሆነው ከቀኑ ስድስት ሰዓት
ገደማ ነበር ፤ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ድረስ የፀሐይ ብርሃን ተጋርዶ በምድር
ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ ። 45 የቤተ መቅደስ መጋ
ረጃም ከመካከሉ ተቀድዶ ከሁለት ተከፈለ ።
46 ኢየሱስም ድምፁን ከፍ አድርጎ "አባት
ሆይ! እነሆ ነፍሴን በእጅህ አስረክባለሁ!"
አለ ፤ ይህንንም ካለ በኋላ ነፍሱ ከሥጋው ተለ
የች ።
47 በዚያ የነበረው መቶ አለቃ የሆነውን
ነገር ባየ ጊዜ "በእርግጥ ይህ ሰው ጻድቅ ኖሮ
አል!" ብሎ እግዚአብሔርን አከበረ ።
48 ነገሩን ለመመልከት እዚያ ተሰብስበው
የነበሩ ሰዎች ሁሉ የሆነውን ነገር ባዩ ጊዜ በማ
ዘን ደረታቸውን እየመቱ ወደየቤታቸው ተመ
ለሱ ። 49 ኢየሱስን በቅርብ ያውቁት የነበሩ
ሰዎች ሁሉና ከገሊላ ጀምሮ ይከተሉት የነበሩ
ሴቶችም በሩቅ ቆመው ይህን ነገር ይመለከቱ
ነበር ።

23፥30 ፦ ሆሴዕ 10፥8 ፤ ራእ. 6፥16 ። 23፥34 ፦ መዝ. 22፥18 ። 23፥35 ፦ መዝ. 22፥7 ። 23፥36 ፦ መዝ. 69፥21 ።
23፥45 ፦ ዘጸ. 26፥31-33 ። 23፥46 ፦ መዝ. 31፥5 ። 23፥49 ፦ ሉቃ. 8፥2-3 ።

### ኢየሱስ ተቀበረ
(ማቴ. 27፥57-61፤ ማር. 15፥42-47፤
ዮሐ. 19፥38-42)

50የአይሁድ ከተማ በሆነችው በአርማትያስ
የሚኖር ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበረ፤ እርሱ ጻድ
ቅና ደግ ሰው ነበረ፤ የአይሁድ ሸንጎ አባልም
ነበረ። 51ይሁን እንጂ በአይሁድ ምክርና ሤራ
አልተባበረም፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት
በተስፋ የሚጠባበቅ ሰው ነበረ። 52ይህ ሰው
ወደ ጲላጦስ ፊት ቀርቦ የኢየሱስን አስከሬን
እንዲሰጠው ጠየቀ። 53አስከሬኑንም አውርዶ
በቀጭን ሐር ልብስ ከፈነው፤ ማንም ሰው ባል
ተቀበረበት ከአለት ተወቅሮ በተዘጋጀ መቃብር
ውስጥ ቀበረው፤ 54ይህንንም ያደረገው ዓርብ
ማታ ለሰንበት ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ
ነበር።
55ከገሊላ ኢየሱስን ተከትለው የመጡ ሴቶች
ከዮሴፍ ጋር ሄደው መቃብሩን አዩ፤ አስከሬ
ኑም እንዴት እንደተቀበረ ተመለከቱ። 56ወደ
ቤታቸውም ተመልሰው ለአስከሬን የሚሆኑ ከር
ቤና ሽቶ አዘጋጁ፤ በሙሴ ሕግ መሠረት በሰን
በት ቀን ዐርፈው ዋሉ።

## ምዕራፍ 24

### ኢየሱስ ከሞት ተነሣ
(ማቴ. 28፥1-10፤ ማር. 16፥1-8፤ ዮሐ. 20፥1-10)

1ሴቶቹ ያዘጋጁትን ሽቶ ይዘው እሑድ
ጠዋት በማለዳ ወደ መቃብሩ ሄዱ፤ 2መቃብሩ
የተዘጋበትን ድንጋይ ከመቃብሩ ወዲያ ተንከ
ባሎ አገኙት። 3ወደ ውስጥ በገቡ ጊዜ ግን
የጌታ ኢየሱስን አስከሬን አላገኙም። 4ስለዚ
ህም ነገር በመገረም ላይ ሳሉ እነሆ የሚያንጸባ
ርቅ ብሩህ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት
መጥተው በአጠገባቸው ቆሙ። 5ሴቶቹም
እጅግ ፈርተው ወደ መሬት አቀርቅረው ሳሉ
ሰዎቹ እንዲህ አሉአቸው፤ “ሕያው የሆነውን
ኢየሱስን በሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታ
ላችሁ? 6እርሱ እዚህ የለም፤ ተነሥቶአል፤
በገሊላ በነበረበት ጊዜ የነገራችሁን አስታውሱ፤
7‘የሰው ልጅ ለኃጢአተኞች ተላልፎ መሰ
ጠት፥ መሰቀልና በሦስተኛውም ቀን ከሞት
መነሣት ይገባዋል’ ብሎአችሁ ነበር።”
8ሴቶቹም የኢየሱስን ቃል አስታወሱ፤
9ከመቃብርም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለዐሥራ
አንዱና ለቀሩትም ነገሩአቸው፤ 10ይህን ለሐዋ
ርያት የተናገሩት መግደላዊት ማርያም፥ ዮሐ
ናና የያዕቆብ እናት ማርያም እንዲሁም ሌሎች
ሴቶች ነበሩ። 11እነርሱ ግን ይህ ነገር ቅዠት
ስለመሰላቸው አላመኑአቸውም። 12ነገር ግን
ጴጥሮስ ተነሥቶ ወደ መቃብሩ ሮጠ፤ እዚያም
ሲደርስ ጐንበስ ብሎ በተመለከተ ጊዜ አስከሬኑ
የተከፈነበትን ቀጭን የሐር ልብስ ብቻ አየ፤
በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤት ተመለሰ።

### ኢየሱስ ለሁለት ደቀ መዛሙርት ተገለጠ
(ማር. 16፥12-13)

13በዚያኑ ቀን ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት
ሁለቱ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ነበር፤ ኤማሁስ
ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል
ርቃ የምትገኝ መንደር ናት። 14እነርሱም
ይህን የሆነውን ነገር ሁሉ አንሥተው እርስ በእ
ርሳቸው ይወያዩ ነበር። 15ይህንንም በሚያወሩ
በትና በሚወያዩበት ጊዜ ኢየሱስ ራሱ ወደ እነ
ርሱ ቀርቦ አብሮአቸው ይጓዝ ጀመር። 16ነገር
ግን በዐይናቸው እያዩት ማን እንደሆነ ማወቅ
አልቻሉም። 17እርሱም “በጕዞው ላይ ሳላችሁ
የምትነጋገሩበት ይህ ነገር ምንድን ነው?” አላ
ቸው።
እነርሱም እያዘኑ ቀጥ ብለው ቆሙ። 18ከእ
ነርሱም አንዱ ቀለዮጳ የሚባለው “በኢየሩሳ
ሌም ከተማ ሆነህ በእነዚህ ቀኖች በዚያ የተፈጸ
መውን ነገር ሁሉ የማታውቅ አንተ ብቻ
ነህን?” አለ።
19ኢየሱስም “ምንድን ነው እርሱ?” አላ
ቸው። እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤
“በናዝሬቱ ኢየሱስ ላይ ስለተፈጸመው ነገር
ነዋ! እርሱ በእግዚአብሔርና በሰዎች ሁሉ ፊት
በቃልና በሥራ ብርቱ የሆነ ነቢይ ነበር።
20የካህናት አለቆችና መሪዎቻችን ለሞት
ፍርድ አሳልፈው ከሰጡት በኋላ ሰቀሉት።
21እኛ ግን ‘እስራኤልን የሚያድን እርሱ ነው’
ብለን ተስፋ አድርገን ነበር። ይሁን እንጂ ይህ
ሁሉ ነገር ከተፈጸመ እነሆ ዛሬ ሦስተኛ ቀኑ
ነው። 22እንዲያውም በእኛ መካከል ያሉ አንዳ
ንድ ሴቶች አስገርመውናል፤ እነርሱ ዛሬ በማ
ለዳ ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር፤ 23ነገር ግን
የእርሱን አስከሬን አላገኙም፤ ‘ሕያው ሆኖ
አል!’ የሚሉ የመላእክትን መልክ አየን እያ
ሉም ተመልሰው መጡ። 24ከእኛም አንዳን
ዶቹ ወደ መቃብሩ ሄደው ልክ ሴቶቹ እንዳ
ሉት ሆኖ አገኙ፤ ኢየሱስን ግን አላዩትም።”
25ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ
የማታስተውሉና ነቢያት የተናገሩትንም ሁሉ
ከማመን የዘገያችሁ! 26መሲሕ ይህንን ሁሉ
መከራ መቀበልና ወደ ክብሩ መግባት ይገባው
የለምን?” 27ከዚህ በኋላ ከሙሴና ከነቢያት
መጻሕፍት ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ
ስለ እርሱ የተነገረውን እየጠቀሰ አስረዳቸው።

23፥56 ፦ ዘጸ. 20፥10፤ ዘዳ. 5፥14። 24፥6-7 ፦ ማቴ. 16፥21፤ 17፥22-23፤ 20፥18-19፤ ማር. 8፥31፤ 9፥31፤ 10፥33-34፤ ሉቃ. 9፥22፤ 18፥31-33።



28እነርሱ ወደሚሄዱበት መንደር በቀረቡ
ጊዜ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ። 29እነርሱ
ግን “ቀኑ መሽቶአል፤ ፀሐይም መጥለቅዋ
ነው፤ ስለዚህ ከእኛ ጋር እዚህ እደር” ብለው
አጥብቀው ለመኑት፤ በዚህ ምክንያት ከእነርሱ
ጋር ሊያድር ወደ ቤት ገባ። 30ከእነርሱም ጋር
በማእድ ተቀመጠ፤ እንጀራ አንሥቶ የምስጋና
ጸሎት ካደረገ በኋላ ቈርሶ ሰጣቸው። 31በዚያን
ጊዜ ዐይናቸው ተከፈተና ኢየሱስ መሆኑን
ዐወቁ፤ እርሱ ግን ወዲያው ከዐይናቸው ተሰ
ወረ። 32እነርሱም እርስ በርሳቸው “በመንገድ
ሳለን ሲነግረንና ቅዱሳት መጻሕፍትንም እየጠ
ቀሰ ሲያስረዳን ልባችን እንደ እሳት ይቃጠል
አልነበረምን?” ተባባሉ።
33እነርሱም በዚያችው ሰዓት ተነሡና ወደ
ኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄዱ፤ በዚያም ዐሥራ
አንዱን ከጓደኞቻቸው ጋር በአንድነት ተሰብስ
በው አገኙአቸው። 34በዚያን ጊዜ ዐሥራ አንዱ
“ጌታ ኢየሱስ በእርግጥ ተነሥቶአል! ለስምዖ
ንም ታይቶአል!” ይሉ ነበር።
35ሁለቱም ደቀ መዛሙርት በበኩላቸው
በመንገድ ላይ የሆነውን ነገርና ጌታ ኢየሱስ
እንጀራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንዳወቁትም
ተረኩላቸው።

### ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠ
(ማቴ. 28፥16-20፤ ማር. 16፥14-18፤
ዮሐ. 20፥19-23፤ ሐ.ሥ. 1፥6-8)

36እነርሱም ይህን ሲናገሩ ሳሉ ኢየሱስ ራሱ
በመካከላቸው ቆሞ “ሰላም ለእናንተ ይሁን!”
አላቸው።
37እነርሱ ግን መንፈስ የሚያዩ መስሎአ
ቸው ደንግጠው በፍርሃት ተዋጡ። 38ኢየሱስ
ግን እንዲህ አላቸው፤ “ስለምን ትደነግጣላ
ችሁ፤ ስለምንስ በልባችሁ ትጠራጠራላችሁ?
39እጆቼንና እግሮቼን አይታችሁ እኔ ራሴ መሆ
ኔን ዕወቁ፤ ዳስሳችሁም እዩኝ፤ በእኔ እንደምታ
ዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም።”
40ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያ
ቸው፤ 41እነርሱም ከደስታና ከአድናቆት ብዛት
የተነሣ ገና አላመኑም ነበር። ኢየሱስም “እን
ዳች የሚበላ ነገር አላችሁን!” ሲል ጠየቃ
ቸው። 42እነርሱም ትንሽ የተጠበሰ ዓሣ
ሰጡት። 43እርሱም ተቀብሎ በፊታቸው በላ።
44እንዲህም አላቸው፤ “ከእናንተ ጋር በነበ
ርሁ ጊዜ በሙሴ ሕግ፥ በነቢያትና በመዝሙር
መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ መፈጸም
አለበት ብዬ የነገርሁአችሁ ቃል ይህ ነው።”
45ከዚህ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተ
ዋል እንዲችሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው።
46እንዲህም አላቸው፤ “መሲሕ መከራ እንደ
ሚቀበልና በሦስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሣ
አስቀድሞ ተጽፎአል፤ 47እንዲሁም በስሙ የን
ስሓና የኃጢአት ይቅርታ ወንጌል ከኢየሩሳሌም
ጀምሮ በየአገሩ ለሕዝብ ሁሉ እንደሚሰበክ ተነ
ግሮአል። 48እናንተም የዚህ ሁሉ ነገር ምስክ
ሮች ናችሁ፤ 49እነሆ እኔ የአባቴን የተስፋ
ስጦታ እልክላችኋለሁ፤ እናንተም ኀይል ከላይ
እስኪሰጣችሁ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ
ቆዩ።”

### ኢየሱስ ወደ ሰማይ ወጣ
(ማር. 16፥19-20፤ ሐ.ሥ. 1፥9-11)

50ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እነርሱን ከኢየሩሳ
ሌም ከተማ አውጥቶ እስከ ቢታንያ ወሰዳቸው፤
በዚያም እጆቹን ዘርግቶ ባረካቸው። 51ሲባርካ
ቸውም ሳለ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ሰማይ
ወጣ። 52እነርሱም ሰገዱለትና በታላቅ ደስታ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 53እግዚአብሔር
ንም እያመሰገኑ ዘወትር ከቤተ መቅደስ አይለ
ዩም ነበር።

24፥49 ፦ ሐ.ሥ. 1፥4። 24፥50-51 ፦ ሐ.ሥ. 1፥9-11።